# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 058 ጥቅምት 28 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







# ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን ለማስመለስ

**ዳግማዊት አበበ**



**ዜና ትንታኔ**

ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማፍራት በአፍሪካና በተለያዩ ታዳጊ ሀገራት ትልቅ ሀገራዊ ችግር ሆኖ ቆይቷል። ቀደም ሲል ምንጩ ያልታወቀ ንብረት ማፍራት ተጠያቂነትን ለማስከተል በተደረገው ጥረትም ከሕግና ፍትሕ አካላት በኩል ርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል ሙሉ የሕግ ማሕቀፍ እንደሌለና መረጃዎችም የተጠናከሩ አለመሆናቸው ተገልጾ ነበር።

ኢትዮጵያ ውስጥ ችግሩ መኖሩ ቢታወቅም ወንጀሉን ለመከላከል ምንጩ ያልታወቀ ንብረት መውረስን መሠረት ያደረገው የንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ከግለሰቦች ሕገ መንግሥታዊ መብቶች ጋር እንዲጣጣም አድርጋ እያዘጋጀች ይገኛል።

ምንጩ ያልታወቀ ንብረትንም ረቂቅ አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን አዋጁ ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት እስከ 10 ዓመት እንዲሁም 10 ሚሊዮን ብርና ከዛ በላይ ያሉትንም ጉዳዮች ተጠያቂ እንደሚያደርግ አዋጁ አስቀምጧል፡፡

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ


**ምንጩ ያልታወቀ ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**










# የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ዘመናዊ የብረት ጎተራዎች ለአርሶ አደሩ እየተዳረሱ ነው

**በሞገስ ፀጋዬ እና በአዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የድህረ ምርት ብክነትን ለመቀነስ ዘመናዊ የብረት ጎተራዎችና የተሻሻሉ ከረጢቶች ለአርሶ አደሩ የማዳረስ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

"ከረሃብ ነፃ ዓለም" ዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ መለስ መኮንን (ዶ/ር) የድህረ ምርት ብክነት መከላከልን አስመልክቶ ባቀረቡት ጥናት እንዳመላከቱት፤ በዓለም ደረጃ በየዓመቱ ከፍተኛ ምርት ይባክናል፡፡ በኢትዮጵያ አነስተኛ አርሶ አደሮች ደክመው ያመረቱትን ምርት በባሕላዊ መንገድ የሚያስቀምጡ በመሆኑ በከፍተኛ ደረጃ ይባክናል፣ ይሰረቃል፤ በተለያዩ ነፍሳት ይጠፋል፡፡ የምርት ማከማቻ ዘዴዎች ኋላ ቀር በመሆናቸው በጥራትና በመጠን ብክነት ይከሰታል ብለዋል፡፡



እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ የድህረ የምርት ብክነትን ለመከላከል ቀላል የሆኑ የብረት ጎተራዎችንና የተሻሻሉ የምርት መያዥ ከረጢቶችን ለአርሶ አደሮች እየተሰራጨ ነው፡፡ በዚህም በብዙ የሀገሪቷ ክፍሎች የምርት ብክነትና ብክለትን መጠበቅ እየተቻለ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የአርሶ አደሩን ፍላጎትና አቅም መሠረት በማድረግ መንግሥት የተለያዩ ሥልጠናዎችንና ማበረታቻዎችን እየሰጠ እንደሚገኝም ገልጸዋል፡፡


**የድህረ ምርት ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**


# በጎነት ያበሳቸው እንባዎች

**ታደሠ ብናልፈው**

**ዜና ሐተታ**

ወይዘሮ አዳነች አብቼ ይባላሉ፡፡ የኮልፌ ቀራንዮ የወረዳ ዘጠኝ ነዋሪ ሲሆኑ የአምስት ልጆች እናት ናቸው፡፡ አጥንትን ከሚሰረስር የጠዋት ብርድና የፀሐይ ግለትን ተቋቁመው በአነስተኛ ንግድ ተሠማርተው የልጆቻቸውን የዕለት ጉርስ የሚሞሉ ብርቱ እናት ናቸው፡፡

ወይዘሮ አዳነች ልጆቻቸውን ለማሳደግ ከውጣ ውረዱ የሕይወት ልፋትና ድካም በላይ


**በጎነት ያበሳቸው ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**


# 297 ሚሊዮን ብር እና 151 ሚሊዮን ዶላር በማሳገድ ምርመራ መጀመሩን ፎረሙ ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ:- በሕግ የሚያስጠይቅ ተግባር ካለ ምርመራ ተደርጎ ርምጃ እንዲወሰድ በተቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከተለያዩ የመንግሥት ተቋማት ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ እና 151 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ ሃብት ታግዶ የወንጀል ምርመራ ሥራ እየተከናወነ እንደሚገኝ የኦዲት ግኝት የባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም አመለከተ፡፡

የሦስት ዓመታት የኦዲት ግኝት የባለድርሻ አካላት የትብብር ፎረም የጋራ ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማ ውይይት ትናንት ተካሂዷል፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የሺእመቤት ደምሴ (ዶ/ር)፤ ቋሚ ኮሚቴው የተሰጡትን ተልዕኮዎች ለማሳካት እንዲቻል የኦዲት ግኝትን በቅንጅት ከባለድርሻ አካላት ፎረም ጋር ሲሠራ መቆየቱን ተናግረዋል፡፡

ፎረሙ ባለፉት ሦስት ዓመታት ትግበራው፤ ከ297 ሚሊዮን ብር በላይ እና 150 ሚሊዮን 504ሺህ ዶላር ያህል ሃብት እግድ እንዲወጣ ማድረጉን በሪፖርቱ አመልክተዋል፡፡

እንዲሁም 46 መኖሪያ ቤቶች እና አንድ ሕንጻ፣


**297 ሚሊዮን ብር ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል**







ፎቶ ገባቦ ገብሬ

አቶ ፈጠነ ተሾመ

## የኢትዮጵያን የሚቲዎሮሎጂ መሠረተ ልማቶች የሚያዘምን ፕሮጀክት ይፋ ተደረገ

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን የሚቲዎሮሎጂ መሠረተ ልማቶች ማዘመን የሚያስችል ፕሮጀክት የሚተገበር መሆኑን የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር የሚተገብረውን የዓለም አቀፍ መሠረታዊ ምልከታ አውታር ፕሮጀክት በትናንትናው ዕለት ይፋ አድርጓል።

የኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ፈጠነ ተሾመ እንደገለጹት፤ ፕሮጀክቱ ኢትዮጵያ ከዚህ በፊት ለዓለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ የምትጠቀምባቸውን በሰው የሚሠሩ 16 የገጸ ምድር የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ሙሉ በሙሉ ወደ ሰው አልባ (አውቶማቲክ) የሚቀይር ነው፡፡

በተጨማሪም የመረጃ ክፍተት ባለባቸው ቦታዎች ተጨማሪ 13 አዳዲስ የገጸ ምድር አውቶማቲክ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎችን ማቋቋምን የሚያካትትም መሆኑን ገልጸው፤ ከተለያዩ አጋር አካላት ጋር በመተባበር የኢትዮጵያን የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት መሠረተ ልማቶች ለማዘመን እና ለማስፋፋት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።

ዘጠኝ ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን ዶላር የተመደበለት እና በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት የሚጠናቀቀው የዓለም አቀፍ መሠረታዊ ምልከታ አውታር ፕሮጀክት ከሚሠሩት ሥራዎች መካከል መሆኑን አስታውቀዋል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለጻ፣ ፕሮጀክቱ ሙሉ በሙሉ ከተለያዩ አጋር አካላት በተገኘ ድጋፍ ይከናወናል።ፕሮጀክቱን ለማስፈጸምም የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት በአጋርነት እንደሚሠራ እና የኖርዌይ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት ሙያዊ የማማከር ድጋፍ እንደሚያደርግ አስረድተዋል፡፡

የፕሮጀክቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ በሀገር ውስጥ የአየር ሁኔታ መከታተያ ጣቢያ በማቋቋም የምትሰበስባቸውና ለዓለም አቀፍ ማኅበረሰብ የምታጋራቸው የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ለማጠናከር መሆኑን አብራርተዋል፡፡

የከፍታ አየር የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያን በተመለከተ ቀደም ሲል የነበሩንን ዘመናዊ የሚያደርግ እና ተጨማሪ ሦስት አዳዲስ የከፍታ አየር ጣቢያን ለማቋቋም፤ እንዲሁም ከዚህ ጋር የተያያዙ የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎችን እና የቴክኖሎጂ መሣሪያዎችን የሚያሟላ እንደሚሆን አብራርተዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የሚተገበረው የገጸ ምድር ጣቢያዎቹ በየ200 ኪሎ ሜትር ርቀት መላ ኢትዮጵያን እንዲሸፍን ሆኖ የተሰራጨ ሲሆን፤ የከፍታ አየር ጣቢያውም በ500 ኪሎ ሜትር ኢትዮጵያን እንዲሸፍን በአዲስ አበባ፣ በነገሌ ቦረና፣ በመቀሌ፣ በጅግጅጋ እና በጋምቤላ እንደሚተከሉ ተናግረዋል፡፡

ፕሮጀክቱ መረጃዎችን ያለማቋረጥ በመሰብሰብና ለዓለም በማጋራት እንዲሁም ከመላው ዓለም የሚሰበሰብ መረጃን በመቀበልና በመተንተን የአየር ሁኔታ መረጃ ተደራሽነትን ለማስፋፋት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረክታል ነው ያሉት፡፡

በዓለም አቀፍ፣ በአሕጉር አቀፍ እና ሀገራዊ የአየር ትንበያ ሞድሎች ውስጥ መረጃዎቹ እንዲካተቱ በማድረግ የትንበያ ትክክለኛነትና ጥራት ለማሳደግ ፕሮጀክቶች ወሳኝ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በዚህም የተሻሻለ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎት በመስጠት የአየር ፀባይ ለውጥን የመቋቋም አቅምን ይጨምራል ብለዋል።

በአጠቃላይ ፕሮጀክቱ ከአደገኛ የአየር ሁኔታና ፀባይ ተጋላጭነትን ለመቀነስ፣ የአየር ንብረት ለውጥ የፓሪስ ስምምነትንና የዘላቂ ልማት ግብን ለማሳካት፣ የሚቲዎሮሎጂ ምልከታን ለማጠናከርና ለማዘመን፣ ለዓለም አቀፍ መረጃ ልውውጥ እና ሌሎች በርካታ ጠቀሜታዎችን እንደሚያስገኝ ገልጸዋል።

# የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር ፍትሐዊ የንግድ ሥርዓትን ማስፈን ይገባል

**መስከረም ሰይፉ**

አዲስ አበባ፡- የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓትን በማጠናከር ፍትሐዊና ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓትን ማስፈን እንደሚገባ የአዕምሯዊ ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

ባለሥልጣኑ በሀገራዊ የአዕምሯዊ ንብረት ጉዳዮች ዙሪያ ከፖሊሲ አውጪዎችና ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ትናንትናው ውይይት አካሂዷል፡፡

የባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር ወልዱ ይመስል እንደገለጹት፤ የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓትን ማጎልበት ከተቻለ የንግድ ሥርዓቱን ፍትሐዊነት ማጠናከር ይቻላል።

የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ምዝገባ በፈጠራ ሥራዎች ላይ ቁልፍ ሚና ቢኖረውም በሚጠበቀው ልክ ትኩረት እንዳልተሰጠው ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ዓለም አቀፍ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ ስምምነቶችን በመፈጸም ተገቢውን ጥበቃ ማድረግ ከቻለች የፈጠራ ሥራዎችን ማብዛት እንደሚቻል ጠቁመዋል።

ዓለም አቀፍ የአዕምሮ ንብረት ስምምነቶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እየቀረቡ ከብሔራዊ ጥቅም ጋር በማይጋጭ መልኩ ተግባራዊ እንዲሆኑ እየተሠራ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህም የአዕምሯዊ ንብረት ባለሀብቶች ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡና ሥራ ላይ እንዲያውሉ ያግዛል ብለዋል፡፡

ባለሥልጣኑ በዘርፉ ለሚያከናውናቸው የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃና ልማት ሥራዎች እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ግንኙነቶቹ በቂ ትኩረትን ሊሰጠው፣ ተቋማዊ አቅሙን እንዲያድግ፣ የሕግ ማዕቀፎችን እንዲሻሻሉና የአፈጻጸም ችግሮችን በመቅረፍ ረገድ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ገልጸዋል።



አቶ ወልዱ ይመስል



ፎዚያ አሚን

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ፎዚያ አሚን በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ የሚሠሩ የፈጠራ ሥራዎችና ምርምሮች በአግባቡ የአዕምሯዊ ንብረት ምዝገባ ሊካሄድላቸው ይገባል ብለዋል።

የፈጠራን ሥራዎች በሀገር ውስጥ፣ በአሕጉር እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና እንዲያገኙ እየተሠራ መሆኑንም አመላክተዋል።

ፈጠራና ቴክኖሎጂዎች መነሻቸው የማኅበረሰቡ ዕውቀት፣ ባሕልና ዕሴት በመሆኑ የአንድ ሀገር የሥልጣኔ ምሶሶዎች መሆናቸውን መገንዘብ ይገባል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በኢትዮጵያ ታዳጊዎች፣ ወጣቶች፣ ምሑራንና ተመራማሪዎችን በማሳተፍ በተለያዩ መስኮች በሚሠሩ የፈጠራና ቴክሎጂዎች ሥራዎች ተስፋ ሰጪ ውጤቶች መታየት እንደጀመሩ ገልጸዋል።

የአዕምሯዊ ንብረት ጥበቃ ሥርዓት ፈጠራን በማበረታታት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርን በማመቻቸት፣ ፍትሐዊና ተወዳዳሪ የንግድ ሥርዓትን በማስፈን ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ ዘርፉን በከፍተኛ ደረጃ መደገፍ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ የዓለም አዕምሯዊ ንብረት ድርጅት ከሚያስተዳድራቸው ስምምነቶች መካከል የናይሮቢና የማራካሽ ስምምነቶችን መፈረሟን ገልጸው፤ ይህም በዓለም አቀፉ የኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ውስጥ ጉልህ ሚና ለመጫወት እና በቴክኖሎጂ ሽግግር፣ በንግድ ኢንቨስትመንትና በሌችም መስኮች ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን ለማሳደግ እንደሚረዳት አብራርተዋል፡፡

ባለሥልጣኑ የሚያስተዳድራቸውን አዋጆች ለማሻሻል እና ተጨማሪ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ለማፀደቅ የሕግ አውጪ አካላትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚና የማይተካ በመሆኑ ትብብር እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ቢሮው በብልሹ አሠራርና ሌብነት ላይ የጀመረውን ርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል

## - 131 ፈጻሚዎች ተጠያቂ ተደርገዋል

**ማሕሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ በሚሰጠው የኦንላይን አገልግሎት ላይ በሚከሰቱ ብልሹ አሠራርና ሌብነት ላይ የጀመረውን እርምጃ አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ የንግድ ምዝገባና ፈቃድ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የተስተዋሉ ብልሹ አሠራሮች እና በሐሰተኛ አካውንቶች የወጡ ንግድ ፈቃዶችን አስመልክቶ በትናንትናው ዕለት መግለጫ ሰጥቷል።

የአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ምክትል ቢሮ ኃላፊ እና የግብይት ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍሰሐ ጥበቡ በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ቢሮው በከተማዋ ፈጣንና ቀልጣፋ የንግድ ሥርዓትን ለማስፈን በሚሰጠው የኦንላይን አገልግሎት ላይ በሚከሰቱ ብልሹ አሠራርና ሌብነት ላይ የጀመረውን ርምጃ አጠናክሮ ይቀጥላል።

ቢሮው የኦንላይን አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ለቁጥጥር አመቺ ለማድረግ ከወረዳ ጀምሮ በአንድ ሺህ 200 ባለሙያዎች ሲሰጥ የነበሩትን አገልግሎቶችን በአንድ ማዕከል በ26 ባለሙያዎች ብቻ አገልግሎቱን እየሰጠ ይገኛል።

ቀደም ባሉ አካውንቶች የተሰጡ አገልግሎቶችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ሥራዎች መሥራታቸውን አቶ ፍስሐ ገልጸው፤ በተሠራ የማጣራት ሥራም ከእውቅና ውጪ በሰባት ክፍለ ከተሞች 339 ሐሰተኛ አካውንቶች ሕገወጥ አገልግሎት ሲሰጡ እንደነበር ማረጋገጥ መቻሉን አብራርተዋል።



አቶ ፍሰሐ ጥበቡ

የተሳሳተ አካውንት በመክፈትና በመተባበር ተሳታፊ የሆኑ ፈጻሚዎችን በሕግ እንዲጠየቁ፣ አስተዳደራዊ እርምጃና በዲሲፕሊን እንዲጠየቁ እንዲሁም አለአግባብ የተከፈቱ አካውንቶች እንዲዘጉ እየተደረገ እንደሚገኝ አስታውቀዋል።

እንዲሁም በበጀት ዓመቱ አጠቃላይ 130 ሺህ በላይ አገልግሎቶች በአንድ ማዕከል የተሰጡ ሲሆን በተሠራ የማጣራት ሥራም 362 በላይ አገልግሎቶች አሠራርን ባልጠበቀና መስፈርትን ሳያሟሉ አገልግሎት መስጠታቸውን ተረጋግጧል ብለዋል።

ከእነዚህ ውስጥ 32 የሚሆኑ አገልግሎቶች ዋና ዋና የሚባሉና የመንግሥትን ጥቅም ሊያሳጡ የሚችሉ አገልግሎቶች በ15 ፈፃሚዎች በተሰጣቸው ኃላፊነት መስፈርት የማያሟላ አገልግሎት የሰጡ እና ባልተሰጣቸው ኃላፊነት ሕገ ወጥ ሥራ የሠሩ ናቸው።

በአጠቃላይም ከ430 በላይ አገልግሎቶች መስፈርት ሳያሟሉ መሰጠታቸውን እና የተሳተፉ 131 ፈጻሚዎችና አመራሮች ተጠያቂ መደረጋቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይም መሰል ሕገወጥ አካውንቶች እንዳይከፈቱ ጥብቅ ቁጥጥር ማድረግ ቴክኖሎጂውን ይበልጥ በማዘመን ብሎም የአገልግሎት ኦዲቱም ቀጣይነት ባለው አግባብ የማስኬድ ሥራ የሚሠራ መሆኑን አቶ ፍስሐ አስታውቀዋል።

በመሆኑም ቢሮው የሚሰጡ አገልግሎቶችን ኦዲት በማድረግ በብልሹ አሠራርና ሌብነት ላይ የጀመረውን እርምጃና ተጠያቂነት የማስፈኑን ተግባር አጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

# አካታችነትን በተግባር እያሳየ ያለው ሀገራዊ ምክክር

ቃልኪዳን አሳዬ

**ዜና ሐተታ**


አቶ ዓለሙ እንደሻ ይባላሉ። የመንጃ ጎሳ አባል ናቸው። አቶ ዓለሙን ከሸካ ዞን ማሻ ወረዳ በባሕልና በሙያቸው ምክንያት የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች ተወካይ በመሆን የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ክልል የኅብረተሰብ ተወካዮችና የባለድርሻ አካላት አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረክ ላይ ሲሳተፉ ነው ያገኘናቸው።

አቶ ዓለሙ፤ በውይይቱ በርካታ ሀገራዊና ለሀገር ጠቃሚ የሆኑ አጀንዳዎች እያደራጁ ስለመሆናቸው ገልጸው፤ አጀንዳዎቹ ተቀባይነት አግኝተው ወደ ተግባር ከተቀየሩ ኢትዮጵያን አንድ የሚያደርጉ እና ወደሚፈለገው ብልፅግና ማማ ላይ እንድትወጣ የሚያስችሉ መሆናቸውን ይጠቁማሉ።


በምክክሩ ምንም አይነት የሀሳብ እና ነፃነት ገደብ ሳይኖር እያንዳንዱ የማኅበረሰብ ክፍል ተወካይ ለአጀንዳ የሚሆን ሀሳብ እያቀረበ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ዓለሙ፤ የሀሳብ ግጭቶችንም በማስማማት ወደሚያግባባ ሀሳብ በመምጣት የምክክር ሂደቱ እየተካሄደ መሆኑን ያነሳሉ።

ወክለው የመጡትን የማኅበረሰብ ክፍሎች በባሕላቸውና በሙያቸው እየደረሰባቸው ያለው መገለል በውይይት እንዲፈታ ሀሳባችንን እያቀረብን ነው። አሁን ላይ በሀገር ደረጃ እየተከናወነ የሚገኘው የሀገራዊ ምክክር ለየት የሚያደርገው ታችኛውን የማኅበረሰብ ክፍል ባካተተ መልኩ እየተከናወነ በመሆኑ ነው፤ ለዚህም ችግሮቻቸው እንደሚፈቱ እምነት እንዳላቸው አቶ ዓለሙ ያመላክታሉ።

እንደ አቶ ዓለሙ ገለጻ፤ የምክክር ኮሚሽኑ ማንም አካል ጣልቃ ገብነት ሳይኖር ችግሮቻችንን እንድንናገር ዕድል ሰጥቶናል። ችግር ተፈጥሯዊ በመሆኑ መከሰቱ አይቀርም፤ ችግሮች እንዲፈጠሩ የሚያደርገው የአንዱን ባሕልና የአኗኗር ዘይቤ የበታች በማድረግ የራስን ማጉላት አንዱ ምክንያት ነው። የትላንትና መጥፎ



አቶ ዓለሙ እንደሻ



አቶ ታመነ ኃይሌ




ወይዘሮ የትምወርቅ ፍቅሩ

ታሪካችንን አስወግደን በመልካም እሳቤዎችን መተካት አለብን።

አቶ ታመነ ኃይሌ እንደ አቶ ዓለሙ ከካፋ ዞን ጊምቦ ወረዳ በባሕልና በሙያቸው ምክንያት የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ወክለው አጀንዳ የማሰባሰብ የምክክር መድረክ ተሳትፎ እያደረጉ ነው። አካል ጉዳተኛም ቢሆኑ ሕይወትን ለማሸነፍ የእንጨትና ብረታብረት ሥራዎችን በመሥራት እንደሚተዳደሩ ይናገራሉ።

በዚህ የምክክር ሂደትም ቀርበው በሚሠሯቸው ሥራዎችና በባሕላቸው ምክንያት መገለል እየደረሰባቸው እንደሆነ መናገራቸውን የሚያወሱት አቶ ታመነ፤ የሀሳብ መለያየቶች ተፈጥሯዊ ናቸው፤ ለዚህም ጎራ በመያዝና በዘፈቀደ ሳይሆን ተቀራርቦ በመነጋገር ወደአንድ ሀሳብ መምጣት ይቻላል ይላሉ።

አቶ ታመነ በምክክር ሂደቱ የሀሳብ ነፃነትን መሠረት በማድረግ ሀሳባቸውን እያቀረቡ ስለመሆናቸውና ምክክሩ በዚህ የሚቀጥል ከሆነ ለውጥ አምጪ መሆኑን በመጠቆም፤ በምክክሩ የሚነሱ አጀንዳዎች በትክክል ተደራጅቶ በተገቢው ከተሠራና እንደሀገር ውጤታማ መሆን ይቻላል ነው ያሉት።

እንደ አቶ ታመነ ገለጻ፤ በምክክሩ ሀገሪቱን ሊገነቡ የሚችሉ ሀሳቦችን ተሳታፊዎች በነፃነት እያነሱና በጋራ በመመካከር አጀንዳዎቻቸውን እያጠናከሩ ነው። በዚህም እንደሀገር የጋራ ችግሮቻችን ምን እንደሆኑ በመለየት ውጤት ለማምጣት የመንግሥት እና የኅብረተሰቡ ድርሻ የጎላ ነው።

ይህ ሀገራዊ ምክክር ሀገራዊ ሠላምንና አንድነትን የሚያመጣው ሁሉም የማኅበረሰቡ ክፍል የሀገሬ ጉዳይ ይመለከተኛል በሚል ሀሳቡን አንፀባርቆ መፍትሔ ማግኘት ሲችል ነው የሚሉት ደግሞ ከምዕራብ ኦሞ ዞን ባቹማ ወረዳ በባሕልና በሙያቸው ምክንያት የተገለሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ወክሎ የተሳተፉት ወይዘሮ የትምወርቅ ፍቅሩ ናቸው።

ወይዘሮ የትምወርቅ የሚኖሩበት የሜኒት ማኅበረሰብ ሸክላ በመሥራት የሚተዳደር ሲሆን ይህ ሀገራዊ ምክክር እንደሀገር ያሉብንን ችግሮች እንድንፈታ ያግዘናል። ሰላም ካለ መሥራት፣ መማርና መለወጥ ይቻላል። ለዚህም በምክክሩ ሀሳቦቻችንን እያንሸራሸርን ነው ይላሉ።

ሀገራዊ ምክክሩ በሀገራችን እስከአሁን የነበሩ ችግሮችን በንግግርና በምክክር ለመፍታት ኮሚሽኑ የጀመረው ጥሩ ጅምር መሆኑን የሚገልጹት ወይዘሮ የትምወርቅ፤ ከቤተሰብ ጀምሮ በመመካከር እና በመደማመጥ ለውጥ ማምጣት እንደሚቻል ይናገራሉ።

እያንዳንዱ ሰው የራሱን ሀሳብ አፍኖ ከሚኖር ይልቅ ሀሳቡን እንዲገልጽ መደረጉ እጅጉን የሚያስደስት ነው። ከዚህ ቀደም ዜጎች ለሀገራቸው እድገት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ብዙም አመቺ ሁኔታዎች አልነበሩም የሚሉት ወይዘሮ የትምወርቅ፤ በአሁን ወቅት ዜጎች በሀገራቸው ሠላም እንዲሰፍን ሀሳብ እንዲያዋጡ ዕድል መስጠቱ አስደሳች መሆኑን ነው የሚናገሩት።

# የከተማ ግብርና ለምግብ ሉዓላዊነት መረጋገጥ

ዮርዳኖስ ፍቅሩ

የኢትዮጵያ ግብርና በአመዛኙ የዝናብ ጥገኛ ሆኖ መቆየቱ፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች አለመሟላት፣ የሕዝብ ቁጥር መጨመርና የመሬት መራቆት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንቅፋት ከሆኑ ምክንያች መካከል ይጠቀሳሉ፡፡

ባለፉት ጥቂት ዓመታት የምግብ ሉዓላዊነትን ማረጋገጥ የሚያስችሉ እንደ ሌማት ትሩፋት፣ የከተሞች የከተሞች ግብርና ተግባር ላይ ውለዋል፡፡ በተከናወኑ ተግባራት በሰብል፣ በእንስሳትና በጓሮ አትክልት ልማት እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች እየተገኙ ይገኛሉ፡፡ እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች፣ የእለት ምግብን ከማረጋገጥ በተጨማሪ፣ ዜጎች ሥራ መፍጠር እንዲችሉና የግብርና ምርት ተጠቃሚዎች በቀጥታ ከአምራች ገበሬው ጋር እንዲገናኙ አስችሏል፡፡ በከተማ ግብርና ዘርፍም ዜጎች በራሳቸው ጓሮ የራሳቸውን ምግብ ፍጆታ ከማምረት አልፈው ለገበያ እያቀረቡም ይገኛሉ፡፡

በሐዋሳ ከተማ አስተዳደር ግብርና መምሪያ ኃላፊ፣ አቶ አበባየሁ ላሊማ፣ በመኸር ወቅት የከተማ ግብርናን በተጠናከረ ሁኔታ ለማስኬድ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡ በከተማዋ ባሉ 32 ገጠር ቀመስ ቀበሌዎች በእርሻና በእንስሳት ዘርፍ ሰፋፊ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በመሬት ላይ በሚሠራ የጓሮ አትክልት ልማት 5 ሺህ 595 ሰዎችን ያሳተፈ ሥራ ለመሥራት እቅድ ተይዞ በታቀደው መሬት ላይ አስፈላጊ ዘር መዘራቱን የተናገሩት ኃላፊው፤ ምርት ዘርና አስፈላጊ ማዳበሪያዎችም ጥቅም ላይ በመዋላቸው የሚፈለገው ምርት ይገኛል ተብሎ እንደሚጠበቅ ያመለከታሉ፡፡

በከተማ ደግሞ በ7ቱም ክፍለ ከተሞች በእቃ ላይ አትክልት የማልማት ሥራዎች እየተሠሩ የሚገኝ ሲሆን፣ 346ሺ ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ ወደ ሥራ ተገብቷል፤ ከ340ሺ በላይ ችግኞችን፣ በእቃ ላይ መትከል ተችሏል፡ ፡ በከተማ በመሬት ላይ ልማት 50 ሄክታር ለማልማት ታቅዶ በመንግሥትና በግል ተቋማት፣ በጤና ተቋማትና



እና በትምህርት ቤቶች ላይ ከ48 ነጥብ 9 ሄክታር ማልማት ተችሏል ይላሉ፡፡

ከጓሮ አትክልት ልማት የሚፈለገውን ያህል ምርት ለማግኘት አስፈላጊ ክትትልና እንክብካቤ እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በተለይም በሽታ እንዳይጠቁ ክትትል እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ቀደም ሲል በክረምት ወራት የተመረቱ ምርቶች በመድረሳቸው ገበያን ከማረጋጋት አንጻር፣ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች በገበያ ላይ ያለው የምርት እጥረትን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ መቻሉንም አንስተዋል፡፡

ከቀይ ሽንኩርት አንጻር ግን እጥረት መግጠሙን ያነሱት ኃላፊው፤ በቀጣይ በበጋ መስኖ ፕሮግራም ቀይ ሽንኩርት ላይ ሰፊ ሥራ ለመሥራት መታቀዱን አስታውቀዋል፡፡

በእንስሳት እርባታ ዘርፍ የተሠሩ ሥራዎችን በተመለከተም ኃላፊው እንደገለጹት፣ የእንስሳት ልማት ዘርፍ ከምግብ ዋስትና፣ ከገበያ አቅርቦት እንዲሁም ከምግብና ሥነ ምግብ ጉዳዮች አኳያ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሠራበት የሚገባ እንደመሆኑ የምርት ጥራትና ምርታማነትን የሚያሻሽሉ በርካታ ሥራዎችን ማከናወን ተችሏል፣ በዚህም በርካታ የእንስሳት ዝርያዎችን ማሻሻል የተቻለ ሲሆን፣ በተለይም የወተት ምርት ላይ በተሠራው ሥራ በቂ የወተት ምርትን ለከተማዋ ነዋሪ በተሻለ መጠን ማቅረብ ተችሏል፡፡

በዶሮ እርባታ ዘርፍም፣ ከአንድ ቀን ጫጩት ጀምሮ የተለያዩ በዘርፉ ልምድ ያላቸውን ግለሰቦች፣ ማኅበራትና ወጣቶች በማስተባበር የዶሮ ምርትን ላይ ሰፋፊና ለውጥ ያስገኙ ሥራዎች መሠራታቸውን አቶ አበባየሁ ተናግረዋል፡ ፡

ኃላፊው እንደገለጹት፣ አምራቾች ያመረቱትን ምርት ሳይቸገሩ ተጠቃሚው ጋር የሚያደርሱበት ሁኔታም ተመቻችቶላቸው ምርታቸውን አውጥተው የሚሸጡባቸው ቦታዎችም ተመቻችቶላቸው ምርታቸውን እያቀረቡ ይገኛሉ፡፡

ከሥራ ዕድል ፈጠራም አንጻር በርካታ በከተማዋ ያሉ ወጣቶች የግብርናውን ሥራ ውጤታማነት እያዩ ሙያዊ ምክርና ድጋፎችን በመጠየቅ በግብርና ተግባር ላይ ለመሠማራት ፍላጎት እያሳዩ እንደሚገኙም በማንሳት፣ በገጠር ቀመስ ቀበሌዎችም ሆነ በከተማ ግብርና የሚከናወኑ ተግባራት የእያንዳንዱ ቤተሰብ ሕይወት የሚለወጥበት በመሆኑ ባለሙያው ተገቢውን ድጋፍ እንዲያደርግ ተገቢው ግብዓት እንዲቀርብላቸውና ሥራዎች በዕቅድ መሠረት እንዲፈጸሙ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል ያሉት ኃላፊው፤ ከእቅድ ወደኋላ መቅረትን ፈጽሞ እንደማይቻል አድርገን ለሀገራችን የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ የሚያስችሉ ሥራዎችን እየመራን ነው ሲሉ አመልክተዋል፡፡

በሃዋሳ ዩኒቨርሲቲ ግብርና ኮሌጅ የሥነ ምግብ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ትምህርት ቤት መምህርና ተመራማሪ ፈቃዱ ረታ እንደሚሉት "በተለይ በከተማ በትንሽ መሬት ላይ የሚከናወነው የግብርና ልማት ሥራ ኢኮኖሚን ከመደገፍ ባለፈ ጤናማ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ከፍተኛ ድርሻ አለው ይላሉ። የከተማ ግብርና ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓትን በማጎልበት ጤናው የተጠበቀ አምራች ትውልድ እንዲፈጠር የሚያግዝ ነው ያሉት።

እንደ ሀገር መንግሥትም ለሥራው ትኩረት መስጠቱ የማኅበረሰቡን ግንዛቤ ስለሚያሳድግ ልማቱን ውጤታማ ያደርገዋል። በአሁኑ ጊዜ መንግሥት በትኩረት እያከናወነ ያለውን ሥራ በምርምር መደገፍና ቀጣይነት እንዲኖረው ማገዝ ያስፈልጋል ሲሉ ይገልጻሉ።

ዜጎች ከዚህ ልምድ ወስደው ባላቸው መሬት ላይ ልማቱን ሊያጠናክሩ እንደሚገባም ነው መምህር ፈቃዱ ያመለከቱት። ቶሎ የሚደርሱና በየጊዜው ለምግብነት የሚውሉ የተለያዩ አትክልቶችን አልምቶ በብዛት መመገብ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን በመከላከል በኩል ጥቅሙ ከፍተኛ መሆኑንም ገልጸዋል።

ኅብረተሰቡ የከተማ ግብርናን ልማድ አድርጎት እንዲቀጥል ደግሞ ከዘር አቅርቦት ጀምሮ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና ግንዛቤ የማሳደግ ሥራን ተከታታይነት ባለው መልኩ ማጠናከር እንደሚገባ ነው ያመለከቱት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ዓለም አቀፍ እውቅና እና ድጋፍ ሊቸረው የሚገባ ሀገራዊ ስኬት!

ዓለማችንን እየተፈታተኑ ካሉ ችግሮች በዋንኛነት የሚጠቀሰው የአየር ሙቀት መጨመር ነው። ችግሩ ዓለምን በብዙ መልኩ እየተፈታተነ ቢገኝም ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አሁንም ዓለም አቀፍ ስጋት እንደሆነ ቀጥሏል። በተለይም የችግሩ ዋነኛ ተጠቂ የሆኑት በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ሕዝቦች ዛሬም ለችግሩ ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጠው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እየጮኹ ነው።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ ዓለማችን በ19ኛው ክፍለ ዘመን ከነበረችበት የሙቀት መጠን አሁን በ1.2 ዲግሪ ሴልሺዬስ፤ ወደ አየር ንብረት የሚለቀቀው የካርቦን ዳይኦክሳይድ መጠንም 50 በመቶ ጨምሯል። በችግሩ ዙሪያ የተጠናከረ ርምጃ መውሰድ ካልተቻለ የምድራችን ሙቀት መጠን በያዝነው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ወደ 2 ዲግሪ ሴልሺዬስ ከፍ ሊል ይችላል።

ችግሩ አሁን ላይ የሰዎችንና የተፈጥሮ ሃብትን ሕልውና እየተገዳደረ ይገኛል። ከዕለት ተዕለት እያደገ ያለው የአየር ሙቀት መጨመር አንዳንድ ሥፍራዎችን ወደ በረሃነት እየቀየረ ነው። እየተከሰተ ካለው ከፍተኛ የዝናብ መጠን ጋር በተያያዘም የተለያዩ የዓለም አካባቢዎች በጎርፍ እየተጠቁ ነው።

የአየር ሙቀት መጨመር ጋር ተያይዞ፤ በርካታ የአፍሪካ ሃገራት በድርቅ እንደሚጠቁ በዓለም ላይ በጣም ለም በሆኑ የግብርና አካባቢዎች የሰብል ምርት እንደሚቀንስ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘም በዓለም አቀፍ ደረጃ ረሃብ እና የተመጣጠነ ምግብ እጥረት ሊያስከትል እንደሚችልም በዘርፉ እየተደረጉ ጥናቶች እያመላከቱ ነው።

በችግሩ ምክንያት አዳዲስ ገዳይ በሽታዎችን እንደሚከሰቱ፣ ሚሊዮኖች በውሃ መጠን መጨመር ምክንያት ከመኖሪያቸው ቀያቸው ሊፈናቀሉ፤ እፅዋትና እንስሳት ከምድራችን ሊጠፉ እንደሚችሉ እና በመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት የሚገኙ የእርሻ ቦታዎች ወደ በረሃማነት እንደሚቀየሩ እያስጠነቀቁ ነው።

ችግሩ አሁን ላይ “ከረሀብ ነፃ የሆነች ዓለም” ለመፍጠር ለተጀመረው ዓለም አቀፍ መነቃቃት ትልቅ ፈተና እንደሚሆን ይታመናል። በተለይ በግብርናው ዘርፍ ላይ እየፈጠረ ካለው ስጋት አኳያ፣ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ በኃላፊነት መንፈስ ፈጥኖ መንቀሳቀስ ካልቻለ ጥረቱ “ላም አለኝ በሰማይ….” አይነት መሆኑ የማይቀር ነው።

በተለይም የበለፀጉ ሀገራት የችግሩ ዋነኛ ፈጣሪዎች/ባለቤቶች ከመሆናቸው አንጻር፣ ከቋንቋ ባለፈ በተጨባጭ ለችግሩ ዋነኛ መፍትሔ መሆን፤ ችግሩን ለመከላከል በሚደረገው ዓለም አቀፍ ጥረት ውስጥ በታማኝነት ዋነኛ ተዋናይ ሆኖ መገኘት ይኖርባቸዋል።

ችግሩ አሁን ላይ በተጨባጭ እያስከተለ ካለው አደጋ አኳያ፣ እነዚህ ሀገራት የችግሩን ግዝፈት ከመተረክ ባለፈ፣ ለችግሩ አዳዲስ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማቅረብ፣ ቀደም ሲል በተለያዩ ወቅቶች ችግሩን አስመልክቶ ለተደረሱ ስምምነቶች ተግባራዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅባቸዋል ።

ይህንን ግዴታቸውን መወጣት ባልቻሉበት ሁኔታ፣ ከረሀብ ነፃ የሆነች ዓለም ለመፍጠር የሚደረገው ጥረት “ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ” አይነት መሆኑ ስለማይቀር፣ ዓለም አቀፉ ኅብረተሰብ ሆነ፣ የጉዳዩ በአሳሳቢነት የሚመለከታቸው አካላት ሀገራቱ የሚጠበቅባቸውን በኃላፊነት መንፈስ እንዲወጡ ጫና ሊያሳድሩ ይገባል ።

ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለም ለመፍጠር በዓለም አቀፍ ደረጃ የተጀመረው መነሳሳት፤ በቅድሚያ ዓለምን ከተደቀነባት ሁለንተናዊ ስጋት ከመታደግ የሚጀምር ሊሆን ይገባል። ለዚህም መላው ዓለም ድምፁን ከፍ አድርጎ መጮኽ፤ ለዚህ የሚሆን ቁርጠኝነት መፍጠር ይኖርበታል።

ችግሩን ባላቸው አቅም ለመከላከል ለሚሞክሩ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ዓለም አቀፍ እውቅና እና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት፤ ተጨባጭ ተሞክሯቸውን በማስፋት ችግሩን ለዘለቄታው መቋቋሚያ ስትራቴጂክ አቅም አድርጎ መውሰድም ያስፈልጋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ስድስት ዓመታት ከፍተኛ ሀብት በመመደብ እና መላውን ሕዝብ በማንቀሳቀስ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር 40 ቢሊዮን የሚጠጉ ችግኞችን በመትከል፤ ችግሩን ባላት አቅም ለመከላከል ያላትን ቁርጠኝነት በተጨባጭ አሳይታለች።

በዚህም የአየር ሙቀት መጨመር የታመመ የአየር ንብረቷን ከማከም ባለፈ፤ ለመጪዎቹ ትውልዶች የተሻለ የመኖሪያ አካባቢ ለመፍጠር በቁርጠኝነት እየሠራች ነው። በዓለም አቀፉ ደረጃም የችግሩ የመፍትሔ አካል በመሆን ጎልታ ወጥታለች ።

ይህ ተጨባጭ ተሞክሮዋ በምግብ እህል እራስን በመቻል ከረሃብ ነፃ የሆነ ሀገር ለመፍጠር እያደረገችው ላለው ጥረትም ትልቅ ጉልበት፣ ዘላቂ የግብርና ልማት እውን ለማድረግም ስትራቴጂክ አቅም እየሆናት ነው። በዚህም ተስፋ ሰጭ ውጤት እያስመዘገበች ትገኛለች።

ይህ የሀገሪቱ ተሞክሮ፤ በአየር ሙቀት መጨመር የታመመ የአየር ንብረትን በማከም የግብርና ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ ከረሃብ ነፃ የሆነች ዓለም መፍጠር እንደሚቻል በተጨባጭ ያመላከተ እና ተገቢ ዓለም አቀፍ እውቅና እና ድጋፍ ሊቸረው የሚገባው ግሩም ስኬት ነው!


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ሁሉም በተሠማራበት የሚጠበቅበትን በኃላፊነት ይወጣ

**አዶኒስ (ከሲኤምሲ )**

አካባቢያችን ያማረ እንዲሆን፣ ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ጣቢያዎች፤ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ መንገዶች… በአጠቃላይ የተሟላ መሠረተ ልማት እንዲኖረን እንፈልጋለን፤ እንመኛለን። በሌሎች ሀገሮች ያየናቸው ቴክኖሎጂዎች የሥልጣኔ መንገዶች ሁሉ በሀገራችን ሆኖ ማየትን እንሻለን።

በውጪ ሀገራት በፊልምና በዶክመንተሪ ወይም ለጉብኝትና ለትምህርት በሄድንባቸው ሀገራት የምናያቸው የመንገድ መሠረተ ልማቶች በሀገራችን እንዲሆኑልን እንመኛለን። የግል መኖሪያ ቤት ባለቤት መሆንን እንፈልጋለን። መመኘት ብቻም ሳይሆን ለምን በእኛ ሀገር ብለን እንቆጫለን። መቼ ነው እኛም እንደ ውጪዎቹ የሠለጠንን የምንሆነው ብለን እናልማለን።

ሁሉንም የተመኘነውን ነገር ያሰብነውን ሁሉ ማድረግ ግን እንደሚቻል በቅርቡ ያየናቸው ጅምር ልማቶች ያሳዩናል። እነዚህን ነገሮች በተሟላ መልኩ ለማግኘት ምን ማድረግ ይገባናል፤ ምን እንሥራ? እንዴት እንሥራ? ከእኔ ምን ይጠበቃል? እኔ ለማስበው የበለፀገች ሀገር ከእኔ የሚጠበቀው ምንድነው ብሎ ራስን መጠየቅ ደግሞ ያስፈልጋል። ሁልጊዜ ከድህነት ተስፈንጥረው የወጡ ሀገሮች ብለን የምንጠቅሳቸው አሉ። እነ ኮሪያ፣ ቻይና ሲንጋፖር … በዋናነት የምናነሳቸው ናቸው።

እነዚህ ሀገሮች የድህነትን ጥግ ያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ ከእኛ ድጋፍ ያገኙ ሀገሮች መሆቸውን ታሪክ ጭምር ያሳየናል። እድገታቸው እኛ የሥልጣኔ በር ከፋች ከሆንባቸው ዘመን ባጠረ ጊዜ ነው። ታሪካቸው የቅርብ ጊዜ ነው። ሆኖም ግን አንድ ጀነሬሽን የሆነ ቦታ ላይ ቆም ብሎ በቆራጥነትና በትብብር አንድ በመሆን፤ ለለውጥ በመነሳት ተጠቃሽ ሀገር ለመሆን በቅተዋል። ምንም በልተው ምንም ሆነው ብቻ ዛሬ ለደረሱበት የእድገት ደረጃ በቅተዋል። የአደጉ ሀገራት የሚለውም መገለጫቸው ሆኗል። ከእነዚህ ሀገራት ምን እንማራለን ?

እኛስ እንዴት ወደ ብልፅግናው እንጓዝ ብለን ቆም ብለን ማሰብ አለብን። መኀነታተሉን፣ መሳሳቡን፣ ሴራን ትተን ሥራ ሠርተን ለሀገር መሥራት እንዳለብን ማወቅ አለብን። ከሙስና የፀዳ ሥራ መሥራት አለብን። ከሁላችን የሚጠበቅብንን ግብርና ታክስ ሌላውንም መክፈል አለብን። "የቄሳርን ለቄሳር…" እንደሚባለው ማለት ነው። ያኔ በሀገራችን የምንፈልገውን ልማት እናያለን ።

ያኔ ለምን መሠረተ ልማት አልተሟላላንም ብለን እንጠይቃለን። ይሠራልን ብለን ድምፃችንን ከፍ አድርገን መውቀስ እና መክሰስ እንችላለን። ማንም ሰው ሊኖር የሚችለው በአንድ አይነት መንገድ አይሆንም፤ የሁሉም የሀብት መጠን ይለያያል። ሁሉም መክፈል ያለበት ግብር በእዛው መንገድ ይሆናል። ሁሉም መክፈል ያለበት ታክስ፤ ቫት የሰበሰበውም የንግድ ማኅበረሰብ የሰበሰበውን በሐቀኝነት ወደ መንግሥት ካዝና ማስገባት አለበት። ይሄ ግዴታ ነው፤ በዚህ መንገድ ተሰብስቦ ወደ ኪስ ማድረግ ኃላፊነትን ካለመወጣትም በላይ በሕግም ያስጠይቃል። ከእምነት አስተምሕሮ አንጻርም ኃጢያት ነው።

አሁን ባለው ሁኔታ ሁሉም የሚጠበቅበትን እያደረገ ነው? ብለን ስንጠይቅ ደግሞ መልሱ አስደሳች አይሆንም። ምንም አይነት ልማት ሊመጣ የሚችለው ገንዘብ ከሰማይ ወርዶ አይደለም፤ በመሥራት ነው። ሥራን ሳይንቁ፣ ጊዜ ሳይቆጭቡ፣ ገንዘብ ገንዘብ ሳይሉ ነው። በተሰማሩበት ሙያና ኃላፊነት በታማኝነት በመሥራት ነው።

የንግዱ ማኀበረሰብን ልክ እንደ መንግሥት ሠራተኛው የሚጠበቅባቸውን ግብር ሳይደብቁና ሳይሰውሩ ሲከፍሉ ነው። በየመንግሥት መሥሪያ ቤቱ በግዢ፣ በግንባታና በሌሎች ምክንያት የሚባክን እና የሚሰረቅ ገንዘብ ለተገቢው አገልግሎት ማዋል ሲቻል ነው። እስካሁን የሚታዩት ነገሮች ከዚህ በብዙ የራቁ ናቸው።

በሠራተኞች በብዛት የሚፈለጉ የሥራ መደቦች አሉ። ለምን ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። በተማሪዎች የሚመረጡ የትምህርት ዘርፎች አሉ፤ የእጅ መንሻ የሚያስገኙ፣ ባለጉዳይ የሚበዛባቸው (ቢዝነስ ያለው)። የተማሪውም ሆነ የወላጅ ምርጫ መሆን ያለበት ተማሪው የተሻለ ዝንባሌ ባለበት የትምህርት መስክ ላይ እንዲሠማራ ግፊት መደረግ ነው።

> **ማ**ንም ሰው ሲኖር የሚችለው በአንድ አይነት መንገድ አይሆንም፤ የሁሉም የሀብት መጠን ይለያያል። ሁሉም መክፈል ያለበት ግብር በእዛው መንገድ ይሆናል። ሁሉም መክፈል ያለበት ታክስ፤ ቫት የሰበሰበውም የንግድ ማኅበረሰብ የሰበሰበውን በሐቀኝነት ወደ መንግሥት ካዝና ማስገባት አለበት

ለሀገሩ በሙያው የተሻለ ሥራ መሥራት የሚችለውም በዝንባሌው ሲማር መሆኑን ማወቅ ይገባል። ይሄ ደግሞ ኮትኩቶ ከሚያሳድግ ቤተሰብ፣ ከሚያስተምር መምህር እና ከማኅበረሰቡ የሚጠበቅ ነው። ተማሪዎች ነጭ ወረቀቶች ናቸው። በአብዛኛው መምህራን በቀረጿቸው ልክ ነው የሚበቅሉት። ስለዚህ መምህራን ብቁና ንቁ ተማሪዎችን ለሀገር ማበርከት አለባቸው፤ በሥነምግባር የተቀረጹ ዜጎችን ማፍራት ይጠበቅባቸዋል።

አገልግሎት ፈልገን በምንገባባቸው የመዝናኛ ስፍራ፣ ምግብና መጠጥ ቤቶችም ሆነ ሌሎች የገበያ ቦታ "ደረሰኝ ሳይቀበሉ ሂሳብ አይክፈሉ" የሚል ማስታወቂያ አለ ። ይሄ ሕጋዊ የሆነ ግብይት እና አገልግሎት ማግኘትን ማረጋገጫ ነው። ምን ያህል ለዚህ ማስታወቂያ እራሳችንን ያስገዛን ነን?።

እኛም ደረሰኝ መቀበል መብታችን ቢሆንም ጠይቆ የመቀበል ልምድ የለንም ወይም ቸልተኛ ነን። አገልግሎት ሰጪውም ሂሳቡ ሲከፈለው ደረሰኝ መቁረጥ አይፈልግም። ከተገልጋዩ የሚሰበስበውን የመንግሥት ቫት እንኳን በአግባቡ ገቢ ለማድረግ ፈቃደኛ አይደለም።

አብዛኛው የንግዱ ኅብረተሰብ ከመንግሥት ጋር አይጥና ድመት የሚጫወት ነው። አንዴ ገቢ በመቀነስና በመሰወር፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሰበሰበውን ታክስ ገቢ ባለማድረግ እየተጋለጠ የአደባባይ ምስጢር ነው። ለመንግሥትም ትልቅ እራስ ምታት የሆነ ማኅበራዊ ችግር ነው። የታማኝነት ችግር በንግዱ ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን በደመወዝ በተቀጠረው የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሠራተኞች ላይ የሚስተዋል ነው ።

ይሄ ደግሞ የትም አያደርስም፤ እድገትንም አያመጣም። የተሻለች ሀገር ፈጥረን ለትውልድ ለማስተላለፍ የምንችልበትን ዕድል የሚያበላሽ ነው። ከዚህ ሀገራዊ ችግር ለዘለቄታው ለመውጣት ሁሉም በተሠማራበት የሥራ መስክ ኃላፊነቱን በአግባቡ ሊወጣ ይገባል፤ ይህን ማድረግ ስንችል ብቻ ነው የበለፀገች ሀገር መፍጠር የምንችለው። ቸር እንሰንብት !

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# "ዘንድሮ በክልሉ ሕገወጥ ዝውውርን ለመቆጣጠር እስከ ቀበሌ ኮሚቴ ተዋቅሮ ይሰራል"

*- አቶ አራርሶ ቢቂላ*
*የኦሮሚያ ክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ*

**አመለወርቅ ከበደ**

የዛሬው የወቅታዊ እንግዳችን የኦሮሚያ ክልል ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ አቶ አራርሶ ቢቂላ ናቸው። በክልሉ ሕገወጥ የሰዎች ዝውውርን የመከላከል ስራ ምን ላይ ይገኛል? የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ጋር ተያይዞ ምን ተሰርቷል? የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም እንዴት ነበር? በተያዘው በጀት ዓመት ምን ለመስራት ታቅዷል? በሚሉ እና ሌሎች ቢሮው በሚያከናውናቸው ተግባራት ላይ ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።

**አዲስ ዘመን፡- የቢሮው ዋና ዋና ኃላፊነቶች ምንድናቸው?**

**አቶ አራርሶ፡-** እንደሚታወቀው ቢሮው በሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ላይ፣ በስራ እድል ፈጠራ እና በውጭ ሀገራት የስራ ስምሪት ላይ ይሰራል። በማሕበራዊ ጥበቃ ከአረጋውያን እና አካል ጉዳተኞች ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይም ስራዎችን ያከናውናል። በተጨማሪም ኢንዱስትሪ ግንኙነት እና ሰላም ላይ የተለያየ ተግባራትን ያከናውናል።

**አዲስ ዘመን፡- በክልሉ ሕገወጥ ስደትን ለመቀነስ ምን አይነት ስራ እየተሰራ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር በ2016 በጀት ዓመት ከክልል እስከ ወረዳ ኮሚቴ በማቋቋም ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ተሰርቷል። ከጎረቤት ክልሎች ጋር ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ ከሶማሌ ክልል እና ከሌሎች ክልሎች ጋር በቅንጅት እየሰራን ነው።

ይህ ጉዳይ ተቀናጅቶ መስራት የሚጠይቅ ነው። በተለይም ሀገር ውስጥ ያሉ ደላሎች እስከ ጎረቤት ሀገራት ድረስ በመሄድ መዋቅራቸውን እየዘረጉ ነው። ይህን መዋቅር ለመከታተል ከጸጥታ አካላት ጋር መስራት አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት እየሰራን ነው። ባለፈው ዓመት የተዋቀረው ኮሚቴ እስከ ወረዳ ነበር፤ በ2017 በጀት ዓመት እስከ ቀበሌ በማድረስ ወጣቶች ላይ ለመስራት እቅድ ተይዟል።

ሕገወጥ ስደትን ለመቆጣጠር መፍትሄ የሚሆነው የመጀመሪያው ለወጣቶች የስራ እድል መፍጠር ነው። ሁለተኛው በሕጋዊ መንገድ አስፈላጊው መረጃ ተሟልቶላቸው እንዲሄዱ ማድረግ ነው። ሕገወጥ ዝውውሩን ለመቆጣጠር ድንበር መዝጋት አይቻልም።

እንደ ክልል ችግሩን ለመቆጣጠር እንዲያስችል ለወጣቶች ግንዛቤ መፍጠር፣ በሀገር ውስጥ የስራ እድል መፍጠር እና በሕጋዊ መንገድ የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት እንዲያገኙ ለማድረግ ከባለፈው ዓመት በበለጠ መልኩ ለመስራት እቅድ ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- በአካባቢው ለሕገወጥ ስደት መንስኤ የሆኑ ጉዳዮች ምንድን ናቸው? በክልሉ ችግሩ የሚበዛው የት የት አካባቢ ነው?**


**አቶ አራርሶ፡-** ወጣቶች ውጭ ሀገር በመሄድ በቀላሉ ስራ ይገኛል የሚል የተሳሳተ ግንዛቤ አላቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ግንዛቤ የመፍጠር ስራ እየተሰራ ነው።

በኦሮሚያ ክልል የት አካባቢ ነው ችግሩ የሚበዛው የሚለውን ስንመለከት፤ ከዚህ በፊት ኦሮሚያ ውስጥ ስድስት ዞኖች የነበሩ ሲሆን፣ አሁን ወደ ስምንት ከፍ ብለዋል። ችግሩ በሁሉም ዞኖች አለ። ነገር ግን ጅማ፣ በሁለቱ ሐረርጌ እና አርሲ ዞኖች ከፍ ይላል።

በ2016 በጀት ዓመት የተሻለ ስራ በመሰራቱ ችግሩ እየቀነሰ መጥቷል። የተሻለ ነገር ቢኖርም አሁንም መስራት ያስፈልጋል። ወጣቶች ግንዛቤ አግኝተው በሀገር ወስጥ ስራ እንዲያገኙ ማድረግ ዋናው ነገር ነው። ሁለተኛው በሕጋዊ መንገድ እንዲሄዱ ማድረግ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ከሁሉም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር እስከ ፌደራል ድረስ ቅንጅት ያስፈልጋል።

**እዲስ ዘመን፡- በክልሉ የስራ እድል ፈጠራ እና በውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ምን አይነት ስራ ተሰርቷል? የተገኘው ውጤትስ ምን ይመስላል?**

**አቶ አራርሶ፡-** የስራ እድል ከመፍጠር አኳያ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል። የኢሉአባቦራ ዞን ብቻ ብንወስድ ከ250 ሺ. በላይ ወጣቶች ተደራጅተው በግብርና ስራ ተሰማርተው እየሰሩ ነው። በባሌ በኩልም እንደዚሁ በግብርና ተሰማርተው እየሰሩ ያሉ አሉ።



በግብርና የተደራጁ ወጣቶች የተሰማሩት በተለያየ የግብርና ስራ ላይ ነው። በሩዝ፣ በሻይ ፣ በቡና በአትክልትና ፍራፍሬ እና በመሳሰሉት ላይ ነው።

በኢንዱስትሪ ዘርፍም ባለፈው በጀት ዓመት አራት ሺ 65 ወጣቶች በሸገር ከተማ በስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል። በተመሳሳይ በቢሾፍቱ ከተማ አንድ ሺ 600 የሚሆኑ ወጣቶች ስራ አግኝተዋል። በአጠቃላይ በክልሉ በሀገር ወስጥ ስራ እንደሚገኝ በማመን በግብርና፣ በኢንዱስትሪ እና በግንባታ ስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

ሌላው የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት በተመለከተ ባለፈው ዓመት በርካታ ሰዎች እንዲሄዱ ተደርጓል። በ2017 ዓ.ም በርካታ ወጣቶችን ለመላክ ጥረት እየተደረገ ነው። ከባለፈው የተሻለ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በግብርና የተሰማሩ ወጣቶች የሚሰሩት ማሳ ተሰጥቷቸው ነው ወይስ ከአልሚዎች ዘንድ ተቀጥረው ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** አንዳንድ ቦታ ላይ ወጣቶቹ ተደራጅተው መሬት ይሰጣል። ጅማ ላይ የተደረገው እንደዚያ ነው። ግብርና ሲባል ከብት እርባታ፣ ዶሮ እርባታ እና ሌሎች የአርብቶ አደር ስራዎችን ስለሚያካትት በእነዚህ ዘርፎች የተሰማሩም አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- በኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩት ምን ላይ እየሰሩ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ፋብሪካዎቹ በዚህ ዘርፍ የወሰዱት ፊዚክስ፣ ኬሚስትሪ እና ባዮሎጂ የተማሩ ተማሪዎችን ነው። ወጣቶች ትምህርት ተምረው ከተመረቁ በኋላ ቀበሌ ውስጥ ዝም ብለው ያለ ስራ ይቀመጣሉ። ይህን ነገር ከቢሾፍቱ እና ሸገር ከተማ ጋር ተወያይተን፤ ኮሚቴ አቋቁመን በስራ እንዲሰማሩ ተደርጓል።

እነዚህ ወጣቶች ስራ አጥተው ቁጭ የሚሉ ከሆነ በኋላ ለሕገውጥ ዝውውር ይዳረጋሉ። ችግሩ እንዳይፈጠር ቀድሞ በከተማ ደረጃ በመወያየት መፍትሄ ለማስቀመት ተፈልጎ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የስራ እድል የተፈጠረላቸው ከዩኒቨርሲቲ ለተመረቁ ብቻ ነው? ዝቅተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸውንም ያካትታል?**

**አቶ አራርሶ፡-** የስራ እድሉ የተፈጠረው ከ10ኛ እና 12ኛ ክፍል ትምህርት ያቋረጡ እና ላልተማሩም ጭምር ነው። እነዚህ በስፋት ነው የስራ እድል ያገኙት በግብርና እና በግንባታ ስራ ላይ ነው። በ2016 ዓ.ም 'አፍሪካ ሆልዲንግ' ከሚባል ግብረ ሰናይ ድርጅት ጋር በመተባበር ከክልሉ ከተለያዩ ዞኖች 24 ሴቶችን ለአምስት ወራት በማሰልጠን በድርጅቱ በኩል ስራ አግኝተዋል።

ከስራ ፈጠራ ጋር ተያይዞ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች ጋር ምን ማድረግ እንዳለብን ተወያይተን በጋራ እንሰራለን። የአፍሪካ ሆልዲንግ ግሩፕ በቀጣይም አብሮን ለመስራት እቅድ አለው። ስለዚህም በ2017 በጀት ዓመት በጋራ እንሰራለን ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስራ አጦቹን የምታደራጁት እራሳቸው መጥተው ሲያመለክቱ ነው? ወይስ ወጣቶቹ ዘንድ ለመድረስ የራሳችሁ አሰራር አለ?**

**አቶ አራርሶ፡-** በተለያዩ የስራ ዘርፎች እንዲሰማሩ የሚደረጉት ወደ ወጣቶቹ ለመድረስ የራሳችን መዋቅር ስላለን በዛ መዋቅር በኩል ነው። እነሱ ብቻ በሚያመለክቱት አይደለም። በተለይ በግንባታ ስራ ላይ የሚደረገው እንደዚያ ነው፤ ሰው ፍላጎት ኖሮት ከተደራጀ ስራ አያጣም።

**አዲስ ዘመን፡- የውጭ ሀገር የስራ ስምሪት በተመለከተ ምን አይነት ስራ ተሰርቷል? በተሰሩ ስራዎች ምን አይነት ለውጥ ተስተውሏል?**

**አቶ አራርሶ፡-** አሁን ላይ ያለው ለውጥ የተሻለ የሚባል ነው። ከዚህ በፊት ከፓስፖርት ጋር ተያይዞ ችግር ነበር፤ በኤጀንሲዎች እና በወጣቶች መሀከል ያለው ትስስር ጥሩ አልነበረም። ያለውን ችግር ለመፍታት ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በመወያየት በኦንላይ እንዲሆን ተደርጓል። ስለዚህ አሁን ላይ ሂደቱ አይዘገይም።

ከዚህ በፊት ማስረጃዎችን ለማሟላት ከፍተኛ ችግር ነበር። አሁንም ችግሮች ቢኖሩም ከበፊቱ አንጻር ችግሩ የቀነሰበት ሁኔታ ነው ያለው። በዘንድሮ በጀት ዓመት ጠንክረን በመስራት የተሻለ ውጤት ለማምጣት ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር እየተወያየን ነው።

የስራ ስምሪቱ ከ2015 ዓ.ም ይልቅ በ2016 የተሻለ ነው። ከዚህ የበለጠ ውጤት በዘንድሮ ዓመት እንዴት ማምጣት አለብን በሚሉ ጉዳዮች ላይ ተወያይተን ስምምነት ላይ ደርሰናል። ከሀገራችን ስፋትና ከሕዝቡ ብዛት አንጻር ስንመለከት አሁንም ብዙ መስራት ይጠበቅብናል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2016 በጀት ዓመት በውጭ ሀገር የስራ ስምሪት ምን ያህል ሰዎች ላካችሁ? ለስራ የሚላኩትስ ስልጠናቸው ምን ምን ያካተተ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** እንደ ኦሮሚያ ክልል የላክነው ከ295 ሺ. በላይ ወጣቶችን ነው። ስልጠና ይሰጣል። በተለይ ወደ መካከለኛው ምስራቅ፤ ዮርዳኖስ፣ ሳዑዲ አረቢያ በአብዛኛው የሚሄዱት ሴቶች ናቸው። ለእነዚህ ሴቶች ስልጠናው የሚሰጣቸው ከቤት አያያዝ እና ከቤት ውስጥ ስራዎች ጋር ተያይዞ ነው።

በክልሉ ወደ ውጭ ሀገር ለስራ ለሚሄዱ ወጣቶች ስልጠና የሚሰጡ አምስት ኮሌጆች አሉ ። በኮሌጆቹ ብዙ ስራ እየተሰራ ነው፤ ከዚህ በፊት ስልጠና ወስደው የሄዱ አሉ። አሁንም ስልጠና እየወሰዱ የሚገኙ ሰልጣኞች አሉ። ስልጠናው ሁሌም ቀጣይነት ያለው ነው።

ስልጠናውን ከዚህ በፊት ውጭ ሀገራት ቆይተው የሚመጡም ይሰለጥናሉ። ነባሮቹ ልምድ ያላቸው ስለሆነ ለእነሱ የሚሰጠው ስልጠና እና አዲስ ለሚሄዱት የሚሰጠው የስልጠና አይነት የተለያየ ነው። ለሶስት ወር፣ ለአንድ ወር እና ለ15 ቀናት የሚወስዱ አሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ለስራ ከሄዱ በኋላ ስለ ደህንነታቸው እና ከገንዘብ ጋር ተያይዞ ባሉ ጉዳዮች የሚደረገው ክትትል ምን ይመስላል?**

**አቶ አራርሶ፡-** ስራዎች የሚሰሩት በኤጀንሲዎች በኩል ነው። ዜጎች ከሄዱ በኋላ የት እንደተቀጠሩ፣ የገንዘብ ሁኔታ እና ጥቃት እንዳይደርስባቸው በየ ሀገሩ ባሉት ኤምባሲዎች በኩል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ክትትል ያደርጋል እኛም ክትትል እናደርጋለን።

**አዲስ ዘመን፡- በስራ ስምሪት ሂደቱ የተወሰኑ ችግሮች መኖራቸውን ገልጸውልኛል፤ እነዚህ ችግሮች ምንድን ናቸው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ያለው ችግር ፓስፖርት ከማግኘት ጋር የተያያዘ ነው። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ቶሎ የማግኘት ሁኔታ አለ። አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ የመዘግየት ሁኔታ አለ። ለዚህ ደግሞ ወጣቶቹ መመላለስ ግድ ይላቸዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ ቦታዎች ላይ ሲዘገይ የቻለበት ምክንያት ምንድነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** እንደሚታወቀው ሀገራችን ሰፊ ናት። ፓስፖርት የሚሰጠው በፌደራል ደረጃ አዲስ አበባ ከተማ ነው። ነገር ግን ሰዎቹ የሚመጡት ከዞን ስለሆነ ርቀት አለ። በአንዴ ሲመጡ ፓስፖርት ለማግኘት ከአንድ ሳምንት እስከ አንድ ወር የሚቆዩ አሉ። ያለውን ክፍተት እንዴት መሙላት እንደሚቻል ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር ውይይት እያደረግን ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ የፓስፖርት ምዝገባ በኦንላይ ነው። ሰራተኞቹ ወደ አዲስ አባባ መምጣት የሚጠበቅባቸው ለጤና ምርመራ ብቻ እንደሆነ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ሲገልጽ ነበር። የሚቆዩት**

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ዘንድሮ በክልሉ ሕገወጥ ዝውውርን ለመቆጣጠር...

ከገጽ 6 የዞረ



**የቴክኖሎጂ ተደራሽነት ያስመሆን ችግር ነው? ወይስ ከምን አንጻር ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** በኦንላይን የሚለቀቀው አጠቃላይ ማስረጃቸው ከተሟላ በኋላ ለስራ ስምሪቱ የተመረጡ ሰዎች ስም ነው። ከፓስፖርት ጋር ተያይዞ የሚጠይቁት በአካል ቢሮ ሄደው ነው። የኦንላይን ስራው ገና ጅማሬ ላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ለፓስፖርት የሚመዘገቡት አዲስ አበባ ሄደው ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** አዎ!

**አዲስ ዘመን፡- ፓስፖርት ለማግኘት በኦንላይ ምዝገባ ተደርጎ፤ ቀነ ቀጠሮ ይሰጣል። አንድ ሰው በዚያ መሰረት ነው የሚሄደው፤ ይህ ነገር ተደራሽ አልሆነም?**

**አቶ አራርሶ፡-** የስራ ስምሪትን በተመለከተ የኦንላይ ምዝገባው አሁን ጅማሮ ላይ ነው። ከዚህ በፊት ኤጀንሲዎች እስከ ዞን ነው ያሉት። አሁን ኤጀንሲዎቹ ተመልሰው ሁሉም ነገር አዲስ አበባ ብቻ ሆነ። ለስራ የሚሄዱት ሁሉንም ማስረጃ አሟልተው ካጠናቀቁ በኋላ በኦንላይን የሚለቀቀው። ይህን ያህል ሰው ከኦሮሚያ ክልል፣ ከዚህ ዞን እና ከተማ የሚል ዝርዝር በኦንላይን ይለቀቃል።

**አዲስ ዘመን፡- ለምንድን ነው ኤጀንሲዎቹ ከዞን ተነስተው አዲስ አበባ ብቻ እንዲሆኑ የተደረገው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ስራና ክህሎት ሚኒስቴር ብቻ ነው የሚያውቀው፤ እኛ ከዚህ በፊት ዞን የነበሩት ወደ አዲስ አበባ መመለሳቸውን እንጂ፤ በምን ምክንያት እንደሆነ አላወቅንም።

በ2014 ዓ.ም ችግር ባለበት አካባቢ ኤጀንሲዎቹ መሆን እንዳለባቸው በመነጋገር፤ እንደዛ እንዲሆን ተደርጎ ነበር። በዛ መሰረት ከፌደራል ፈቃድ አግኝተው ወደ እኛ ይመጣሉ፤ እኛ ደግሞ ወደ ዞን እንመድባቸዋለን። ለምሳሌ ከዚህ በፊት ቢሾፍቱ፤ አዳማ፤ ነቀምት እና ሻሸመኔ ላይ ነበር።

አሁን ሁሉም ነገር ኦንላይን ስላደረጉት አዲስ አበባ እንዲሆን ተደርጓል። ይህ ነገር ለስራ ጥሩ ነው፤ ግን ችግር ያለበት ቦታ ኢጀንሲዎቹ ካሉ አዲስ አበባ ሳይሄዱ እዛው ችግሩ ይፈታል። እንደ ቢሮ እንደዛ ነው የምናስበው። ሀሳባችን እንደዛ መሆኑን ለስራና ክህሎት ሚኒስቴር አሳውቀን እየተወያዩበት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ምን ምላሽ ተሰጠ?**

**አቶ አራርሶ፡-** ገና እየጠበቅን ነው። ኤጀንሲዎቹ እስከ ዞን ወይም ወረዳ ድረስ መምጣት አለባቸው እንጂ ወጣቶቹ አዲስ አበባ እንዲመላለሱ ማድረግ እና አንድ ቀን አዲስ አበባ ከተማ ማደር በጣም ከባድ ነው። እስከ ወረዳ ካልተቻለ እስከ ዞን ድረስ እንኳን ቢሆን ለወጣቶቻችን መፍትሄ ይሰጣል ብለን እናምናለን።

ዞን ላይ ቢሮ ከከፈትን በኋላ እንደገና ዘግተን ወደ አዲስ አበባ ተመልሰናል። ይሄ ነገር እንዴት ነው እያሉ እየጠየቁ ነው የሚል ጥያቄ ከኤጀንሲዎቹ በኩል እየተነሳ ነው። ይሄ ነገር መፍትሄ እንደሚያስፈልገው ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር እየተወያየን ነው። መፍትሄ ይገኛል ብለን እናምናለን።

**አዲስ ዘመን፡- ለስራ የሚሄዱ ዜጎች መጀመሪያ አዲስ አበባ የሚሄዱት በእናንተ በኩል ተመዝግበው ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** እኛ ከኤጀንሲዎች ጋር ተነጋግረን ለወጣቶች የሚያስፈልገው ስልጠና በኮሌጆች ይሰጣል። ከዛ በኋላ ኤጀንሲዎቹ ከስራና ክህሎት ሚኒስቴር እና ከኢሚግሬሽን ጋር ተነጋግረው ወጣቶቹ እንዲሄዱ ይደረጋል። አስተባባሪ ስላለን የሚሄዱትን መረጃ በዛ በኩል እናገኛለን። ከዚህ በፊት የነበረው አሰራር እንደዛ ነበር። አሁን በኦንላይን ስለተደረገ እኛ ሳናውቅ ነው የሚሄዱት።

**አዲስ ዘመን፡- ፓስፖርት የሚያወጡት ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** በፊት የነበረው ዞን ላይ በኤጀንሲዎች በኩል ምዝገባ ጨርሰው፤ ፓስፖርት ይጨርሳሉ። ከጨረሱ በኋላ በኮሌጅ ደረጃ አስፈላጊው ማብራሪያ ተሰጥቷቸው ይሄዳሉ። ፓስፖርቱን ከዛ በኋላ ነው የሚያገኙት። አሁን የተለወጠው እሱ ነው።

**አዲስ ዘመን ፡- በ2016 በጀት ዓመት ለምን ያህል ወጣቶች የስራ እድል ተፈጠረ?**

**አቶ አራርሶ፡-** በኢንዱስትሪ ላይ በሸገር ከተማ አራት ሺ 65 የስራ እድል ተፈጥሯል፤ አንድ ሺ 65 የተፈጠረው ደግሞ ቢሾፍቱ ከተማ ላይ ነው። ጠቅላላ በኢንዱስትሪ አካባቢ አምስት ሺ አካባቢ የስራ እድል ተፈጥሯል። በግብርና ዘርፍ በከብት እርባታ፣ በዶሮ እርባታ፣ በሩዝ ምርት፣ በሻይ ቅጠል ስራ እና በሌሎች የግብርና ስራ አጠቃላይ እንደ ኦሮሚያ ክልል 350 ሺ የሚሆን የስራ እድል ተፈጥሯል።

> **አሁንም አልፎ አልፎ በምስራቅ በኩልና በሞያሌ በኩል ሰው ይወጣል። ይህን ነገር በአንዴ ማቆም አይቻልም። ችግሩን ለመፍታት ከሕግና ከጸጥታ አካላት ጋር እየሰራን ነው**

**አዲስ ዘመን፡- ከአረጋውያን ጋር ተያይዞ ምን እየተሰራ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ከአረጋውያን አያያዝ ጋር ተያይዞ ብዙ ስራ ሰርተናል። በቢሾፍቱ ከተማ ከ200 በላይ አረጋውያን በቀን ምሳ እንዲያገኙ ተደርጓል። ሌላው በቢሾፍቱ አረጋውያንን ተጠቃሚ የሚያደርግ ማእከል ከዚህ በፊት የተሰራ ነበር አሁን ደግሞ ተጨማሪ ተሰርቷል።

**አዲስ ዘመን፡- ማእከሉ ምን አይነት ጥቅም የሚሰጥ ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ማእከሉ አረጋውያን ያላቸውን የሕይወት ልምድ ለወጣቶች እንዲያካፍሉ እና ለራሳቸውም ገቢ እንዲያገኙ እንደ "ካፍቴሪያ" አይነት ነገር ነው። ተሰርቶ ተጠናቋል፤ ግን ወደ ስራ አልገባም። ወደፊት እሱን ማስፋፋት አለብን ብለን እንደ ክልል እቅድ ይዘናል።

በዚህ ሁኔታ ገቢ ያገኛሉ፤ ጧሪ ቀባሪ የሌላቸውን አረጋውያን ማህበሩ ተጠቃሚ ያደርጋል። እራሳቸውን ችለው እንደማህበር ይንቀሳቀሳሉ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ማእከሉን በሌሎች ክልሎች የማስፋፋት እንቅስቃሴው ምን ይመስላል?**

**አቶ አራርሶ፡-** ሸገር ከተማ ላይ ለገጣፎ ለገዳዲ እየተሰራ ነው። የግንባታው ሂደት 75 ከመቶ ደርሷል። ለሌላው አርሲ፣ ሰሜን ሸዋ እና ቦቆጂ ከተማ ላይ መሬት አግኝተን እየሰራን ነው የሚገኘው። ማእከሉን ለማስፋፋት በዘንድሮ ዓመት እቅድ ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- ማእከሉ ምን ምን ያሟላ ነው? ስራውን ለመስራትስ ያነሳሳችሁ ምክንያት ምንድን ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** ቤተ መጻህፍት አለው፤ ለተለያዩ ዝግጅቶች አከራይተው እንዲጠቀሙ አዳራሽም ያለው ሲሆን፣ አልፎ አልፎ ሌሎች ገቢ ማግኛ ስራዎችም ይሰራሉ ማለት ነው።

ይህን ለማድረግ ያነሳሳን ሁልጊዜ አቅመ ደካሞችን ለመርዳት ግብረ ሰናይ ድርጅቶችን ከመለመን በእንደዚህ አይነት መልኩ መስራት አለብን በሚል ነው፤ የጀመርነው ኮሚቴ አቋቁመን ነው። የተጀመረው በ2013 ዓ.ም ሲሆን፣ አሁንም የሚቀጥል ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የአቅመ ደካሞችን ቤት ከመገንባት ረገድ ምን ተሰርቷል?**

**አቶ አራርሶ፡-** አቅም የሌላቸው አረጋውያንን ቤት ማደስና መስራት በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት የተገነባው ከ68 ሺ በላይ ነው።

እንደ ኦሮሚያ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ከ28 ሺ በላይ ቤት ተገንብቷል። ነገር ግን አጠቃላይ እንደክልል የተገነቡና የታደሱ ቤቶች ቁጥር ከ68 ሺ በላይ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የቤት ግንባታው የተገነባው ከየት በተገኘ ገንዘብ ነው? እነማን ናቸው የተሳተፉት?**

**አቶ አራርሶ፡-** ግንባታው የተደረገው በሕብረተሰብ ተሳትፎ ነው። እንደ ቢሮ ከቀበሌ እስከ ክልል የተደራጀ አፎሻ ወይም እድር አለ። ከዚህ በፊት ከወረዳ እስከ ቀበሌ ብቻ ነበር የእድር አደረጃጀቱ፤ አሁን እስከ ክልል ሊደርስ ችሏል። በዛ እድር ገንዘብ ይቆጥባሉ፤ ከዛ ደግሞ ለአቅመ ደካሞች የቤት እድሳት ያደርጋሉ።

**አዲስ ዘመን፡- ቢሮው በ2017 በጀት ዓመት ምን ምን ተግባራትን ለማከናወን እቅድ ይዟል?**

**አቶ አራርሶ፡-** ሕገ ወጥ ዝውውርን ለመከላከል ባለፈው በጀት ዓመት ከክልል እስከ ወረዳ ነው ኮሚቴ ያቋቋምነው። ዘንድሮ በክልሉ ሕገወጥ ዝውውርን ለመቆጣጠር እስከ ቀበሌ ኮሚቴ ተዋቅሮ ይሰራል። ወጣቶች ሀገር ውስጥ ስራ እንዲያገኙ እና በሕጋዊ መንገድ እንዲሄዱ በቋሚነት ለመስራት አቅደናል።

ሌላው በኢንዱስትሪ ግንኙነት እና ከሰላም ጋር ተያይዞ ነው። እንደ ሀገር ዝቅተኛ የክፍያ ጣራ የለም። ምርታማነትን ለመጨመር አሰሪና ሰራተኛ ተስማምተው መስራት ይኖርባቸዋል። አሰሪው ሰራተኛውን እንደቤተሰብ ማየትና አስፈላጊውን የደህንነት እቃዎች ማሟላት አለበት። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ከኢንዱስሪዎች ጋር በየጊዜው ውይይት እናደርጋለን። በተያዘው ዓመትም አጠናክረን እንቀጥላለን።

ባለፈው ዓመት በክልሉ 10 ኢንዱስትሪዎች ላይ ሰርተን ነበር። አሁን እሱን በማስፋፋት ወደ ተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ተደራሽ ለመሆን ነው። እሱን ወደ ሸገር እና አዳማ ከተማ አስፋፍተን በአሰሪ እና ሰራተኛ መሃል ያለውን ቅራኔ በውይይት መፍታት አለብን ብለን ይዘናል።

**አዲስ ዘመን፡- 10 ኢንዲስትሪዎች በምን ዘርፍ የተሰማሩ ናቸው? በኢንዱስትሪዎቹ የተሰራው ስራ ምንድን ነው?**

**አቶ አራርሶ፡-** የቆርቆሮ፣ የልብስ፣ የውሃ፣ የዱቄት፣ የዳቦን ጨምሮ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች ናቸው። በእነዚህ ኢንዱስትሪዎች የደመወዝ ጭማሪ በተመለከተ ብዙ ጊዜ የሚነሳ ጥያቄ አለ። በዚህ ጉዳይ ላይ ከፌደራል ዝቅተኛ የደመወዝ ክፍያ ከመጠበቅ እኛ እራሳችን ተወያይተን መፍትሄ ማምጣት አለብን ብለን ይዘናል። ባለፈው ዓመት አንዳንድ ቦታዎች ላይ ያለው ችግር ተፈትቷል።

**አዲስ ዘመን፡- በ2016 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ላይ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?**

**አቶ አራርሶ፡-** የደመወዝ ጥያቄ ነው፤ በሀገራችን ዝቅተኛ የደመወዝ ጣራ አልተወሰነም። በዚህ ምክንያት በአንድ ቦታ የተነሳው ጥያቄ መልስ ሲያገኝ በሌላ ቦታ ጥያቄ ይነሳል።

ሌላው ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር ነው። አሁንም አልፎ አልፎ በምስራቅ በኩልና በሞያሌ በኩል ሰው ይወጣል። ይህን ነገር በአንዴ ማቆም አይቻልም። ችግሩን ለመፍታት ከሕግና ከጸጥታ አካላት ጋር እየሰራን ነው። በክልሉ ያሉ ወጣቶች ብዙ ስለሆኑ አንዱ ስራ ሲያገኝ፣ አንዱ በሕጋዊ መንገድ የመሄድ እድሉን ሲያገኝ፤ አንዳንዱ የማያገኝበት ሁኔታ ስላለ፤ አልፎ አልፎ ይህ ችግር ይከሰታል።

**አዲስ ዘመን፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካልዎት?**

**አቶ አራርሶ፡-** ሕዝባችን ከተረጅነት መላቀቅ አለበት ብለን ማህበራዊ ጉዳይም ስለሚመለከተን እየሰራን ነው። ዜጋው ሁልጊዜ ሀገር ውስጥ ስራ ማግኘት ይቻላል ብሎ ማመን አለበት። ሰው በራሱ የሚተማመን ከሆነ ነገሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻሉ መጥተው ያቀዱትን ማሳካት ይቻላል።

ስለዚህ ወጣቶች በራሳቸው እንዲተማመኑ እና ወደ ውጭ ሀገራት ለመሄድ ከፈለጉም በሕጋዊ መንገድ መሄድ እንዳለባቸው መልዕክቴን አስተላልፋለሁ።

**አዲስ ዘመን፡-** ስለነበረን ቆይታ እናመሰግናለን፡፡

**አቶ አራርሶ፡-** እኔም አመሰግናለሁ

# በጎነት ያበሳቸው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የሚያስጨንቃቸው አንድ ነገር ነው። እሱም እሳቸውና ልጆቻቸው የሚኖሩበት ቤት ለመፍረስ ቋፍ ላይ በመድረሱ ነው። በዚች ቤታቸው ጣራ ላይ የወደቀው የተላላጠ የኤሌክትሪክ ገመድ እሳት እየፈጠረ ማስቸገሩና ዝናብ በጣለ ቁጥር ወደ ቤት የሚገባው ጎርፍም ሌላው የሚያስጨንቃቸውና እረፍት የነሳቸው ጉዳይ ነው።

ዛሬ አልያም ነገ ልጆቻችን ጎርፍ ይወስዳቸዋል፤ በቤቱ ጣራ ላይ የወደቀው የኤሌክትሪክ ገመዱ በንክኪ እሳት ፈጥሮ ይፈጃቸው ይሆን የሚለው ሀሳብ በሥራ የደከመ ሰውነታቸው በመኝታ ሳያርፍ ዓይናቸው በእንባ እንዲታጠብ አድርጎኝ ቆይቷል ይላሉ። ከሁሉም ቤት ውስጥ ወልዳ የተኛችና የአዕምሮ ዘገምተኛ የሆነች የ8ኛ ክፍል ተማሪ መኖራቸው ስጋታቸውን እጥፍ ድርብ ያደረገባቸው መሆኑን ነው የተናገሩት።

ቦንዳ ሸጠው የሚያገኙት ገቢ ስጋታቸውን መቅረፍ ስለማይችል ያለውን ነገር ተላምዶና ተቋቁሞ ከመኖር ውጭ ምንም አይነት አማራጭ አልነበራቸውም። ምርጫ በሌለው ሕይወት ውስጥ እየኖሩ ከቀኖች ሁሉ የተቀደሰች ቀን የተቀደሰ ዕድል አመጣችላቸው፤ የተቀደሰውን የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዕድልን፤ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መርሐ ግብር በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ቤታቸውን ፈርሶ አዲስ በተሠራላቸው፤ ከነበሩበት ስቃይና ሰቀቀን ወጥተው በደስታ እንዲኖሩ የሕይወት ዕድል ሚዛን ፈቀደችላቸው።

ወይዘሮ አዳነች አብቼ «በክረምት ወቅት ዝናብ ሲጥል ልጆቼን የማስተኛበት ቦታ እያጣሁ አለቅስ ነበር፤ ወደ ቤት የሚገባው ጎርፍ ልጆቼን ይወስድብኛል እያልኩ አስባለሁ፤ ንፋስ በነፈሰ ቁጥር ጣራው ላይ የወደቀው የኤሌክትሪክ ገመድ እሳት ፈጥሮ አንድ ቀን ያቃጥለናል፤ በተለይም ወልዳ የተኛችውና የአዕምሮ ዘገምተኛ የሆነችው ልጅ ይጎዱብኛል ብዬ ከአቅም በላይ እፈራለሁ፤ እጨነቃለሁ። ቤቴን እንዳላድሰው የማገኘው ገቢ ከዕለት ጉርሳችን የሚተርፍ አልነበረም»ይላሉ።

ቤቱ ከማርጀቱ የተነሳ አንድ ቀን ወድቆ በእኔና በልጆቼ ላይ ጉዳት ማድረሱ አይቀርም ነበር ሲሉ ጊዜውን ለማስታወስ በሚመስል ትውስታ አጫውተውናል።

«ለሰው ልጅ ትልቁ ሀብት ቤት ነው፤ ዛሬ አላህ ቆጥሮልኝ። የአዲስ ቤት ባለቤት ሆኛለሁ፤ ደስታዬ እጥፍ ድርብ ነው፤ የቤት ባለቤት በማድረግ ከነበርኩበት ሰቀቀን ያወጣኝን የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን፤ ባለሀብቶች በአጠቃላይ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ተሳትፈው ቤቴን የሠሩልኝ ሁሉ አመሰግናለሁ፤ ለእኔ እንደደረሱልኝ አቅም ለሌላቸው፤ ታመው ቤታቸው በላያቸው ላይ ለወደቀባቸው ይድረሱ» ሲሉ እናታዊ ምስጋናቸውን አስተላልፈዋል።

ተማሪ አያት ዘይኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪ ናት፤ የወይዘሮ አዳነች የአዕምሮ ዝግመት ያለባት ልጃቸው ናት። ተማሪ አያት «ዝናብ ሲጥል ቤታችን ያፈሳል፤ በፍሳሹ ምክንያት ትምህርቴን ለማጥናት እቸገር ነበር፤ ዛሬ ቤታችን ተሠርቶልናል፤ በጣም ደስተኛ ነኝ፤ በትምህርቴ በርትቼ ዶክተር በመሆን ዜጎችን ያለምንምን ክፍያ አገለግላለሁ።» የሚል ምኞቷን ገልጻልናለች።

ዛሬ ቤታችን ታድሶ ከመኖር የበለጠ በጎነት ምን ያህል ዋጋ እንዳለው አስተምሮኛል፤ የተደረገልን ርዳታ በጎነትን እያሰብኩ እንዳድግና ለወገኖች እንድደርስ ትልቅ ተነሳሽነት ፈጥሮብኛል ስትል ሐሴት በመላው ስሜት አውግታናለች።

በክረምት የበጎ ፍቃድ መርሐ ግብር አገልግሎት፤ የአቅመ ደካማዎችን ቤት በማደስና በመሥራት ኑሯቸውን የማሻሻል፤ የሰቆቃ ሕይወት እንባን የማበስ ሥራ እየተሠራ ይገኛል፤ በበጎ ፍቃድ መርሐ ግብር እየተሠራ ያለውም ሥራ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውን የዜጎችን ተጠቃሚ እያደረገ ነው።

አቶ ይማም ሳይድ ሌላኛው፤ በኮልፌ ቀራንዮ በወረዳ ዘጠኝ በፍሳሽ ቤት የአለጧሪና የአለቀባሪ የሚኖሩ አቅም ደካማ ናቸው፤ አብሯቸው የሚኖር ልጅም ሆነ የሥጋ ዘመድ የላቸውም፤ እንደ አቅማቸው ያገኙትን ሥራ በመሥራት የዕለት ጉርሳቸውን ለመሙላት የሚታትሩ አዛውንት ናቸው።

«የምሠራው ሥራ ከዕለት ጉርስ የሚያልፍ አልነበረም፤ ከዕለት ጉርስ የሚተርፍ ባለመሆኑም በላዬ ላይ ዝናብ እየወረደብኝ ለመኖር ተገድጃለሁ፤ በብርድና በስቃይ ዓመታትን ኖሬያለሁ፤ ዝናብ ሲጥል ግቢው ጭቃ ስለሚሆን እየወደኩ ጉዳት ይደርስብኝ ነበር፤ በክረምት በጎ ፍቃድ ደጋግ ወገኖቼ ቤቴን ሠርተውልኛል፤ ከክረምት ሰቀቀን፤ ከበጋ ፀሐይ ወጥቻለሁ፤ ለካስ የሚያስበን ወገን አለን፤ በበጎነት ላደረጉልኝ እርዳታ ፈጣሪ አብዝቶ ይክፈላቸው» ሲሉ ነግረውናል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ንቅናቄ ተፈጥሮ እየተሠራበት ያለው አቅመ ደካማዎችን ዝቅ ብሎ የማየት፤ የጎደላቸውን፤ የቸገራቸውን የመሙላት፤ ኑሯቸውን የማሻሻል ሥራ ይበል የሚያስብል ነው፤ ተጠናክሮ ይቀጥል ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ቤቴ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርትና ሥልጠና ጥራትና ቁጥጥር ባለሥልጣን ከመሠራቱ በፊት እያፈሰሰ ለልጆቿቸውም ሆነ ለእሳቸወ አስቸጋሪ እንደነበር አቶ ታዲዮስ ሰመረ ነግረውናል።

« በመካኒክ ሙያዬ የማገኘው ገቢ ከእኔና ከቤተሰቦች የዕለት ጉርስና ከልጆች የትምህርት ቤት ክፍያ የሚሻገር አይደለም፤ በዚህ ምክንያትም በክረምት ወቅት የሚያፈሰውን ቤቴን ማደስም ሆነ መሥራት አልቻልኩም። ያለኝ አማራጭ ዝናቡን ለማስቀም ሸራ ማልበስ፤ በቆርቆሮ በፕላስተር ጣራውን መጠገን ነው፤ እሱም ዘላቂ መፍትሔ አልነበረም፤ በሚያፈስና በእርጅና ሊወድቅ በአዘመመ ቤት መኖር ፈታኝ ነበር » ሲሉ አጫውተውናል።

የአዲስ አበባ ትምህርትና ሥልጠና ጥራት ቁጥጥር ባለሥልጣን ትውልድ በትምህርት ከማፍራት ባለፈ ሰው ተኮር ሥራ እየሠራ ነው፤ እየሠራ ባለውም ሰው ተኮር ሥራ ቤቴን አፍርሶ በአዲስ መልኩ ሠርቶልኛል፤ ከነበርኩበት የሰቀቀን ኖሮ ወጥቼ የተሻለ ኑሮ እየኖርኩ ነው ሲሉ ደስታቸውን አጋርተውናል።

በወጣትነት ዘመናቸው ጉልበታቸውን ሳይሰስቱ ሀገርን አገልግለው ችግር ያጋጠማቸውን፤ ጤና ክዷቸው የአልጋ ቁራኛ ያደረጋቸውን ዜጎች እንባ ለማበስ እየተሠራ ያለው ሥራ የበጎነት ፍቃድ አገልግሎት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች አስተያየታቸውን ሰጥተውናል።

# የድህረ ምርት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ረሃብን ለማጥፋት ምርታማነትን ከማሳደግ ጎን ለጎን የድህረ ምርት ብክነትን መከላከል አስፈላጊ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ መንግሥት እ.ኤ.አ ከ2023 ጀምሮ ሀገራዊ የድህረ ምርት አያያዥ ስትራቴጂ አዘጋጅቶ ሥራዎች እየሠራ ነው ብለዋል።

አርሶ አደሮች ምርታቸውን የሚያከማቹት በጉድጓድ ውስጥ በመሆኑ ከአስር ኩንታል ምርት ውስጥ እስከ አራት ኩንታል ይበላሻል። መንግሥት የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ የጥራት ልዩነት ሳይኖር አከማችቶ ማስቀመጥ የሚያስችሉ ተሻሽለው የመጡ ከረጢቶችንና የብረት ጎተራዎችን በማቅረብ ላይ ነው ሲሉ ጠቅሰዋል።

እንደ መለስ (ዶ/ር) ማብራሪያ፤ ካለፉት ስድስት ዓመታት ወዲህ በፖሊሲ፣ በአዋጆች፣ በመመሪያዎችና አጠቃላይ በማበረታቻ ሥራዎች ውስጥ በሚሠሩ ስትራቴጂዎች ውስጥ የድህረ ምርት ብክነት ለመቀነስ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራ ነው። ለአዝዕርት፤ ለአትክልትና ፍራፍሬ ሰብልና ለእንስሳት ተዋፅዖዎች ምን አይነት የምርት ማጓጓዣዎችና ማከማቻዎችን መጠቀም አለብን የሚለው ተለይቶ ወደ ሥራ ተገብቷል። በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ፤ ደቡብ ኢትዮጵያና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለአርሶ አደሩ የማስፋፋት ሥራ እየተሠራ ነው። በማኅበራት፣ በአነስተኛና መካከለኛ ኢንቨስተሮች ዘመናዊ የምርት ማከማቻ እየተጠቀሙ ነው። በዚህም ውጤት ማምጣት መቻሉን ገልጸዋል።

በአዝዕርት ሰብል ከ20 እስከ 30 በመቶ የምርት ብክነት አለ ያሉት መለስ (ዶ/ር)፤ ይህንን እኤአ በ2030 ወደ 10 በመቶ ዝቅ ለማድረግ እቅድ ተይዞ እየተሠራ ነው። በአትክልትና በሰብል በፍራፍሬ ምርቶችን ላይ ከ30 እስከ 50 በመቶ የሚሆን የምርት ብክነት አለ፤ ይህንን ብክነት በ2030 በግማሽ የመቀነስ እቅድ አለ። በአጠቃላይ እኤአ በ2050 የድህረ ምርት ብክነትን አምስት በመቶ በታች የማድረስ ሥራ ሀገራዊ እስትራቴጂክ እቅድ ተነድፎ እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ በዓመት ከ12 ሚሊዮን ቶን በላይ የድህረ ምርት ብክነት አለ ያሉት ሚኒስትር ዴዔታው፤ ብክነት የሚደርሰው ከምርት ስብሰባ ጀምሮ እስከ መጠቀም ባለው ሂደት ውስጥ ነው። በኢትዮጵያ በየዓመቱ የሚባክነው ምርት 46 ሚሊዮን ዜጋ መመገብ የሚያስችል ነው ብለዋል።

በሀገር ደረጃ 22 ሚሊዮን ዜጎች የምግብ ዋስትና አልተረጋገጠላቸውም። ከስምንት እስከ 10 ሚሊዮን የሚደርሱ ዜጎች ደግሞ የእለት ቀለብ እርዳታ ተሰፍሮ የሚሰጣቸው አሉ። ይህን ችግር ለመፍታትም ምርታማነትን ከማሳደግ ጎን ለጎን የምርት ብክነትን በመከላከል ረገድ እየተሠራ ያለው ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አመልክተዋል ።

# 297 ሚሊዮን ብር እና 151 ሚሊዮን ዶላር ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

86 ተሽከርካሪዎች፣ ሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን የሚያወጣ የአክሲዮን ብር ዋጋ ያለው፣ 81 ሺህ ገደማ ካሬ የመሬት ይዞታዎች እግድ እንደወጣባቸው ተመልክቷል።

ከፎረሙ አባላት መካከል የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትር ዴኤታ እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር) የሕዝብ ሀብት በአግባቡ ለታለመለት ዓላማ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ ኅብረተሰቡም የሚፈልገውን አገልግሎት በሚፈለገው ደረጃ እየተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ ትግበራው የሚበረታታ መሆኑን አመልክተዋል።

ሪፖርቱ አበረታች ጅማሬዎች መኖራቸውን አመላካች በመሆኑ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባም አመልክተዋል። ባለፉት ሦስት ዓመታት በፎረሙ የተከናወኑ ተግባራት የተያዘውን እቅድ ለማከናወን የሚያግዝ መሆኑን ማሳየቱንም አመልክተዋል። በቀጣይም ኅብረተሰቡ በሚጠይቀው መልኩ ሀብት ሳይባክን ለማስኬድ ከዚህ የበለጠ ተግባር ማከናወን ይገባልም ብለዋል።

የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ተስፋዬ ዳባ በበኩላቸው ምክር ቤቱ ከተሰጠው ሥልጣን ውስጥ የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ አንዱ መሆኑን አስታውሰዋል።

ነገር ግን ቋሚ ኮሚቴው በተለይ የመንግሥት በጀት በትክክል ሥራ ላይ መዋሉን ከዋና ኦዲተር ጋር በተናበበ መልኩ መተግበሩ በበጎነት እንደሚታይ አንስተዋል። ተጠያቂነትን ለማስፈን የሄደበት ርቀትም እንደሚበረታታ አንስተዋል።

በአንዳንድ ተቋማት ችግሮች የሚፈጠሩት የፋይናንስ ሥርዓቱን ባለማወቅ በመሆኑ በአስተዳደር ጉዳይ እንዲታይ ቢደረግ ነገር ግን ከፋይናንስ ሥርዓቱ ውጪ የሚንቀሳቀሱ አካላት ካሉ ተጠያቂ ለማድረግ ትኩረት ቢሰጥ መልካም እንደሚሆን አንስተዋል።

ፎረሙ የኦዲት ግኝት ባለድርሻ አካላት ባለፉት ሦስት ዓመታት የጋራ የክትትል፣ ቁጥጥር እና ድጋፍ ተግባራትን ከመፈጸም አንጻር በታዩ ዋና ዋና ጥንካሬዎችና እጥረቶች እንዲሁም የትኩረት አቅጣጫዎችን በመለየት ውይይቱ ተካሂዷል።

ፎረሙ ባካሄደው ግምገማ በፋይናንስ ሕጋዊነት ኦዲት በግኝት ከለያቸው መካከል የጥሬ ገንዘብ ጉድለት፣ ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ከአንድ ወር ጀምሮ 10 ዓመትና ከዚያ በላይ የቆየ መሆኑ፣ የመንግሥትን ገቢ በወጡ ሕጎች መሠረት አለመሰብሰብ፣ ሕግን ያልተከተሉ ክፍያዎች መፈጸም ይገኙበታል።

ሕግን ያልተከተሉ ክፍያዎች መፈጸም፣ ገቢ እንዲሰበስቡ የተፈቀደላቸው የመንግሥት ተቋማት የተሰበሰበውን ገቢ በትክክል መዝግቦና በሂሳብ ሪፖርት አካትቶ ለገንዘብ ሚኒስቴር የማያቀርቡ ተቋማት መኖራቸውንና ለግንባታ፣ ለሌሎች ግዢዎች፣ ለደመወዝ ለውሎ አበልና ለሌሎች ክፍያዎች ሊከፈል ከሚገባው በላይ ወጪ ማድረግም በፋይናንስ ሕጋዊነት ኦዲት በግኝት ያቀረባቸው ጉድለቶች ናቸው።

ከንብረት አስተዳደር ጋር ተያይዞም ፎረሙ ለቋሚ እቃዎች የተሟላ መለያ ቁጥር አለመስጠት፣ የቋሚ እቃ መዝገብ አለማዘጋጀት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ እቃዎችን በሕጉ መሠረት አለማስወገድ ተጠቃሽ ናቸው።

በክዋኔ ኦዲትም በአብዛኛው የመንግሥት የግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜና በጀት ያለማጠናቀቅ፣ ለፕሮጀክቶች በጀት ከመፈቀዱ በፊት በበቂ ጥናት ላይ የተመሠረቱ፣ የተሟላና የተረጋገጠ ዲዛይን መኖሩ በአግባቡ የማይረጋገጥ መሆኑ ለይቷል።

በተጨማሪም በተለይም ግዙፍ ፕሮጀክቶቹ ግልጽ እና ተጨባጭ የትግበራ መርሐ ግብር የተዘጋጀላቸው መሆኑን ከማረጋገጥ እና በግንባታ የሚሳተፉ ተቋራጮችን የካፒታል አቅም አነስተኛ መሆን፣ የአማካሪዎች አፈጻጸም ከጥራት፣ በጊዜና በጀት አኳያ የክትትል መስፈርት በመዘርጋት በመረጃ በመመሥረት በቂ ክትትል ስለማያደርጉ የፕሮጀክት አፈጻጸም ጉድለት መኖሩን መለየቱን አመልክቷል።

ፎረሙ ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት አስተያየት ለመጀመሪያ ጊዜ በቀረበባቸው 59 ተቋማት ላይ የገንዘብ ቅጣት፣ ከባድ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፣ እና በሦስት ዩኒቨርሲቲ ኃላፊዎች ደግሞ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ማድረጉም ተጠቅሷል።

# ምንጩ ያልታወቀ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተወካዮች ምክር ቤት የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ምንጩ ከማይታወቅ ንብረት ማስመለስ ረቂቅ አዋጅ ዙሪያ ከፍትሕ ሚኒስቴር የሥራ ኃላፊዎችንና ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ውይይት አድርጓል።

ለመሆኑ የንብረት ማስመለስ አዋጅ ፋይዳው ምንድነው፤ አዋጁ ያሉበት ስጋቶችስ የሚሉ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የሚመለከታቸው አካላት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

በፌዴራል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ማጣራት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አዳነ መለሰ ፤ በሥራ ላይ ያለው የንብረት ማስመለስ አዋጅ ውስንና ወጥ አለመሆን፣ መንግሥት የኢኮኖሚ ወንጀሎችን ለመከላከል ካለው ቁርጠኝነት እንዲሁም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ሕጎች ለአዋጁ መውጣት ምክንያት መሆናቸው ያነሳሉ፡፡

ረቂቅ አዋጁ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት የፍትሐብሔር ተጠያቂነት በሁሉም ሰውና በሕግ ሰውነት ባላቸው ተቋማት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ያስቀመጠ ነው ይላሉ፡፡

የአዋጁ መነሻ ሃሳብ ከተባበሩት መንግሥታት ፀረ ሙስና ኮንቬንሽን የመነጨ መሆኑንና ወቅታዊና አስፈላጊ በመሆኑ የሚደገፍ ነው ያሉት፡፡

የንብረት ማስተዳደርን በተመለከተ በአዋጁ የፍትሕ ሚኒስቴር ኃላፊነት እንደሚወስድ አመላከተው፤ ይህም ግልጽነት የጎደለው አሠራር እንዳያስከትል እራሱን የቻለ ነፃና ገለልተኛ ተቋም ቢቋቋም የተሻለ ይሆናል ሲሉ ይናገራሉ ፡፡

በንብረት ማስመለስ ሂደት የሚገኘው ሀብት በአዋጁ እንደተቀመጠው ከሆነ በፍትሕ አስተዳደር ዘርፍ ላይ ለተሠማሩ አካላት አቅም ግንባታ እንደሚውል ያመለክታል ያሉት አቶ አዳነ፤ ነገር ግን የፀረ ሙስና ትግል ብዙ ባለድርሻ አካላትን የሚያካትት በመሆኑ የሚገኘው ሀብት ለተለያዩ ተቋማት ለትውልድ ሥነምግባር ግንባታ ቢውል መልካም መሆኑን ይገልጻሉ ፡፡

በሌላ በኩል በሀብት ማስመለስ ሥራው ወንጀሉን የሚጠቁመው አካል ደኅንነት ለመጠበቅ እንዲያስችልም የመረጃ ማሰባሰብ ሥራው ዲጂታል መሆን አለበት፡፡ ይህም በአዋጁ በግልጽ መቀመጥ ይኖርበታል ይላሉ፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት አቶ ጌታቸው ዋቄ እንደሚሉት፤ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 25 ላይ በሚወረስ ንብረት ላይ ሦስተኛ ወገን መብት ካለ ማስረጃ አቅርቦ ማስቀየር ይችላል የሚል ሲሆን እዛው አንቀጽ ላይ ንዑስ ቁጥር አራት ላይ ግን በዋናው ገንዘብ ብቻ ይላል፡፡ ይህም በተለይም ባንኮች በንብረት የሚመሠረቱትን የመያዣ መብት የሚገድብና የወለድ ማስከፈል መብታቸውን የሚከለክል በመሆኑ መታየት ይኖርበታል፡፡

በሌላ በኩል የሚወረሰው ንብረት ፋብሪካ አልያም ሌላ ንብረት ሊሆን ይችላል የሚሉት አቶ ጌታቸው፤ ይህም የሚተዳደርበት ሥርዓት እና የሚበላሹ ንብረቶች የሚወገዱበት ሥርዓት በአዋጁ በግልጽ ቢቀመጥ የተሻለ ይሆናል ይላሉ፡፡

አቶ ጌታቸው፤ የንብረት ግምት ማውጣት ለአዋጁ ተፈጻሚነት ፈታኝ የሚሆን ጉዳይ ነው ሲሉ ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ንብረት የሚገምት ተቋም ባለመኖሩ ገማች ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ ይሆናል ሲሉ ይናገራሉ፡፡

በዋናነት አዋጁ የፋይናንስ ተቋማትን የብድር ሥርዓት ሊያዛባና ባንኮችም የሰጡት ብድር ተመላሽ እንዳይሆን ስለሚያደርግ በጥንቃቄ ሊታይ እንደሚገባ ይገልጻሉ፡፡

ስለአዋጁ ዓላማ ማብራሪያ የሰጡት የፍትሕ ሚኒስትር ወይዘሮ ሐና አርዓያሥላሴ በበኩላቸው፤ የሀብት ማስመለስ አዋጁ በሀገሪቱ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሰ ያለውን የኢኮኖሚ ወንጀል ለመከላከልና ለመቆጣጠር አስፈላጊ ነው፡፡ በሕገ-ወጥ መንገድ የተገኙ ንብረቶችን ለማስመለስም ቁልፍ ሚና አለው ይላሉ።

ከዚህ ቀደም ያሉት ሕጎች ውስንና የተበታተኑ መሆናቸውን አንስተው፤ የሀብት ማስመለስን በሚመለከት ሁሉን አቀፍና አንድ ወጥ የሆነ ሕግ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑንም ነው ያስረዱት።

የኢኮኖሚ ወንጀሎች ድንበር ተሻጋሪና ከፋይናንስ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ረቂቅ አዋጁ ይህንን ለማስቀረት ድንበር ተሻጋሪ ሥራዎችን መሥራት የሚያችል ነው ሲሉ ያስረዳሉ።

ምንጩ ያልታወቀ ሀብት በዚህ አዋጅ የፍትሐብሔር ተጠያቂነት በሁሉም ሰውና በሕግ ሰውነት ባላቸው ተቋማት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን አንስተው፤ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትን አዋጁ ከወጣበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን አዋጁ ከመውጣቱ በፊት እስከ 10 ዓመት ያሉ ጉዳዮችን ማየቱ የሀገሪቱን የመረጃ አያያዝ ከግምት ውስጥ በማስገባት መሆኑን ያብራራሉ፡፡

አዋጁ ወጥ የሆነ የንብረት ማስመለስ አስተዳደር ሥርዓት ሊዘረጋ የሚችልና በወንጀል የተገኘ ንብረትን የማስመለስ፣ ማጣራት፣ መያዝ፣ ማገድና መክሰስ የሚሉ በዝርዝር ጉዳዮችን የሚያስቀምጥ መሆኑንም ነው ያስታወቁት።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

# የአየር መንገዱ የተፋጠነ የስኬት ጉዞ ማሳያ

ወርቅነሽ ደምሰው




ፎቶ፡ ገባቦ ገብሬ

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከከፍታም በላይ ከፍ ብሎ መብረር መጓዙን ቀጥሎበታል። ኢትዮጵያን በመላው ዓለም በማስተዋወቅ የሀገር ኩራት የሆነው አየር መንገዱ በአፍሪካም ቀዳሚው መሆን የቻለም ነው። ዓለም አቀፍ ውድድር በበዛበት የአቪየሽን ዘርፍ ከአፍሪካ የቀዳሚነቱን ስፍራ እንደያዘ መዝለቅ መቻሉን በየጊዜው እያረጋገጠና እያስመሰከረ የመጣ የአህጉሪቱ ኩራት ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ባከናወናቸው ስኬታማ ተግባሮችም ታላላቅ ሽልማቶችን በየጊዜው በማግኘት ይታወቃል። በርካታ ዓለም አቀፍ ሽልማቶችን የተቀበለ ነው።

በሰብአዊ ተግባሩም ይጠቀሳል። በቅርቡ ከተበረከቱለት ሽልማቶች መካከል በኮቪድ ወቅት ላበረከተው ሰብአዊ ተግባር የተበረከተለት ዓለም አቀፍ ሽልማት ለእዚህ በአብነት የሚነሳ ነው። በኮቪድ 19 ወቅት ሁሉም አየር መንገዶች ሊባል በሚችል መልኩ ስራ አቁመው እያለ ለወረርሽኙ ተጠቂዎችና የሕክምና ተቋማት መዳህኒትና የመሳሰሉት በመጓጓዝ ታላቅ የማህበራዊ ኃላፊነት ተግባር ያከናወነም ነው።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ግሩፕ በሚል በስሩ በርካታ ግዙፍ ተቋማትን ማፍራት የቻለው ተቋሙ፣ በበረራ ትምህርት ቤቱ፣ በግዙፍ ሆቴሉ፣ በአውሮፕላን ጥገና ተቋሙ፣ ለበረራ የሚያስፈልጉ ምግቦችን በሚያዘጋጀው ድርጅቱም ይታወቃል።

መንገደኞችና ጭነት በማጓጓዝ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ በየጊዜው በተለያዩ ዘርፎች የተለያዩ ሽልማቶችን እየወሰደ ስሙን አስጠብቆ መዝለቅ ችሏል። አየር መንገዱ ከቦይንግና ከኤርባስ ኩባንያዎች የመንገደኞች ምቾች የሚያስጠብቁ እጅግ ዘመናዊ የሆኑ አውሮፕላኖች ማስመጣቱን ቀጥሏል።

መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ቀዳሚ በሆነበት አፍሪካ፣ 63 መዳረሻዎች ያሉት ሲሆን፣ ይህም በአህጉሪቱ ግዙፉና ቀዳሚው አየር መንገድ እንዲሆን ያደርገዋል። በዓለም አቀፍ ደረጃ 133 መድረሻዎች አሉት። በዓለምም ከ100 አየር መንገዶች 36ኛ ደረጃ ላይ መቀመጡን በተያዘው የፈረንጆቹ 2024 የወጣ መረጃ አመልክቷል።

አገልግሎቱን ለማስፋት፣ ይበልጥ ለማዘመን፣ ተወዳዳሪነቱን ለማላቅ ሁሌም የሚታትረው አየር መንገዱ፣ በአቪዬሽን ኢንዱስትሪው ልቆ መውጣት የሚያስችሉ በርካታ ተግባሮችም እየተከናወኑለትም ይገኛል። በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድም ይህንኑ አመልክተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባለፈው ሳምንት ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ በሰጡበት ወቅት በሀገሪቱ እየተመዘገበ ላለው እድገት የአገልግሎት ዘርፉ እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ አስታውቀዋል። ከአገልግሎት ዘርፉም የኢትዮጵያ አየር መንገድን በአብነት ጠቅሰው ሲያብራሩ አየር መንገዱ በዚህ በጀት ዓመት 124 አዳዲስ አውሮፕላኖችን ማዘዙን ገልጸዋል።

በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ ብቻ ሳይሆን፤ በአፍሪካ ሁለተኛ የሆነውን አየር መንገድ በእጥፍ የሚበልጥ አቅም እየፈጠረ ነው ሲሉም አየር መንገዱን ገልጸውታል። አሁን ያለው አውሮፕላን ማረፊያ ከ20 እስከ 25 ሚሊዮን ተሳፋሪዎች በዓመት ማስተናገድ እንደሚችል ተናግረው፣ ይህም ያለውንና በቀጣይ የሚመጣውን ፍላጎት ለማስተናገድ በቂ አለመሆኑን አስታውቀዋል።

ይህን ፍላጎት ለመመለስም በዓመት ከ100 እስከ 130 ሚሊዮን መንገደኞችን ማስተናገድ የሚችል ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ለመገንባት ጥናቱ ተጠናቋል ሲሉም አመልክተዋል። አዲስ የሚገነባው አውሮፕላን ማረፊያ አሁን ስራ ላይ ካለው በአየር ርቀት ከ40 ኪሎ ሜትር የሚያንስ መሆኑንም አመልክተው፣ ሁለቱ ኤርፖርቶች በባቡር እንደሚገናኙና ሁለቱንም በጋራ ለመጠቀም ሰፊ እድል እንደሚፈጥርም ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አየር መንገዱ በአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ መሆን ብቻ ሳይሆን፤ ባለትልቁ አውሮፕላን ማረፊያም ይሆናል ሲሉም ጠቅሰው፣ ‹‹ሜጋ ፕሮጀክት ነው፤ ሰፊ ስራ እየሰራን ነው። ይሄን ውጤት ካመጣን አየር መንገዳችን ካለው ክብርና ዝና በተጨማሪ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ወስጥ የሚጨበጥ ወጤት እያመጣ የሚቀጥል ተቋም ይሆናል›› ብለዋል።

አንደኛ ወደብ አልባ ለሆኑ ሀገራት እንደዚህ አይነት ተቋማት፤ የገበያ ብቻ ሳይሆኑ ስትራቴጂክ ናቸው። በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ መጠንከር፤ መገንባት አለባቸው። ለዚህ ነው ለቁጥር ለማመን በሚከብድ ደረጃ ሰፋፊ የአውሮፕላን እና የኤርፖርት ልማቶች የተጀመሩት ሲሉ ገልጸዋል።

ይህንንም የኢትዮጵያ ማንሰራራት ማሳያ ነው ሲሉ ተናግረው፣ ‹‹124 አውሮፕላን ማዘዝ ቀላል ነገር አይደለም። በዚያው ልክ ፓይለት፣ በዚያው ልክ የጥገና ቦታ፣ በዚያው ልክ በጣም በርካታ ዝግጅቶች ማድረግንም ይፈልጋል ሲሉም አስታውቀዋል።

ይህ ከፍታው የተረጋገጠለት የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሰሞኑን በአፍሪካም የመጀመሪያው የሆነውን ኤ350-1000 ኤር ባስ አውሮፕላን ተረክቧል። የአየር መንገዱና የአየር መንገዱ የቦርድ ኃላፊዎች በተገኙበት ስነስርዓት ከፈረንሳይ ቦይንግ ኩባንያ ርክክብ የተደረገለት አውሮፕላኑ፣ ከትናንትና በስቲያ ደግሞ ቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርስ ደማቅ አቀባበል ተደርጎለታል።

ግዙፉ ኤ 350-1000 የመንገደኞች አውሮፕላን “የምድረ ቀደምት መገኛ - ኢትዮጵያ” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ ከፍተኛ የመንግሰት ባለስልጣናትን ጨምሮ በርካታ ሰዎችን አሳፍሮም በኢትዮጵያ የአየር ክልል ላይ ለሁለት ሰዓት ዝቅ ብሎ መብረሩም ታውቋል።

መረጃዎች እንደሚያመላክቱት፤ ኤ350- 1000 ኤርባስ አውሮፕላን ሌሎች አውሮፕላኖች ከተሰሩበት ቁሳቁስ ለየት ባለ መልኩ የተሰራ ሲሆን፣ ይህም ሁኔታ ከሌሎች አውሮፕላኖች ይልቅ በአየር ላይ መብረሩን ቀላል ያደርግለታል። አውሮፕላኑ በርካታ መንገደኞችንና እቃዎችን በቀላሉ መጫን እንዲችልም ያደርገዋል። ከ350 እስከ 410 የሚደርሱ መንገደኞችን ከእነ እቃቸው መጫን የሚችል ሲሆን፣ በካርጎ ደግሞ 208ሺ ኪ.ግ የሚደርስ እቃ መጫንም ይችላል።

16ሺ 482 ኪሎ ሜትር ያለ ማረፍና ያለማቋረጥ መብረር የሚችለው አውሮፕላኑ፣ ነዳጅም ቆጣቢና ለአየር ንብረት ተስማሚ መሆኑም ተነግሮለታል። ከሌሎች አውሮፕላኖች ጋር ሲነጻጸር 25 በመቶ ያህል ነዳጅ ይቆጥባል።

አውሮፕላኑ ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ በደረሰበት ወቅት የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋዜጠኞች ያነጋገሯቸው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ዋና ሥራ አስፈጻሚ መስፍን ጣሰው፤ አየር መንገዱ ኤ350- 1000 ኤርባስ የተሰኘውን ይህን አውሮፕላን ከፈረንሳይ ኤርባስ ኩባንያ ተረክቦ ወደ አዲስ አበባ ማምጣቱን ጠቅሰው፣ ይህ ግዙፍና ዘመናዊ አውሮፕላን ለኢትዮጵያ አየር መንገድ የእድገት ጉዞ ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥር ተናግረዋል።

‹‹ የአውሮፕላኑ አየር መንገዱን መቀላቀል ለአፍሪካ የአቪየሽን ኢንዱስትሪም አዲስ ምዕራፍ የከፈተ ነው›› ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ የኤ350-1000 አውሮፕላን ከኢትዮጵያ ባለፈ ለአፍሪካ አቪየሽን ዘርፍ አዲስ ተስፋን የሰነቀ ስለመሆኑም ተናግረዋል። አየር መንገዱ የላቀ የደንበኞች አገልግሎት እንዲሰጥ የሚያስችለው ከመሆኑም በላይ በዘርፉ ያለውን ተወዳዳሪነት ይበልጥ እንደሚያሳድግም አስታውቀዋል።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ይህ አውሮፕላን አየር መንገዱ ካዘዛቸው ተመሳሳይ አውሮፕላኖች ወደ ኢትዮጵያ በመግባት የመጀመሪያው ነው። ቀሪዎቹ ሦስቱ በቅርብ ወራት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ።

አውሮፕላኑ በአይነቱ ከሌሎች አውሮፕላኖች ይለያል። 395 ወንበሮች ያሉት ሲሆን፣ ሌሎች አውሮፕላኖች ላይ የሌሉ እዚህ አውሮፕላን ላይ ብቻ የተገጠሙ እጅግ ዘመናዊ የመንገደኞች መገልገያ ፋሲሊዎች የተገጠሙለት ነው። ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያውና እጅግ ዘመናዊ የሆነው የአውሮፕላን ውስጥ የመንገደኞች የበረሪ መዝናኛ (ኢንፍላይት ኢንተርቴመንት) አንዱ ሲሆን፣ ልዩ የሙዚቃና የቪዲዩ ሲስተምም አለው።

ሁለተኛው ልዩ የሚያደርገው ቢዝነስ ክላሱ (አንደኛ ማዕረግ የሚባለው) 46 ወንበሮች ያሉት መሆኑ ሲሆን፣ ለእዚህ አገልግሎት የሚውሉ መቀመጫዎች እስካሁን ከ30 ወንበር የማይበልጡ ነበሩ። የአውሮፕላኑ ቢዝነስ ክላስ 46 ወንበሮች ያሉት መሆኑ ብዙ የአንደኛ ማዕረግ መንገደኞችን ለማጓጓዝ ያስችላል።

የአውሮፕላን ውስጥ የመብራት ሲስተም (ላይቲንግ ሲስተም) እጅግ ዘመናዊ መሆኑም ሌላው ልዩ የሚያደርገው ነው። መንገደኞች በሚጓዙበት ወቅት ሲቀመጡም፣ ሲተኙም ሆነ ሲበሉ እና የተለያየ አይነት ብርሃን በማቅረብ ጉዞአቸው ምቾት የተሟላበት እንዲሆን ያደርጋል።

ነዳጅ መቆጠብ የሚያስችል መሆኑም ሌላው ልዩ የሚያደርገው ነው። አውሮፕላኑ ይህንን ሁሉ ያሟላ በመሆኑ በትልቅነትም ሆነ የመንገደኛ ምቾች ከመጠበቅ አንጻር ለየት እንዲል እንዳደረገው ይገልጻሉ።

የኤ350-1000 አውሮፕላን ለአፍሪካም በኢትዮጵያ አየር መንገድ የገባ የመጀመሪያው አውሮፕላን ነው ያሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ሁልጊዜም አዳዲስ አውሮፕላኖች በማምጣት ከአፍሪካ ግንባር ቀዳሚ መሆኑን አስታውቀዋል። አሁንም ያስመጣው አውሮፕላንም አየር መንገዱ ይህን አካሄድ አጠናክሮ መቀጠሉን እንደሚያመለክት ገልጸዋል።

‹‹ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከአፍሪካ ትልቁ አየር መንገድ እንደመሆኑ ብዙ አገራትን በመብረር ይበልጣል፤ ብዙ አውሮፕላኖችንም በማብረር እንዲሁ እኛ እንበልጣለን። አፍሪካ ውስጥ ሁለተኛ ደረጃ የያዘው አየር መንገድ የኛን ግማሽ ያህል ብቻ ነው አውሮፕላን ያለው። እኛ ግን ትልቁን ነን ብለን አልተቀመጥንም፤ የበለጠ ጥረት በማድረግ በፍጥነት ለማደግ እየሰራን ነው ›› ሲሉ አብራርተዋል።

አየር መንገዱ ከዚህ በኋላ ብዙ አውሮፕላኖችን ለማስመጣት ማቀዱን ዋና ሥራ አስፈጻሚው ጠቅሰው፤ ከ120 በላይ አውሮፕላኖች በትዕዛዝ ሂደት ላይ መሆናቸውንም አስታውቀዋል። እነዚህ አውሮፕላኖችም በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት ወደ አገር ውስጥ እንደሚገቡ ገልጸዋል።

‹‹ አዳዲስ የጉዞ መድረሻዎች እየተከፈቱ መሆናቸውንም ተናግረው፣ ይህም የመንገደኞች ብዛት እንዲጨምር ያደርጋል፤ እድገታችንም ፈጣን ይሆናል›› ሲሉ ተናግረዋል።

‹‹ ብዙ ስንበር፣ ብዙ መንገደኞች ማጓጓዝ ስንችል ገቢያችንን ይጨምራል›› የሚሉት ዋና ሥራ አስፈጻሚው፤ አየር መንገዱ አሁን ካሉት የበረራ መዳረሻዎች በተጨማሪ ብዙ አዳዲስ መስመሮች እንደሚከፈቱ ጠቁመዋል። ከጥቂት ቀናት በፊት ባንግላዴሽ አዲስ መስመር መከፈቱን አስታውሰው፤ በቅርቡም ወደ ላይቤሪያ በረራ እንደሚጀመርና በየጊዜው አዳዲስ መዳረሻዎችን በመክፈት ብዙ መንገደኞችን ማግኘትና ማደግ እንደሚቻል አመላክተዋል።

አየር መንገዱ አሁን የኤ350-1000 አውሮፕላን ያስመጣ እንጂ ቀሪዎቹ ሦስቱ አውሮፕላኖችም በፍጥነት እንደሚመጡ ገልጸው፤ ሌሎች በሂደት የሚመጡ መኖራቸውንም ጠቁመዋል። እነዚህን አውሮፕላኖች ለማሰራት ከፍተኛ ወጪ እንደሚጠይቅ የተናገሩት ዋና ስራ አስፈጻሚው፣ የኤ350-1000 አውሮፕላን ዋጋ 200 ሚሊዮን ዶላር እንደሆነም ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥና የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሰብሳቢ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ በበኩላቸው ኤ350-1000 አውሮፕላን በአፍሪካ የአቪየሽን ኢንዱስትሪ አዲስ ምዕራፍ የከፈተ መሆኑን ተናግረዋል። አየር መንገዱ በአቪየሽን ዘርፉ እያሳየ ያለውን ስኬት ከኢትዮጵያም ባሻገር ለመላው አፍሪካውያን ኩራት መሆኑንም ጠቁመዋል።

ግዙፉ ኤ350-1000 የመንገደኞች አውሮፕላን በአፍሪካ መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ መግባቱ የአየር መንገዱን ስም ይበልጥ ከፍ እንደሚያደርግ ገልጸው፡ አየር መንገዱ በተፋጠነ የስኬት ጉዞ ላይ መሆኑን እንደሚያሳይ አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ይህን አውሮፕላን ማስመጣቱ በእድገትና በስኬታማ ጉዞ ላይ ስለመሆኑ ሌላው ማሳያ መሆኑን ጠቅሰው፤ አየር መንገዱ ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ከሚያበረክተው ዘርፈ ብዙ አስተዋፅዖ ባለፈ ዓለም አቀፍ የአቪዬሽን ሀብት መሆኑንም አመላክተዋል።

‹‹ኢትዮጵያን የዓለም አቀፍ አቪዬሽን ማዕከል ለማድረግ እየተሠራ ነው›› ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ፤ ለዚህም በዓመት ከ110 ሚሊዮን በላይ መንገደኞችን የማስተናገድ አቅም ያለው አዲስ የአውሮፕላን ማረፊያ ልማትን ጨምሮ በርካታ መሠረተ ልማቶች ላይ ኢንቨስት እየተደረገ መሆኑን አስታውቀዋል።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

## ጎሜ

# ባለመኪናዎቹ

ምሕረት ሞገስ

መስከረም ጠብቶ የሁለተኛው ወር ጥቅምት ሲጀምር፤ የክረምቱ ዝናብ ቆሞ አካባቢው በልምላሜ ሲዋብ ፀሃይ ደመቅ ብላ ስትወጣ፤ መንግስቱ ተሰማ ጓደኞቹ ናፈቁት። ከዘውዴ መታፈሪያ እና ከገብረየስ ገብረማሪያም ጋር ለመገናኘት አሠበ። እንደተለመደው የሚያመሹበትን ግሮሰሪ አስታወሰና ትንሽ ተከዘ።

የእጅ ስልኩን አንስቶ ወደ ገብረየስ ደወለ። ገብረየስ ጥሪውን ለመመለስ አልዘገየም፤ ከወዲያኛው ማዶ ገብረየስ « የጠፋ ሰው» አለው፤ መንግስቱ በበኩሉ « አሁንም የደወልኩት እኔው ነኝ። ምነው ጠፋህ እንዳትባል መቅደምህ ነው? » ሲል በጥያቄ አሳቀቀው። በእርግጥም ገብረየስ የሚለው አልነበረውም። መወቃቀሳቸውን ጨርሰው፡ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ አስራ ሁለት ሰዓት አካባቢ ለመገናኘት ቀጠሮ ያዙ።

መንግስቱ ገብረየስን ብቻ ሳይሆን ዘውዴንም ለማግኘት በማሰቡ፤ እርሱም ጋር ደወለ። ዘውዴ እንደገብረየስ አልፈጠነም፡ ጭራሽ ጥሪው ሳይነሳ ቀረ። መንግስቱ ግራ ገባው ደጋግሞ ሲደውል ዘውዴ «በኋላ እደውልልሃለሁ» የሚል መልዕክት ላከለት። መንግስቱ ተረጋጋ። ቁጭ ብሎ መቼ እንደተገናኙ ሲያስታውስ፤ ለራሱ «ያቺ ማምሻ ግሮሰሪ ከመፍረሷ በፊት ነው፡፡» ብሎ አንድ ዓመት አካባቢ እንደሚሆነው ገመተ። « ወይ ጉድ ጊዜ ለካ የሚነጉደው እንዲህ ነው። ዕድሜም የሚሔደው እንዲሁ እንደቀልድ ነው፡፡» ብሎ ሃሳቡን ሳይጨርስ ዘውዴ ደወለለት።

ዘውዴ ከሰላምታ በፊት ልክ እንደገብረየስ « እንዴት ትዝ አልኩህ? » አለው፤ መንግስቱ በበኩሉ «እንዴት ትዝ አትለኝም? አንተስ አሁን እኔ አስታውሼ ስለደወልኩልህ እንጂ መቼ አስታወስከኝ? » ሲል ምላሽ ሰጠው። « እኔማ መከረኛ ነኝ፤ እንደ አንተ አልደላኝም፤ ቢደላኝ ኖሮ እንዴት እንደማስታውስህ አሳይህ ነበር። » ሲል ዘውዴም በበኩሉ ምላሽ ሰጠ። መንግስቱ ደግሞ፤ « እንግዲህ ማምሻ ግሮሰሪ ፈርሳለች። ደህና ቦታ ወስጄ ልጋብዝህና እንዴት እንደደላኝና እንዴት እያስታወስኩህ እንዳለሁ ላሳይህ?» በማለት የግብዣ ጥያቄ አቀረበለት። ዘውዴ እርሱም ጓደኞቹን ናፍቋልና አላመነታም ወዲያው እሺታውን ገለፀ።

የሚገናኙበትን ቦታ ግን ለመወሰን ተቸገሩ። ዘውዴ ተከራይቶ የሚኖርበት ቤት በመፍረሱ፤ እየኖረ ያለው አራብሳ የሚባል አካባቢ ነው። መንግስቱ ደግሞ ቤት ሠርቶ ለቡ መኖር ጀምሯል። ገብረየስ በበኩሉ እየኖረ ያለው በደህና ጊዜ ያገኛት ላፍቶ አካባቢ የምትገኘው የጋራ መኖሪያ ቤት ነው። መሃል ላይ ለመገናኘት ተስማሙ፤ ነገር ግን ለሁሉም አማካይ የሚሆነው ቦታ የቱ ነው የሚለው ላይ መግባባት አቃታቸው።

ዘውዴ በበኩሉ ከአራብሳ ተነስቶ መገናኛ እንደሚቀርበው ከዛ በላይ ለመሔድ እንደሚቸገር ተናገረ። መንግስቱ «ግዴለም እኔ እና ገብረየስ መኪና ስላለን መገናኛ ቢርቀንም እንመጣለን፡፡ » አለው። ዘውዴ መገናኛ ለመገኘት ተስማማ። መንግስቱ እና ገብረየስ አሥራ ሁለት ሰዓት ላይ የተቀጣጠሩበት ቦታ ላይ ደረሱ። ዘውዴ ግን ከ45 ደቂቃ ቆይታ በኋላ ሲደርስ፤ እነ መንግስቱ ያዘዙት እስኪመጣላቸው እየጠበቁ ነበር። የሞቀ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ምግቡ ሲቀርብ ዘውዴ በመድረሱ ተጨማሪ ምግብ አዘዙ።

መንግስቱ ለዘውዴ « ዛሬም አዲስ ሰፈር ገብተህ ታረፍዳለህ? » ሲል ጠየቀው። ዘውዴ ፈገግ አለ። «የሚያስረፍደው አሮጌነት ሳይሆን ርቀት ነው። ሰፈሩ አዲስ ነው፤ ነገር ግን በጣም ሩቅ ነው። ርቀቱ ደግሞ እንደልብ ትራንስፖርት ማግኘት አያስችልም። እኔም ታክሲ ሳጣ በአስቀያሚ ባስ ተሳፍሬ ከቤቴ አሥር ሰዓት የወጣሁ ከሶስት ሰዓት ድካም በኋላ አንድ ሰዓት ሊሞላ ሲል እናንተ ያላችሁበት ደረስኩ፡፡» ሲል፤ «አይ » አለ መንግስቱ፤ « እኔስ ከቤቴ የወጣሁት አስራ አንድ ተኩል ነው። በ35 ደቂቃ እዚህ ደረስኩ፡፡» ሲል ገብረየስም፤ «እኔም ተመሳሳይ ነው፤ የወጣሁት አስራ አንድ ከሃያ አካባቢ ነው። ይሄንን ሶስት ሰዓት የፈጀ ሰፈርማ ማየት አለብን» አለ።

ዘውዴ፤« እናንተማ ባለመኪና ናችሁ፤ እኛ ሰፈር ለመሄድ መንገዱ ካልተዘጋ በ30 ደቂቃ ትደርሳላችሁ። ችግር የሚሆነው ለእንደኔ አይነት ድሃ እና እግረኛ ነው፡፡» አለ። አያይዞ ለመንግስቱ፤ « እኔ የምልህ በር ላይ የቆመችው መኪና ያንተ ናት? መኪና ቀየርክ እንዴ? » ሲል ጥያቄ አቀረበ። ገብረየስ በበኩሉ ፈገግ እያለ «እስከ አሁን አላየኸውም እንዴ? አንድ ሰሞን ደስታ በደስታ ሆኖ ነበር። ገዘፍ ያለ መኪና ያስደስታል፡፡» አለ። ዘውዴ መለስ ብሎ፤ « ታዲያ ምን ነው? ይህን የመሰለ መኪና እኔ እንደመጣሁበት አውቶቢስ አቆሸሽካት? » ሲለው መንግስቱ ሽምቅቅ አለ።

ገብረየስ እየሳቀ፤ « የገዛት ዕለት ብታየው ደስታውና ፈንጥዝያው የተለየ ነበር። ‹ብርቅ እና ድንቅ ያለ አንድ ቀን አይደምቅ › እንደሚባለው ለአንድ ቀን አብለጨለጫት። በኋላ ግን ረሳትና አቆሸሻት፤ የእኔዋ የድሃ መኪናስ አየኻት እንዴት ፅድት እንዳለች አስተውለሃል?» ሲል ገብረየስ ፊቱን ወደ ዘውዴ አዙሮ ጥያቄ አቀረበ።

ዘውዴ የቀረበውን ምግብ እየጎረሰ፤ « የአንተ እንኳ የመኪናዋ እርጅና እንጂ ፅዳቷ ተጠብቋል። የመጣሁበትን ባስ ቆሻሻ ብታዩ መፈጠራችሁን ትጠሉ ነበር። ለነገሩ የመንግስቱ መኪና እንደዛ ይቆሸሻል ብዬ አላስብም፡፡» ሲል ምላሽ ሰጠ። መንግስቱ እየሳቀ፤ « ቁርጥ እየጋበዝኩ፤ ዲ ፎር ዲ መኪናን ከባስ ጋር ማነፃፀር በጣም ትልቅ ሃጢያት ነው፡፡» ብሎ ሳቁን ቀጠለ።

ገብረየስ እየሳቀ « መንጌ አልገባህም፤ ዘውዴ ምን እያለህ መሰለህ አዝማሚያው እንደሚያሳየው ‹ጅብ ውሃ ሲጠጣ ከታች ያለችውን አህያ አታደፍርሺብኝ አላት› እንደሚባለው ነው። እንደተለመደው ሊነቁርህ ፈልጎ ነው። መኪና መግዛትህን ለማጣጣል ወይም መኪና ስለቀየርክ ተበሳጭቶ ነገር እየፈለገህ ነው እንጂ፤ መኪናህን አንተ ባታጥበው ሄደህ ማሳጠብ ያቃትሃል? » አለው።

ገብረየስ ወደ ዘውዴ መለስ ብሎ አይን አይኑን እያየ « በነገራችን ላይ ስለባስ መቆሸሽ ስትናገር፤ ከተማዋ በጣም እየፀዳች አንዳንዱ ቤቱን ደጁን መኪናውን ብቻ ሁሉን ነገር ለምን እንደማያፀዳ ግራ ይገባኛል። አንተ የተሳፈርክበት ባስ መፅዳት አለበት። ተቋሙ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ሲሰጥ በፀዳ እና በሚመች መልኩ ቢሆን መልካም ነው። የአውቶቢሱ እና የተሳፋሪው ቁጥርን ማመጣጠን ቢከብድ እንኳ፤ አውቶቢሶቹን ፅዱ ማድረግ የሚከብድ አይመስለኝም።

ነገር ግን የአውቶቢስ አለመፅዳት ችግሩ የተቋሙ እና የሹፌሩ ብቻ አይደለም። የአንተም ኃላፊነት ነው። ተሳፋሪው ራሱ ለሚሳፈርበት መኪና ካልተጠነቀቀ ምን ማድረግ ይቻላል? እንደውም ለንፅህና ያለን አመለካከት በደንብ መስተካከል አለበት፡፡» ሲል ዘውዴ በንዴት የጎረሰውን እያላመጠ በመስማማት አንገቱን ግራ እና ቀኝ ነቀነቀ።

ዘውዴ በጣም ተናደደ። « የመንግስቱ ሳያንስ አንተም የሁሉም ችግር መነሻ እኔ እንደሆንኩ ማስመሰል ጀመርክ? በጣም ይገርማል። ይሄ በቅርቡ ስንለያይ የመጣ ለውጥ ነው። ‹ጥርስ የሌላት ጥርስ የላትን ነክሳ አነካከስ ታስተምራለች› እንደሚባለው፤ አንተ ለጊዜው ምንም ጥርስ ባይኖርህም አሁን ላይ ጥርስ ያለውን መንግስቱን ክፉ ነገር አስተምረህ ከአንተም የከፋ እንዳታደርግብኝ፡፡» ብሎ እጁን ለመታጠብ ተነሳ።

መንግስቱ ሳቀ። « ምን ማለት ነው? ጥርስ ያለው ጥርስ የሌለው እያለ የሚናገረው። እርሱም ጥርስ ኖሮት የምጋብዘውን ስጋ አኝኮ እየዋጠ ጥርስ የለኝም ብሎ ነገር ምንድን ነው?» ሲል ገብረየስን ጠየቀ። ገብረየስ በበኩሉ፤ « ዘውዴ ለነገር የሚችለው የለም። ከማንም በላይ ነገር አዋቂ ነው። ችግሩ ግን ነገር ማወቅ አያሳድግም። እንደውም በተቃራኒው ያደኸያል። ችግሩ ይሄ ነው። አንተ ደግሞ ነገር አይገባህም። በእርግጥ ነገር የማይገባህ መሆኑ ጥሩ ነው። ዋናው ጉዳይ መኪናህን ግን አሳጥብ፡፡» አለው፡፡

እጁን ታጥቦ የመጣው ዘውዴ ሰምቶ ነበር። « አዎ ለሚለፉትም እዘንላቸው። እንዲህ ከተማዋን እያሳመሩ፤ እናንተ ደግሞ የፀዳችዋ ከተማ ላይ ቆሻሻ መኪና እየነዳችሁ ውበቷን አትቀንሱት፡፡» ሲል ገብረየስ ሳቁን መቆጣጠር አቃተው። አፉን በእጁ አፍኖ ወደ መታጠቢያ ቤት እየሮጠ ሔደ። መንግስቱ ግራ ገባው። ዘውዴ የተናገረው እውነት ነው። ገብረየስ ለምን ይህን ያህል ሳቀ ሲል ራሱን ጠየቀ።

ገብረየስ ታጥቦ ተመለሰ። ለዘውዴ « አንተ እኮ ችግርህ ሁልጊዜ የሚታይህ ጨለማ ብቻ ነው። ጨለማን ለሚያስብ ሰው ብርሃን አይታየውም። ዛሬ ግን ለመጀመሪያ ጊዜ የከተማዋን ውበት ስታደንቅ ሰማሁ። ለመጀመሪያ ጊዜ ብርሃን ታየህ። ሰዎች ከተማዋን እያሳመሯት እንደሆነ ከአፍህ ስሰማ ተገርሜያለሁ። አንተም ተለውጠሃል፡፡» ብሎ ሰውነቱ እስኪርገፈገፍ ከት ብሎ ሳቀ።

ገብረየስ ቀጠለ፤ « ያ ሁሉ ማብጠልጠል ቀረ። ‹ሽሮ ቢደነፋ እንጀራ እስከሚቀርብ ነው› እንደተባለው። ከአካባቢው ስትነሳ ቅር ብሎህ አሁን ከአካባቢው ስትርቅ ከተማዋ ውበቷ መታየት ሲጀምር ጭራሽ ተቆርቋሪ ሆነህ መኪናችሁን አፅዱ ከተማዋን አታቆሽሹ ማለት ጀመርክ። እንኳን ለዚህ አበቃህ። » ብሎ በሹፌት ብድግ ብሎ ወታደራዊ የአክብሮት ሰላምታ ሰጠው።

ዘውዴ በበኩሉ፤ « እኔ የከተማዋን ማማር ነቅፌ አላውቅም። ነገር ለማምታታት አትሞክር። አሁንም ቢሆን መኪናዎች እና ትራንስፖርት ሥርዓቱ ላይ ትልቅ ተቃውሞ አለኝ። ይኸው የታክሲ ታሪፍ አምስት ብር ሲጨመር፤ መንገዱን እየቆራረጡ የሃያ ብሩን መንገድ 40 ብር፤ የ40 ብሩን መንገድ እስከ 80 ብር እየሸነሸኑ ተሳፋሪውን እያንገላቱ ነው። አውቶቢስም ቢሆን እናንተ ባለመኪና በመሆናችሁ ስለማታውቁት እንጂ፤ አውቶቢሱም በአንድ መስመር ላይ 10 ብር ጨምሯል። ይህ ማለት ደግሞ በእኔ እምነት ሕዝቡን ማገልገል ሳይሆን ሕዝብን ማንገላታት ነው። ሕዝብን ሳያስደስቱ ዋጋ ጨምሮ ቆሻሻ ውስጥ እንዲሳፈር ማስገደድ እንደውም ሊያስጠይቅ ይገባል» አለ።

መንግስቱ በበኩሉ፤ « ጭማሪው እንኳ ከነዳጅ ዋጋ ጋር የተያያዘ ነው። መንግስት ከአንተ እና ከእኔ የሰበሰበውን ግብር ለነዳጅ ድጎማ እያዋለው መቀጠል አያዋጣውም። ስለዚህ ከነዳጅ ላይ ድጎማውን ሲያነሳ የበለጠ መወደዱ አይቀርም። አጭር መንገዶች ገንዘብ የሌለውም ቢሆን በእግሩ መሔድ ይልመድ። በሽታ እየተስፋፋ ነው፤ እንደውም የእግር መንገድ መለመድ አለበት። በእኔ በኩል የታክሲም ሆነ የአውቶቢስ ዋጋ ጭማሪ ላይ ተቃውሞ የለኝም፡፡» ሲል ምላሽ ሰጠ፡፡

ገብረየስ በበኩሉ፤ « የነዳጅ ድጎማን ማንሳት እንኳን ከባድ ነው። እኔም በሳምንት ለነዳጅ የማወጣው ገንዘብ ከአራት ዓመት በፊት ከማወጣው በእጥፍ ፤ እንደውም ከእጥፍ በላይ ጨምሯል፡፡» ሲል ዘውዴ ቀበል አድርጎ፤ « አንተ ስለነዳጅ ዋጋ ታወራለህ። እኔ እኮ ክርክስ ባሉ አሮጌ፣ ምንም ፅዳት አግኝተው የማያውቁ በሚመስሉ ታክሲ እና አውቶቢሶች እየተሳፈርኩ፤ የተጋነነ ክፍያ መክፈሌ ተገቢ አይደለም እያልኩ ነው። መንግስቱ እንኳ የዋጋ ጭማሪውን እንዲቃወም አልጠብቅም። እንደውም በዚህ ጊዜ ስለትራንስፖርት ዋጋ ጭማሪ ሲማረር ብሰማው መንግስቱ እርሱ መሆኑን እጠራጠር ነበር፡፡» አለ፡፡

መንግስቱ ፈገግ ብሎ፤ « እንግዲህ ሁሉም የሚያስበው በራሱ ዙሪያ ነው። በእርግጥ ታክሲ እና አውቶቢሶችም ሆኑ አጠቃላይ የግል እና የመንግስት መኪኖች ፅዱ መሆን እንዳለባቸው አያጠያይቅም። በሌላ በኩል ደግሞ ሁሉንም ማስደሰትም ከባድ ነው። ልማት እና ዕድገት ከፈለግን የተወሰነ ሰው ሊጎዳ ይችላል። መቼም ሆን ብሎ ሰውን የሚጎዳ ነገር አይሠራም። እዚህ ላይ መተማመን ይገባል። ከዚህ ውጪ ሁሉም ነገር ላይ ጥርጣሬ እና ክስ ማብዛት፤ ስህተት እየፈለጉ ማንጓጠጥ ጥቅም የለውም። ከዛ ይልቅ ብንደጋገፍ እና ብንማማር ይሻላል። » ሲል ምላሽ ሰጠ።

**ይኸው የታክሲ ታሪፍ አምስት ብር ሲጨመር፤ መንገዱን እየቆራረጡ የሃያ ብሩን መንገድ 40 ብር፤ የ40 ብሩን መንገድ እስከ 80 ብር እየሸነሸኑ ተሳፋሪውን እያንገላቱ ነው፡፡ አውቶቢስም ቢሆን እናንተ ባለመኪና በመሆናችሁ ስለማታውቁት እንጂ፤ አውቶቢሱም በአንድ መስመር ላይ 10 ብር ጨምሯል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በእኔ እምነት ሕዝቡን ማገልገል ሳይሆን ሕዝብን ማንገላታት ነው**

# የዘመን ጥበብ

## ከአንድ ጥላ ስር

ሙሉጌታ ብርሃኑ







ከአንድ ጥላ ስር አረፍ ስንል እዚህም ጥበብ አለች። ጎንን ባሳረፉበት ሁሉ መቀመጫ ድቃስ፣ ለዓይን ምግብ፣ ለልብ እርካታን አታጣም። ያላጣችውን እኛም አናጣም። ከሁሉም ዘንድ፣ ከሁሉም ቦታና ጊዜ አይጠገቤ ሆና የምትኖርን ቢፈልጉ እንደ ጥበብ ያለችውን ከወዴትም አያገኟትም። “ስጡ ይሰጣችኋል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ” የተባለውስ ለጥበብ ይሆን? ጥበብ ሰው ፈልጋ ታጣ ይሆናል እንጂ ሰው ጥበብን ከፈለጋት ጆሮ ዳባ አትልም። እንደሰው በግርድፉ “አይችሉም! አይሆንም!” አትልም። መቻልን አስችላ ለሁሉም፣ በሁሉም ቦታና ጊዜ ከመልካም መልካሙ ተጓድላ አታውቅምና እይታችን ወደ ልብ ብርሃን ይሁን።

ልብ የበራ ዕለት ዓይን ምን ግዱ...ሁሉ በእጄ የሆነችን ጥበብ የያዙ ጊዜም የዓለም ጥልቀትና ስፋት የመዳፍ ያህል ነው። በዓይን ብንመለከት እስከቆመው ተራራ ድረስ ነው። ልብ ግን የተራራውን ጽላሎት ተሻግሮ ወዲያ እስከዳርቻው ያሳየናል። ይህች ጥበብ ናት፤ እሷም እንዲህች ያለች ናት። አንዲት ጥላ ከልብ ብርሃኖች መንደር ትገኛለችና በእርሷው ጎኔን ስንል አንድም ከማህበሩ ፈለገ ኪን፣ ሁለትም ከመንደሩ ብዕረኛ መጽሐፍ ለመግለጥ ነው።

በኢትዮጵያ ዓይነ ስውራን ብሔራዊ ማህበር ውስጥ ልቡ በጥበብ የሚቃጠል አንድ ወጣት ነበር። ይኼ ወጣትም “ለምንድነው እኛ የማህበሩ ዓይነ ስውራን የራሳችን የሆነ የኪነት ቡድን የማይኖረን?” እያለ ሁሌም ይብሰለሰል እንደነበር አጫወተኝ። “እህሳ!” ብዬ ነገረ ጅምሩን እንዲጨርስልኝ ጠበቅኩት። “ከዚያማ ይህን ሀሳቤን ከውጥን ለማድረስ እቅዴን ነድፌ የዓይነ ስውራን ማህበርን ጉትጎታ ጀመርኩ። ተሰጥኦ ያላቸው አባላት ብዙ ሆነው ሳለ ይኼ ሁሉ ተሰጥኦ ለምን ይባክናል ብዬ በማስረዳትና ሌላ ሌላም በማድረግ ላይ ታች አልኩ። በመጨረሻም ይሁንታውን ከበጎ ፈቃድ ጋር አገኘሁ። ቀጥሎም ለባለተሰጥኦዎች ጥሪ በማድረግና ከሌሎቹም ጋር በትጋት በማፋጠን የማህበሩን የኪነት ቡድን መሠረትነው” አለኝ።

“ታዲያ ስሙን ማን አላችሁት?” ብለው “ፈለገ ኪን” ነበር ያለኝ። እውነትም በልብ ፈለግ ሮጠው ያገኙት ነው። ቀጥሎ ግን በዓመታት የሚቆጠር እድሜ ሊኖረው እንደሚችል የራሴን ግምት በውስጤ ይዤ፣ ከተመሠረተ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ብጠይቀው “ሦስተኛ ወሩ ነው። ነሐሴ ላይ ነበር የተመሠረተው” የሚል ምላሽ ሰጠኝ። እኔ ግን ይህን ያህሉን የቆየ ተቋም እንዴትስ ነው እስከዛሬ ድረስ የራሱ የሆነ የኪነት ቡድን ሳይኖረው የከረመው? ስል መገረሜ አልቀረም ነበር።

ይሁንና “ፈለገ ኪን” በማለት የመጀመሪያው የጥበብ ቀዳሽ አስቀዳሽ መሆን ለቻለው፣ ለማህበሩ መስራች ወጣትና የጥበብ ሰው ኢሳያስ ባንቻ አድናቆትን ከክብር መቸሬ አልቀረም። ቅጠል ከግንዱ ላይ ነውና ሦስተኛው የፈለገ ኪን የጥበብ ዘንጋዳ ባሳለፍነው ቅዳሜ ተገምጧል። ታኘኮ ተበላ እንጂ አልተተፋም። ገና ከጅምሩ እንዲህ ለመጣፈጥ ከቻለ እያደር እንደወይን ነው ብዬ አሰብኩ።

በማህበሩ ቅጥር ግቢ ውስጥ ያለችው ትንሽ አዳራሽ በረከቷ ትልቅ ነበር። ጥበብ በተጠራችበት ሁሉ የማይቀረው ታላቁ ገጣሚ፣ ተርጓሚና ጸሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት በዕለቱም ከፊት ገጭ ብሎ አገኘሁት። ሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን ሞቷል ቢሏችሁ “የለም! መቼ ሞቶ!” የሚያስብል አድባር በመድረኩ ሙሉ ደብቦ ይታይ ነበር።

ከሕይወቱ ሕይወትን፣ ከሥራዎቹ ሥራን እየጨለፉ እንኩ በሞቴ! ነበር። ከዘከሩ አይቀርም እንዲህ ነው መዘከር ያስብላል። በአዳራሸዋ ተገኝቶ የዓይነ ስውራኑን ፍካት ለተመለከተ ግን አንዳች ሀሴትን የሚዘራ ነበር። በንዳድ ከርሞ ዝናብ እንዳገኘ ቅጠል መለምለማቸው ከፊታቸው ላይ ይነበባል። ከማህበሩ በወጡ በራሳቸው ባለተሰጥኦዎች ሲቀርቡላቸው የነበሩትን ዝግጅቶችን በሙሉ እያጣጣሙ ሲታደሙት ነበር። ግጥሞችና ጽሁፎች በቀረቡ ቁጥር ሁሉ መስማት ሳይሆን እንደ ወተት ሲጠጡ ነበር ቢባል አያስቀጥፍም።

የፈለገ ኪን አንደኛው የአካል ክፋይ የሆነው ትንሹ ባንድ በአንዲት ኪቦርድ ታጅቦ በሙዚቃ ባለተሰጥኦው ሲቀርብ ለጥቂቶች ብቻ የተሰናዳ ኮንሰርት ነበር የሚመስለው። ታዳሚና ሙዚቀኛው በአንድ ዓይነት ስሜት ውስጥ ሆኖ መመልከት ከስንት አንዴ የሚታይ ልዩ ድባብ ነው። እንደ ውቅያኖስ ሰፍተው እንደ ባህር ከጠለቁት የሎሬት ጸጋዬ ገ/መድህን ሥራዎች ጥቂቶቹ ተመራርጠው በመድረኩ ላይ ሲቀርቡ ለዛቸው ያማረ ነበር።

መልኩን ሳይመለከቱ የውስጡን ከውስጣቸው የቀበሩት የታላቁ የጥበብ ሰው ንግግርና የሕይወት ተሞክሮን ለመስማት ከማንም በላይ ናፍቀውና ጓጉተው ሲጠብቁት የነበረ ነገር ስለመሆኑ አቀባበላቸውን ብቻ መመልከቱ በቂ ነበር። በእያንዳንዱ ንግግሩ የፊት ገጽታቸው ሲያበራ ይታይ ነበር። ከባላገር መንደር መጥቶ እርሱና ጸጋዬ ገ/መድህን የተገናኙባትን ቀጭን መንገድ፣ ከሕይወት ጉዞው ጨልፍታ በመተረክ ገጣሚና ጸሀፊ ተውኔት አያልነህ ሙላት አንደኛው የፈለገ ኪኖች ውበት ነበር። የደራና የፈካ ኪን፣ ጥለቱ ይዘናፈል! ብለናል።

ሁለተኛው ጠማር ሲፈታ ትንሽዋ መጽሐፍ ከነ ትልቅ የጥበብ ድቃሷ ትነሳለች። ዓይነ ብርሃን ያልገታው ልበ ብርሃን “እንዴት ያለው የብዕር ጮማ ነው!” የሚሉትን ዓይነት መጽሐፍ ጽፎ፣ በ87 ገጾች ጀቡኖ፣ በጥበብ ጥራዝ ደጉሶ እንካችሁ! “ከለቻ” ብሏል። ከዚህ ቀደም ደግሞ “እየመሆረሩ መሀይም” በማለት ነበር የመጀመሪያ የሆነችውን የጥበብ በኩራቱን ማበርከቱ።

ደራሲው ሀብታሙ ባንታየሁ የብዕር አኬሩ ቀንታው ከቅርብ ሩቅ ከሆነ ከአንደኛው ሰሞን ላይ “ከለቻ” ያላትን ሁለተኛውን መጽሐፉን ለንባብ አብቅቷል። መጽሐፍ ያህልን ነገር ለመጻፍ ቀርቶ ሳይበሉ መቀመጥ፣ ሳይጠጡ መሽናት እንኳን የለምና ሳይጽፍ አስቀድሞ ማንበብ ግዴታው መሆኑ እርግጥ ነው። ግን ልበ ብርሃን እንደመሆኑ ዓይኖቹ ከማንበብ ርቀዋል። ግን “ጓደኞቼ እያነበቡልኝ” ብሏልና በጎደለን የሚሞላውን አያሳጣን። እንደኛ ሀገር ደግሞ ልዩ ልዩ መጽሐፍትን ለዓይነ ስውራን በሚሆን መልኩ በብሬል ነድሎ ማቅረቡ የማይታሰብ መሆኑን ለማንም የሚነገር አይደለም። ይህ ደራሲም በመጣበት የስነ ጽሁፍ መንገድ ውስጥ አይገጥሙ ትግል ገጥሞ ለዚህ መብቃቱን ማሰብ ይሻል።

እርሱና መሰሎቹ ብዕር ባነሱ ቁጥር ሌላው ደግሞ “በርታ! በርቱ!” ሲል ለእነርሱ ክብርን፣ ለሥራውም አድናቆቱን ባይሰስት ብዙ ሀብታሙዎችን እናቆም ነበር።

መጽሐፏን ካነበብኳት በኋላ አንድ ዘውግ ፈልጌ ልለጥፍባት ብልም በጄ አልል አለችኝ። በመጀመሪያ መጽሐፏን ስመለከታት “ልቦለድ” የሚል ነገር ተጽፎ አገኘሁባት። መግቢያዋን ሳነብ ደግሞ የወግ ዘውግ ያላት መስላ ታየችኝ። ምዕራፍ አንድ “አይጠፋ ዘር”ን ሳነብ ግን የእውነትም ልቦለድ ናት ብዬ ነበር። ግን ደግሞ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ሙሉ ታሪኮቹ፣ እንዲሁም የተራኪ ገጸ ባህሪያቱ የማንነት ኡደት ከአንድ ግለሰብ ስር የተነቀሉ ይመስሉና ወስደው ከግለታሪክ ጋር ያላትሙኝ ጀመር።

ግለታሪኮች ክህደት ከተፈጸመባቸው ልቦለድ የመሆን እጣፈንታ ይኖራቸዋልና ውሳኔው በደራሲው ነው። እናም ግምቴ እውነት ይሆን? ስል ደራሲው ሀብታሙ ባንታየሁን ጠየቅኩት። በእርግጥ ሙሉ ለሙሉ ባይሆንም ከራሱ ታሪክ የጨለፋቸው ጥቂት ነገሮች ስለመኖራቸው ነግሮኛል። ከራሱ ሕይወት ጥቂት ቢነሰንስበትም መጨረሻው ግን ልቦለድ ብቻ ነው።

“ከለቻ” ሲል ደራሲው ከዚህች ርዕስ ላይ ፊጥ ማለቱ ለምንና እንደምን ይሆን? በሦስቱ ፊደላት ብቻ የመጽሐፉን ጭራ ለመያዝ ግን አይቻልም። በበርካታ የማህበረሰብ ክፍሎች ውስጥ ልዩ ልዩ ትርጓሜና መልክ ይዞ የሚገኝ ቃል በመሆኑ። ደራሲው ግን “ድንገቴ የሠርግ ስነ ስርዓት” ከሚለው ጋር ማጋባቱን ተናግሯል። ከለቻን ለመጻፍ ደራሲው ያልገባበት የምናብ ባሕር፣ ያልዞረበት ሕዋ አለመኖሩን ሲያነቡት ፊደላቱ ይናገራሉ። በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ከቋንቋ ረገድ ሁኔታው ከሚፈቅደው በላይ አጠጥሮ ሙሉ ዐረፍተ ነገሩን ድፍን ማድረጉ አስፈላጊ ባይሆንም ደራሲው ግን እንደስሙ ሙሉ የቃላት ሀብታም መሆኑን ይናገራል። በአብዛኛው ከየገጾቹ ውስጥ በየታሪኩ መሃል የገቡ በርከት ያሉ ግጥሞች በራሳቸው ሚስጥር አዘል የታሪክ አቀበት መሆናቸው ያስመሰግነዋል።

ባለ አምስት ምዕራፎች ስብስብ የሆነችው ከለቻ ድብልቅ የብዕር ጠብታዎችን ጠቅለል አድርጋ አቅፋላች። እንግዲህ ከድግስ ድግሱ፣ ትኩስ ትኩሱ ያምራልና መጽሐፏ ከያዘችው ጨለፍ ጨለፍ ብናደርግባት ሳታጠግበን አትቀርም። “አይጠፋ ዘር” ብሎ በምዕራፍ አንድ በመጀመር መቼቱን ወደ አንደኛው የጎጃም መንደር ይወስደናል። የትንሹ ልጅ የልጅነት ሰሞን ትዝታውን በመተረክ ይጀምራል።

“አይጠፋ ዘር” ግን እንደዋዛ አንዲት መንደር ሳትሆን በልዩ የኪዳን አድባር የቆመች ቅጥር ናት። ከመንደሩ ውሪዎች ጋር “ኢስቲ፣ ኢላማ፣ ዳቶ፣ ዎቶ...” በመቆጣጠር ጣፋጩን የልጅነት ጨዋታን ጀምሮ ድንገት ሕልም በሚመስል የምናብ ዓለም ጭልጥ ብሎ ሌላ ሰማይና ምድር ውስጥ እናገኘዋለን። ከዚህ የሚጀምረው የደራሲው ምናብ እሩቅ መጥቆ ያስመጥቀናል። ይሁንና የደራሲው የሀሳብ ጭብጥ የተራኪ ገጸባህሪውን የልጅነት ትዝታን ማጋራት አይደለም። በዚያ አድርጎ የሳላትና ሊመለከት የወደደው ሌላ ስውር ዓለም መኖሩ ነው። ምናልባትም ደግሞ በልቦለድነት ብቻ እንዲታለፍ ያልፈለገው የጀርባ ምስል ስለመኖሩም ጭምር ልናጤንበት እንችላለን።

ደራሲው እልም ካለ የምናብ በረሃ ካስገባን በኋላ ምልሰቶችን ማብዛቱ ትንሽ የአንባቢውን የምናብ ፍሰት መረበሹ አይቀርም። “...የሕልም ዓለም ወጥቼ ዙሪያዬን ስቃኝ ፈገግታቸው የሚሞቅ በወርቅ ወንበር የተቀመጡ ሽማግሌ ተመለከትሁ። ...” በዚህች ዐረፍተ ነገር መካከል ሁለት የተለያዩ የምናብ ዓለማት እንዳሉ ያመለክተናል።

በመጀመሪያው በሕልም ዓለም ውስጥ ሲመለከት ከነበረው ምናብ አውጥቶ ወዲያው ደግሞ “...በወርቅ ወንበር የተቀመጡ ሽማግሌ ተመለከትሁ” ማለቱ መልሶ ሌላ ሁለተኛ ሕልም የሚመስል የምስል ውክልና ያለው አገላለጽ በመሆኑ ስሜትን ያጭበርብራል። ለምሳሌ ይህችን ቅጽበት የምንመለከተው በአንድ ፊልም ላይ ቢሆን ኖሮ አሁናዊ ምስሉ በየትኛው ላይ እንደሆን ለመለየት አዳጋች ይሆንብንና እንድንጠይቅ ሳይሆን እንድንዝለው ያደርገናል። ምልሰቶች ሊበዙ የሚችሉ ቢሆንም እንደ ከለቻ ባለች ትንሽ መጽሐፍ ውስጥ ግን የምናብ ቆይታን ከማንገጫገጫቸውም ሀሳቦችም ይደረታሉ።

የራሳቸው የሆነ ጊዜና ቦታ ጠብቀው ሰፋ ባለ መልኩ ሲሆን ውበት ይኖረዋል። አንባቢን ማስጨነቁ የአንድ ደራሲ ችሎታና የመጽሐፉ ድምቀት ቢሆንም አጠቃቀሙን በብልሃት ማድረጉ ደግሞ ሌላ ጥበብ ነው።

ከለቻ ጉዞውን እየቀጠለ ምዕራፍ ሁለትን ስንደርስ “እናት አባት የቀበረ” ታሪኩ በምዕራፍ አንድ ለነበረው ዋና ገጸባህሪ ሁለተኛው የሕይወት ቀንበጡ ናት። የዚህ መጽሐፍ ትልቁ መቼት “አይጠፋ ዘር” መሆኑን የሚያረጋግጥልን አንድም ይሄኛው ምዕራፍ ነው። ትንሹ ልጅ መንደራቸውን ለቆ ለአስኳላ ወደ ቢቸና ሲያቀና ዞሮ አይጠፋ ዘርን በዓይኖቹ ሲሰናበታት ይነግረናል። ለምን ይሄን ስያሜ እንዳገኘ እናቱን በመጠየቅ ስለዚህ መንደር መነሻና አድባር ስታወጋው እናነባለን።

ደራሲው በምዕራፍ አንድ ላይ የደበቀንን አንዳንድ ነገሮች እዚህኛው ምዕራፍ ላይ እንድናገኘው አድርጎበታል። በትንሽ ገጾች ውስጥ እጅግ ጥልቅ ወደሆነ ምናብ ውስጥ እንደመግባቱ ሁለቱን ምዕራፎች በአንድ ደብሎ በይበልጥ ሰፋ ባለመልኩ ቢሄድባቸው ምናልባትም አንድ ረዥም ልቦለድ ሊወጣው የሚችል ነው። እንደ ታሪክ ፍሰት ምዕራፍ ሁለት ቆንጆ ልንለው የምንችለው ነው።

እንደመጀመሪያው ብዙ ምስሎችን አጭቆ በአንድ ጀንበር እንካችሁ አይለንም። ሰከን ባለ ምናብ ደስ ብሎን እንድናነበው ያደርገናል። በምዕራፍ ሦስት “ምን አገባኝ” ይላል። ደራሲው በቁጥር ባይገልጸውም ከመጀመሪያው ጀምሮ የነበረው ተራኪና ዋና ገጸባህሪው በአፍላ ወጣትነት ላይ ያለ ይመስላል። በድቁና ሕይወቱ ውስጥ ያለፈበትን መንገድ በመተረክ ሌላ ሊኖረው የሚፈልገው ዓለም እንዳላው ያሳብቃል። ያንን ሕይወትም “ሞት ጋባዧ ምላስ” በሚለው ምዕራፍ አራት ላይ የተገናኘው ይመስላል። እዚህ ደግሞ ምናባዊ ምልሰቱ በእውን ከምናውቃቸው ሰዎች ጋር ወስዶ ያላትመናል።

“...ከፍለን ስንወጣ በሩ ስር ጋሽ ስብሓት፣ በዓሉ ግርማ፣ ዓለማየሁ ገላጋይ፣ አያ ሙሌና በእውቀቱ ስዩም ጠረጴዛ ከበው ይጀብናሉ። ...በማለት ጭራዬን ቆላሁና ጉልበታቸውን ሳምሁ። ጋሽ ስብሓት “አፉ ማር” ብሎ ጠራኝና አንገቴ ስር ጨመጨመኝ...” እያለ ተራኪው ገጸባህሪ ከአምስቱ ጋር ስድስተኛ ሆኖ የጀማ ዳቦ ስለመቁረሱ ይነግረናል። በማንነታቸው የምናውቃቸው እንደመሆናቸው ደራሲው ለምናቡ ዓለም ካስማ አድርጎ ያቆማቸው ሰዎች ሲገልጽልን በምናብ የተሳሉበትን መንገድ ለጨዋታው ድምቀት ይሆናል ብለን እንውሰደው (ምልሰት እንደመሆኑ) በንግግራቸው ውስጥ ግን በሚገባ አሳይቷቸዋል። በሕይወት ያሉትም ሆኑ የሌሉት ሕልማቸው የነበረውንና የሆነውን፣ እንዲሁም ያላቸውን ነገር ደራሲው በተራኪው ገጸባህሪ በኩል ትውልዱን ወክሎ ሲቀበላቸው እንመለከታለን።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ተራኪው ገጸባህሪ በአካልም ሆነ በአዕምሮ ጎልብቷል። ልዩ ልዩ ስሞችም ወጥተውለታል። ወደ አንድ የፍቅር መንገድ ሲገባ እንመለከታለን። ደራሲው ከመጀመሪያው ጀምሮ ዳር ዳር ሲለን የነበረ ጉዳይም ከዚህች በፍቅር ከወደቀላት ሴት የሚወለድ ስለመሆኑ በእርግጠኝነት ይናገራል። አምስተኛውና የመጨረሻው ምዕራፍ ራሱ “ከለቻ” ነው። አፉ ማር ያቺን የልቡ ዘለበት የሆነችውን በከለቻ ሥርዓት ለማግባት ይሰናዳል። ታዲያ አፉ ማርን አጅበው በሠርገኝነት የሚሄዱት ሰዎች ጋሽ ስብሓት፣ በዓሉ ግርማ፣ ዓለማየሁ ገላጋይ፣ አያ ሙሌና በእውቀቱ ስዩም ናቸው። አፉ ማር የተመኛትን ኮረዳ ለማምጣት ከወላጆቿ ቤት ገብተው እንደባህሉ ምሰሶውን ይይዛሉ።

ደራሲው ከሳለው ዓለም ውስጥ ሠርጉ ሠርግ ብቻ አለመሆኑን ልብ ይሏል። ከሠርጉ ምሽት ጫጉላው፣ ከጫጉላው ወዲያም አፉ ማር ሣልሳዊ ቴዎድሮስን ከብዟለም ማህጸን ይጠብቃል። ታሪኩም ከምናብ ባሻገር፣ ከጥላው ስር ይቀጥላል።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## የማኅበረሰብ ልማት ፕሮግራም ቤተሰብን ለመታደግ

አስናቀ ፀጋዬ

ሕፃናት የነገ ሀገር ተረካቢ ናቸው ሲባል በተደጋጋሚ ይደመጣል። ይህ የተባለው ያለምክንያት አይደለም። ትውልድ ሲያልፍ ተተኪዎቹና ሀገርን በሁለንተናዊ መልኩ የሚያስቀጥሉት የዛሬዎቹ ሕፃናት የነገዎቹ ወጣቶችና ጎልማሶች በመሆናቸው ነው። ሕፃናት የነገ ሀገር ተረካቢና ትውልድ አስቀጣይ እስከሆኑ ድረስ ደግሞ በሕፃናት መፃኢ ተስፋ ላይ መሥራት ለነገ የሚተው ተግባር አይደለም። ለዛም ነው በርካታ ሀገራት በሕፃናት ላይ ይበልጥ ትኩረት አድርገው የሚሠሩት። በተለይ ዛሬ ላይ የብልፅግና ማማ ላይ የደረሱ ሀገራት በሕፃናት ላይ ትኩረት አድርገው በመሥራታቸውም ነው ራሳቸውን በሁለንተናዊ መልኩ መለወጥ የቻሉት።

ከዚህ በተቃራኒ ኢትዮጵያን ጨምሮ ገና በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በሕፃናት ላይ ትኩረት አድርገው ባለመሥራታቸው ዛሬም ድረስ በሚፈለገው ልክ ራሳቸውን መለወጥ አልቻሉም። በሕፃናት አስተዳደግ፣ ሥነምግባር፣ ትምህርትና ስብዕና ግምባታ ላይ በበቂ ሁኔታ ባለመሠራታቸው ሀገር ተረካቢና ትውልድ አስቀጣይ ማኅበረሰብ በሚገባ መፍጠር ተስኗቸዋል። ቤተሰብና ማኅበረሰብ ላይ ጠንካራ ሥራ ባለመሥራታቸው ቤተሰብ ሲፈርስ ሕፃናት ወላጅ አልባ ሲሆኑ፣ ጎዳና ላይ ሲወጡና ለከፋ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ሲጋለጡ ታይቷል።

ይህ ደግሞ በተዘዋዋሪ በነገ የሀገር ሁለንተናዊ ግንባታና የለውጥ ሂደት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ማድረሱ አልቀረም። በኢትዮጵያም እየሆነ ያለው ከዚህ እውነት የራቀ አይደለም። ለዚህ ደግሞ ከቤተሰብ ጀምሮ እስከመንግሥት ድረስ ያለው ሁሉ በየደረጃው ተጠያቂ ነው። ይህ እንዳለ ሆኖ ግን በሕፃናት ላይ ምንም አይነት ሥራ አልተሠራም ብሎ መደምደም አይቻልም። ሥራው ግን በቂ አይደለም። በተለይ ችግሮች ከመፈጠራቸው በፊት በሕፃናት ላይ ብዙ መሥራት ይቀራል። ሕፃናት ላይ ሥራዎች ተሠሩም አልተሠሩም ግን ሕፃናት በተለያዩ ምክንያቶች ለችግር መጋለጣቸው አይቀሬ ነው።

> **ሕፃናት የነገ ሀገር ተረካቢ ናቸው ሲባል በተደጋጋሚ ይደመጣል። ይህ የተባለው ያለምክንያት አይደለም። ትውልድ ሲያልፍ ተተኪዎቹና ሀገርን በሁለንተናዊ መልኩ የሚያስቀጥሉት የዛሬዎቹ ሕፃናት የነገዎቹ ወጣቶችና ጎልማሶች በመሆናቸው ነው**

በወላጆች አለመስማማት ምክንያት በሚፈጠር ፍቺ፣ ሞት፣ ኢኮኖሚያዊ ችግሮችና በሌሎችም ማኅበራዊ ቀውሶች መንስኤ ሕፃናት ለተለያዩ ችግሮች ሊጋለጡ ይችላል። ይህን ችግራቸውን ለመፍታት ታዲያ በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በርካታ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል። ሥራውን መንግሥት ለብቻው ማከናወን ስለማይችልም ነው ዘለግ ላሉ ጊዜያት በተለይ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሲሠሩ የቆዩት።

ከነዚህ ውስጥ ላለፉት ሃምሳ ዓመታት በሕፃናት፣ ቤተሰቦቻቸውና በማኅበረሰብ ላይ ሲሠራ የቆየው ኤስ ኦ ኤስ የሕፃናት መንደሮች በኢትዮጵያ ተጠቃሽ ነው። ድርጅቱ ላለፉት አምስት አስርት ዓመታት ያስመዘገባቸውን ስኬቶች በመዘከር የተመሠረተበትን 50ኛ ዓመት ሲያከብር ቆይቷል። በዓሉ ተከታታይነት ያላቸው ሁነቶችን ተከናውነውበት ላለፉት አስር ወራት ሲከበር ቆይቶም ከሰሞኑ ተጠናቋል።

የኤስ ኦ ኤስ ሕፃናት መንደር በኢትዮጵያ ብሔራዊ ዳይሬክተር አቶ ሣሕለማርያም አበበ እንደሚናገሩት፣ ድርጅቱ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የሚሠራው የወላጅ ጥበቃና እንክብካቤ ያጡ ሕፃናትንና በተመሳሳይ ዕጣ ፈንታ በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሆኑ ሕፃናትን የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ በመስጠት በተለይ ደግሞ በቤተሰብ ማሕቀፍ ውስጥ እንዲያድጉ በማድረግ ለሁለንተናዊ እድገታቸው የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ በመስጠትና የወደፊት ዕጣ ፋንታቸውን የተቃና እንዲያደርጉ ማገዝ እንዲሁም በማኅበረሰብ ልማት ሥራ ላይ መሳተፍ ነው። ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ውስጥም 8 ነጥብ 1 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕፃናትን፣ ወጣቶችና ቤተሰቦቻቸውንና የማኅበረሰብ አባላትን ማገዝ ችሏል።

ድርጅቱ ከሚሰጣቸው ማኅበራዊ አገልግሎቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ልጆች በቤተሰቦቻቸው ማሕቀፍ ውስጥ እንዲያድጉ የሚያደርግበት፣ ቤተሰብን ከመበተን የሚታደግበት፣ ቤተሰብን አቅሙን በማጎልበት ልጆቹ ሁለንተናዊ እድገታቸው የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ መስጠት የሚችልበት አቅም የሚያመጣበት የቤተሰብ ማጠናከሪያና ማኅበረሰብ ልማት ፕሮግራም ነው። በአሁኑ ሰዓት በዚህ ፕሮግራም ብቻ በቁጥር ሀያሰባት የሚሆኑ የፕሮግራሙ አስፈፃሚዎች አሉ።

ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ምክንያቶች ልጆች ከቤተሰቦቻቸው ሊለዩ የሚችሉበት ሁኔታ ስላለና እነዚህ ልጆች ከቤተሰብ ማሕቀፍ ሲወጡ ደግሞ በአማራጭ የልጆች ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም ውስጥ እንዲታቀፉ ይደረጋል። በዚህ የአማራጭ የልጆች ጥበቃና እንክብካቤ ፕሮግራም ውስጥ ልጆች ከተቻለ የተቋጠረ ዝምድና ካላቸው ቤተሰቦች ጋር አብረው እንዲያድጉ ይደረጋል። ይህ ካልሆነ ደግሞ የአደራ ቤተሰቦች ውስጥ እንዲያድጉ ይደረጋል። ይህም ባይሆን እዛው ማኅበረሰቡ ውስጥ በጣም የአካባቢው ኑሮ አድማጭ መሠረት ካደረገ የልጆች አገልግሎት የሚሰጥ አደረጃጀት ካለ በዚህ ውስጥ እንዲያድጉ ይደረጋል። ከዚህ ባለፈ ደግሞ ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ መንደሮች መጥተው እንዲያድጉ ይደረጋል።

በሌላ በኩል ድርጅቱ በወጣቶች ልማት ፕሮግራም በርካታ ወጣቶችን ተደራሽ አድርጓል። በአደጋ ጊዜ ድጋፍ መስጫ ፕሮግራሞች ቁጥራቸው በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች ተጠቃሚ ሆነዋል። በተመሳሳይ በትምህርት ፕሮግራምም ድርጅቱ በራሱ ተቋማትና ከድርጅቱ ውጪ ባሉ ተቋማት በመንግሥት የትምህርት ተቋማት ውስጥ በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኙ ተደርጓል። በጤናም አገልግሎትም በርካታ ሕፃናትና ወጣቶች አገልግሎት እያገኙ ነው።

ባጠቃላይ በዚህ ዓመት ወደ 500 ሺ የሚሆኑ የፕሮግራሞች ተሳታፊዎች አሉ። እነዚህን የፕሮግራም ተሳታፊዎች ለማገዝ ወደ 1 ጥብ 4 ቢሊዮን ብር ወጪ ተደርጓል። የልጆችንና የማኅበረሰብ ሕይወት በዘላቂነት ከመለወጥ አንፃር ድርጅቱ ብዙ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። በልጆች ላይ የሚታየውን ችግር በስፋት ለመቅረፍ ድርጅቱ እ.ኤ.አ ከ2023 እስከ 2027 የሚዘልቅ ስትራቴጂክ እቅድ አዘጋጅቶ ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል።

በዚህ ስትራቴጂ እቅድ መሠረት እ.ኤ.አ እስከ 2027 ድረስ የተደራሽነቱን ቁጥር ወደ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን ለማሳደግ እቅድ ይዞ እየሠራ ነው። በሚቀጥሉት አስር ዓመታት ደግሞ የተደራሽነቱን ቁጥር ወደ 14 ሚሊዮን ለማሳደግ ያስባል። የሥራ ስምሪቱንም አገልግሎት ከመስጠት ጎን ለጎን ወደሌላ አቅጣጫ ማስፋት ይፈልጋል። በተመሳሳይ ሥራ ከተሠማሩ ድርጅቶች ጋር በጋራ መሥራትና በእነርሱ ብዙዎች ጋር መድረስ ይፈልጋል። ዋና በጀቱን በአስር ዓመታት ግዜ ውስጥ በራሱ አቅም ለመሸፈን እቅድ ይዟል።

# ዓለም አቀፍ



## ናታንያሁ የመከላከያ ሚኒስትሩን ማባረራቸውን ተከትሎ በእሥራኤል ተቃውሞ ተቀሰቀሰ

በጋዜጣው ሪፖርተር

የእሥራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ቤንያሚን ናታንያሁ የመከላከያ ሚኒስትሩን ዮአቭ ጋላንትን ማባረራቸውን ተከትሎ በሀገሪቷ ተቃውሞ ተቀሰቀሰ።

ናታንያሁ በእሳቸውና በመከላከያ ሚኒስትራቸው መካከል የተፈጠረው "የመተማመን ቀውስ" ወደዚህ ውሳኔ እንዳመራቸው ገልጸው በጋላንት ላይ ያላቸው እምነት በቅርብ ወራት ውስጥ "ተሸርሽሯል" ብለዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ እሥራኤል ካትስ እሳቸውን እንደሚተኩ ገልጸዋል። ጋላንት በበኩላቸው ከሥልጣን የተነሱት በሦስት ጉዳዮች ላይ በተፈጠረ አለመግባባት መሆኑን ገልጸዋል።

ከነዚህም መካከል እሥራኤል የቀሩትን ታጋቾች ከጋዛ ለመመለስ ስምምነቶችን ለመቀበል መሸከም የምትችለው ስምምነት ውስጥ ልትገባ ይገባል የሚለውን ጨምሮ ነው።

አደባባይ ላይ የወጡ በርካታ ተቃዋሚዎች ናታንያሁ ከሥልጣን እንዲወርዱ የጠየቁ ሲሆን አዲሱ የመከላከያ ሚኒስትር ታጋቾችን የማስለቀቅ ስምምነት እንዲያስቀድሙ ጥሪ አቅርበዋል።

ናታንያሁ እና ጋላንት ለረጅም ጊዜ ልዩነት በተሞላበት የሥራ ግንኙነት ቆይተዋል። እሥራኤል በጋዛ ላይ በምታደርገው የተቀናጀ ጥቃት ላይ ልትከተለው ስለሚገባ የጦርነት ስልት ላይ ከፍተኛ አለመግባባት እንዳሉ ሪፖርቶች ወጥተዋል።

የቀድሞው የመከላከያ ሚኒስትር እሥራኤል አክራሪ የሚባሉ የይሁዲ እምነት ተከታዮች በውትድርና ከመሰማራት ነፃ መደረጋቸው መቀጠሉ ደስተኛ አልነበሩም።

የጋዛ ጦርነት ባለፈው ዓመት መስከረም መጨረሻ ከመጀመሩ ከወራት በፊት ናታንያሁ የመከላከያ ሚኒስትሩን በፖለቲካ ልዩነት ምክንያት አባረዋቸው ነበር። ሆኖም ከፍተኛ የሕዝብ ተቃውሞን ተከትሎ ወደ ኃላፊነት ስፍራቸው እንዲመለሱ ተደርገው ነበር።

የመባረራቸውን ዜና ተከትሎ ጋላንት "የእሥራኤል መንግሥት ደኅንነት የሕይወቴ ተልዕኮ ሆኖ ይኖራል" ሲሉ በማኅበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ላይ ለጥፈዋል።

## ለትራምፕ ድምፃቸውን የሰጡ የማኅበረሰብ ክፍሎች የትኞቹ ናቸው

ዶናልድ ትራምፕ 47ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት በመሆን ትናንትና ተመርጠዋል። ዶናልድ ትራምፕ አሜሪካንን እ.አ.አ. ከ2016 እስከ 2020 ድረስ በፕሬዚዳንትነት ያገለገሉ ሲሆን ከአራት ዓመት በፊት በተካሄደ ተመሳሳይ ምርጫ በጆ ባይደን ተሸንፈው ሥልጣን አስረክበው ነበር፡፡

በአሜሪካ ፕሬዚዳንት ምርጫ ታሪክ ዶናልድ ትራምፕ በተከታታይ መምራት ያልቻሉ እና ዳግም በመወዳደር ፕሬዚዳንት መሆን የቻሉ ሁለተኛው ፕሬዚዳንት ሆነዋል ሲል ኤፒ ዘግቧል፡፡ ምክትላቸው ጄቫንስ ደግሞ የአሜሪካ 50ኛው ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ተመርጠዋል፡፡

ዶናልድ ትራምፕ በተለይም ወንዶች እና የኢኮኖሚ ጉዳይ ያሳሰባቸው አሜሪካውያንን ትኩረት ስበዋል ተብሏል፡፡ ትራምፕ በፍሎሪዳ በዌስት ፓልም ቢች ከደጋፊዎቻቸው ጋር በነበራቸው ቆይታ ቀጣዮቹን አራት አመታት የድንበር ጥበቃዎችን በማጠናከር እና ኢኮኖሚውን በማሻሻል ትኩረት እንደሚያደርጉ ተናግረዋል።

የሚጠብቀን ሥራ ከባድ እና አድካሚ ነው ያሉት የሪፐብሊካኑ ዕጩ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከሰቱ ጦርነቶችን እንደሚያስቆሙ የገቡትን ቃልም ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር እንደሌለ ተናግረዋል።

በዘንድሮ ምርጫ ትራምፕና ካማላ ሃሪስ የመራጮችን ድምፅ አገኝበታለሁ ያሏቸውን ከኢኮኖሚ እስከ ውጭ ጉዳይ ፖሊሲ፣ የድንበር ጥበቃ እና ሕገወጥ ስደተኝነት እንዲሁም በሌሎች ፖሊሲያዊ ጉዳዮች ላይ ሀሳባቸውን አቅርበዋል፡፡

ሀገሪቱ ወደ አሉታዊ አቅጣጫ እየተጓዘች ነው ብለው የሚያምኑ መራጮች 6 በመቶ ያህሉ ለትራምፕ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል፡፡ ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች አስፈላጊ ናቸው ያሉ መራጮች ደግሞ ከ79-80 በመቶ ትራምፕን መርጠዋል፡፡



ሴቶችን በተመለከተ ሃሪስ ከፍተኛ ድጋፍ እንደሚኖራቸው ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም ትራምፕ 51 በመቶ የሴቶችን ድምፅ ስለማግኘታቸው ተሰምቷል፡፡

ከቆዳ ቀለም ጋር በተያያዘ ደግሞ የትራምፕ የምርጫ ቅስቀሳ ቡድን ላቲን እና ጥቁር አሜሪካውያንን በማሳመን ደረጃ የተሳካ ሥራ መሠራቱን ሮይተርስ አስነብቧል፡፡

በ2020 አራት በመቶ ብቻ የላቲን አሜሪካን ድምፅ ባገኙበት የኔቫዳ ግዛት በዘንድሮው አመት 11 በመቶ ድምፅ መያዝ ችለዋል፡፡

በእድሜ ደረጃ ትራምፕ ከ18 እስከ 45 ዓመት እድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ አሜሪካውያን ዘንድ ተመራጭ ናቸው፡፡

በአንጻሩ ካማላ ሃሪስ በወጣት እድሜ እና በጎልማሳ እድሜ ላይ በሚገኙ ሴቶች እንደሁም ከ45 ዓመት በላይ በሚገኙ ሁለቱም ፆታዎች የተሻለ ድጋፍ አግኝተዋል፡፡

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

# በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ስኬታማ ለመሆን

**የሳይንስ፣ ቴክኖሉጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ሰነድ ሰሞኑን ይፋ ሲደረግ የግብዓት ማሰባሰቢያ ውይይት ሲካሄድ ሚኒስትሩ፤ ፖሊሲው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዲጂታላይዝ ለማድረግ የተያዘውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ያግዛል**

በዓለማችን ቀዳሚ 10 ኩባንያዎችን፤ ቢሊየነሮችን እንጥራ ቢባል በአንድም በሌላ በኩል ከኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሌጂ ጋር የተያያዙ ሆነው እናገኛለን። አፐል፣ ሜታ ሸርዝ፣ ማይክሮ ሶፍት፣ ጉግል፣ አልፋቤት፣ አማዞን፣ አሊባባ፣ ቴስላ፣ ወዘተረፈ በአብነት ማንሳት ይቻላል። በዚህ ዝርዝር ውስጥ ቦይንግን፣ ኤር ባስን፣ ቶዮታን፣ ኤክሶን፣ ብሪቲሽ ፔትሮሊየምን፣ ራምኮን ፈልገን አናገኛቸውም። የዓለማችን ቀዳሚ ቢሊየነሮችም እነ ኤለን መስክና ማርክ ዙከንበርግ ናቸው። ለዚህ ነው የጠራ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና የኢኖቬሽን ፖሊሲ እድገትን፣ ልማትንና ዓለማቀፍ ተወዳዳሪነትን ከማሳለጡ ባሻገር የብልጽግና ሞተር ነው የሚባለው።

ፖሊሲው በጥብቅ ዲስፐሊንና በትክክለኛ ስትራቴጂ ከተተገበረ ለሀገር በረከትና ትሩፋት ይዞ ይመጣል። ኢኮኖሚያዊ እድገትን ያመጣል። የስራ ዕድል ይፈጥራል። ተወዳዳሪነትን ይጨምራል። ሕይወትን ያቀላል። እንዲሁም ፖሊሲው ቀጣይነት ያለው ልማትን፤ ትምህርትን ለማጎልበትና ክህሎትን ለማሳደግ፤ የጤና አገልግሎትን ለማዘመን፤ ጥናትና ምርምር ለማሳለጥ፤ ሀገራዊ ደህንነትን እውን ለማድረግ፤ ሀገራችን ከዓለማቀፍ ተግዳሮቶች አንጻር ራሷን እንድታዘጋጅ እና በመንግስት መዋቅርና ተቋማት መካከል ቅንጅታዊ አሰራር እንዲፈጠር ያግዛል።

የተዋጣለት የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና የፈጠራ ፖሊሲ ተለዋዋጭ በሆነው ዓለም ሀገሪቱ ቅድሚያ ከምትሰጣቸው ዕቅዶች ጋር ለማስተሳሰር፣ ቀጣይነት ያለው ልማት ለማረጋገጥና ለፈተና የማይበገር ኢኮኖሚ እውን ለማድረግ ያግዛል። እንዲህ የገዘፈ ሀገራዊ ፋይዳ ያለው ፖሊሲን ለመተግበር በተዘጋጀ ስትራቴጂ ላይ የመከረ ውይይት ሰሞኑን ተካሂዷል። የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ወደትግበራ መግባቱ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ሀገራት ለማሰለፍ የተያዘውን ሀገራዊ እቅድ ለማሳካት መሠረት ይሆናል ሲሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ሰሞኑን መግለጻቸውን አዲስ ዘመን ዘግቧል።

የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ማስፈፀሚያ ስትራቴጂ ሰነድ ሰሞኑን ይፋ ሲደረግ የግብዓት ማሰባሰቢያ ውይይት ሲካሄድ ሚኒስትሩ፤ ፖሊሲው የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ዲጂታላይዝ ለማድረግ የተያዘውን ዕቅድ ከግብ ለማድረስ ያግዛል። አዲሱን ስትራቴጂ ተጠቅሞ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲውን በአግባቡ ለመተግበር ቁርጠኝነትን እና በትብብር መሥራትን እንደሚጠይቅ ጠቁመው፤ ሁሉም ባለድርሻዎች ለፖሊሲው ተግባራዊነት የየድርሻቸውን አስተዋጽኦ ማበርከት ይኖርባቸዋል። ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች፣ የልማት አጋሮችና ሌሎችም ባለድርሻዎች ለስትራቴጂው ተግባራዊነት የሚያደርጉትን ድጋፍ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ አቅርበዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ቴክኖሎጂ ለግብርና፣ ጤና፣ ትምህርት እንዲሁም አምራች ዘርፉ እድገት ላይ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተ መሆኑን አስታውሰው፤ ይህም ምርታማነትን ከማሳደግ ባለፈ የሥራ እድል ፈጠራን በማበረታታት በኩልም በር ከፋች ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። የፖሊሲው ትግበራ ኢትዮጵያን መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለማሰለፍ መሠረት ይሆናል። ስትራቴጂው በ2014 ዓ.ም የጸደቀውን የሳይንስ፣ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ወደ ትግበራ ለማስገባት የሚረዳ ነው ብለዋል።

ፖሊሲው ዘርፈ ብዙ ጉዳዮችን ያካተተ መሆኑን አንስተው፤ ስትራቴጂው ደግሞ የሌሎችን ሀገራት ልምዶች በመቀመርና ሀገራዊ ነባራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ባስገባ መልኩ ፖሊሲውን ወደ ትግበራ ለማስገባት የሚያስችሉ ዝርዝር እቅዶችን ያካተተ ነው። ለትግበራው የሚያስፈልጉ የሰው ሀብት፣ የፋይናንስ ምንጭና ከልማት አጋሮች ጋር በምን መልኩ መተባበር ይቻላል የሚሉትን እንዲሁም ሌሎችንም አስፈላጊ ጉዳዮች ያካተተ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል።

በርካታ የአፍሪካ ሀገራት የሳይንስ፣ ቴክሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ የላቸውም። ፖሊሲ ያላቸውም ማስፈጸሚያ ስትራቴጂ አላዘጋጁም በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ አንድ ርምጃ ወደፊት ተጉዛለች ብለዋል። የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ በ2014 ዓ.ም መጽደቁ የሚታወስ ሲሆን፤ ማስፈጸሚያ ስትራቴጂው ለቀጣይ 10 ዓመታት እንደሚያገለግል ተመላክቷል። ፖሊሲው ከወጣ በኋላ የማስፈጸሚያ ስትራቴጂው ለምን ይሄን ያህል ዘገየ የሚል ጥያቄ ማንሳት የተገባ ነው።

ሀገራት ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽንን በመጠቀም የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገታቸውን ፈጣን ቀጣይነት ያለው እና ተወዳዳሪ ማድረግ እንደቻሉ የዕድገት ታሪካቸው ያሳያል። በቅርብ ዓመታት ውስጥ አስደናቂና ፈጣን እድገት ያስመዘገቡት የደቡብ ምሥራቅ እስያ ሀገራት ስኬት ዋናው ምክንያት ሀገራቱ የቴክኖሎጂ እውቀትና ክህሎትን በመጠቀም ገበያ መር ኢኮኖሚን መገንባታቸውና የቴክኖሎጂ አቅም ማካበታቸው መሆኑ አንዱ ማሳያ ነው።

በሌላ በኩል የ2030 የዘላቂ ልማት ግቦችን እንዲሁም የአፍሪካ 2063 አጀንዳን ለማሳካት የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ወሳኝ ድርሻ አለው። በሀገራችን ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር ለማምጣትም ሆነ እድገቱን ቀጣይ ለማድረግ የሚኖረውን ሚና በመገንዘብ በ2004 ዓ.ም ትኩረቱን በመካከለኛና ትላልቅ የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ ቴክኖሎጂን መጠቀም፣ መቅዳትና ማላመድን መሠረት ያደረገ የሳቴኢ ፖሊሲ በማውጣት የተለያዩ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡

በፖሊሲው አፈጻጸም ሂደት የተገኙ ውጤቶች ቢኖሩም መሰረታዊ ለውጥ ከማምጣት አንፃር ግን ስኬታማ እንዳልነበር ከተደረጉ ጥናቶችና ዳሰሳዎች መረዳት ተችሏል። ይህ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ በዋናነትም በሀገራችን ከፍተኛ የኢኮኖሚ እድገት ቢኖርም ቴክኖሎጂን የመማር ሂደትን ከውጭ ቴክኖሎጂ ሽግግር በተጨማሪ በቴክኖሎጂ ልማት ላይ ትኩረት ለማድረግ፤ የኢንተርፕራይዞች አቅም በማሳደግ ከምርታማነት ጋር ያላቸው ትስስርን ለማጠናከር፤ ለፈጠራ ስራ /Innovation/ ትኩረት ለማድረግ፤ የፖሊሲው ዝግጅት አተገባበርና ክትትል ላይ በትኩረት መሥራት እንዲሁም የዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ጋር የተጣጣመ ፖሊሲ በማስፈለጉ ፖሊሲውን መከለስ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

ከ2012 ዓም አንስቶ ተግባራዊ የሆነው ሀገር በቀል የኢኮኖሚክ ማሻሻያ አጀንዳ ቀድሞ የልማት እድሎች ተደርገው ይወሰዱ ከነበሩት ከግብርና እና ከማኑፋክቸሪንግ በተጨማሪም ቱሪዝም፣ ማዕድን እና አይሲቲ አስቻይ የሆኑባቸው አገልግሎቶችን አዳዲስ የልማት ምንጮች አድርጎ ወስዷል። የኢኮኖሚ ማሻሻያ ዋና ዋና ግቦች የስራ እድል መፍጠር፣ የሀገሪቱን የውጭ ገቢ መጨመር፣ የአጠቃላይ ሀገራዊ ምርትን ማሳደግ፣ አዳዲስ ሀብት መፍጠር እና ወደ አካታች ብልጽግና መገስገስ ነው። ለዚህ ርዕይ ስኬት ደግሞ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ እንደ ወሳኝ የማስፈጸሚያ መሳሪያ ጥቅም ላይ እንደሚውል ተገልጿል።

በዚሁ መነሻነት ለአዳዲስ ለውጦች እና ፍላጎቶች ምላሽ መስጠት የሚችል እና የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማትን የሚያፋጥን ሁሉ አቀፍ ፖሊሲ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ከሶስት ዓመት በፊት ጸድቆ ወደ ስራ ገብቷል። በፖሊሲው ዝግጅት ሂደት የዘርፉ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ የሀገራት ተሞክሮ፣ የ10 ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በግብዓትነት ተወስደዋል። ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ ማሳካት እንዲችል የሰው ሀብት ልማት፤ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና የእውቀት አስተዳደር፤ ምርምርና ልማት፣ ኢኖቬሽንና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት፤ የፋይናንስ አቅርቦት፣ መዋዕለ-ንዋይ፣ ድጋፍና ማበረታቻ፤ ጥራትና አእምሯዊ ንብረት፤ ትብብርና ትስስር፤ አካባቢያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት ወሳኝ የፖሊሲ ጉዳዮች ተደርገው ተለይተዋል። የዚሁ ፖሊሲ ርዕይ፡-የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ርዕይ የተቀረፀው “ሀገራችን ለአፍሪካ የብልፅግና ተምሳሌት ሀገር ሆና ማየት ነው” ከሚለው መነሻ ሲሆን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ርዕይ የሚከተለው ነው።

“በ2030 በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ልማት ተወዳዳሪና ተመራጭ ሀገር ሆና ማየት”ሲሆን ተልዕኮው ደግሞ፡- ለሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ምቹ ሥነ-ምህዳር በመፍጠር፤ ዘርፉ ለሥራ ዕድል እና ለሀብት ፈጠራ እንዲሁም ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ዕድገት ያለውን ድርሻ ማሳደግ ነው።

**የፖሊሲው ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።**

1. ፍላጎትን መሰረት ያደረገ እና የቀጣይ ዘመን ኢንዱስትሪ ውስጥ በብቃት የሚሳተፍ የሰው ኃይል የሚፈጠርበትን ሥርዓት መዘርጋት፤
2. ለሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር፣ እንዲሁም ለኢኖቬሽን መደላድል ለመፍጠር የሚያስችሉ መሰረተ-ልማቶችን በቀጣይነት ማልማት፤
3. ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ቢዝነስን መሠረት ያደረጉ ኢኖቬሽኖችን በማበረታታት ለሥራ ዕድል፣ ለሀብት ፈጠራና ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት (GDP) ዕድገት የሚኖረውን ድርሻ ማሳደግ፤
4. በቴክኖሎጂ ልማትና ኢኖቬሽን የግሉን ዘርፍ ሚና በማሳደግ መሪነቱን ማረጋገጥ፤
5. የሀገር በቀል ዕውቀቶችን በማልማት ጥቅም ላይ ማዋል የሚያስችል የአደረጃጀት እና የአሠራር ሥርዓትን በመፍጠር የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል መገንባት፤
6. የተቋማት ትስስርና ትብብርን በማጠናከር ሀገራዊ፣ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ አጋርነት እና ተጠቃሚነትን ማሳደግ፤
7. ምቹ የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ሥነ-ምህዳር እንዲፈጠር የሚያስችሉ የሕግና የአሠራር ማዕቀፎችን መዘርጋት፤ ናቸው።

**የፖሊሲው አቅጣጫዎችና ስትራቴጂዎች**

በፖሊሲው ዝግጅት ሂደት የዘርፉ ነባራዊ ሁኔታዎች፣ የሀገራት ተሞክሮ፣ የ10 ዓመቱ ሀገራዊ የልማት እቅድ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በግብዓትነት ተወስደዋል። ፖሊሲው የታለመለትን ዓላማ ማሳካት እንዲችል የሰው ኃብት ልማት፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ሽግግር እና የእውቀት አስተዳደር፣ ምርምርና ልማት፣ ኢኖቬሽንና የኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪነት፣ የፋይናንስ አቅርቦት፣ መዋዕለ-ንዋይ፣ ድጋፍና ማበረታቻ ይሻል።

ጥራትና አእምሯዊ ንብረት፣ ትብብርና ትስስር፣ አካባቢ ማህበራዊና ባህላዊ ልማት ወሳኝ የፖሊሲ ጉዳዮች ተደርገው ታይተዋል። ለተለዩት ወሳኝ ጉዳዮች ግቦች እና የማስፈጸሚያ ስልቶች ተዘጋጅተውላቸዋል።

በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን፣ የምርምርና ልማት በሀገር ውስጥም ይሁን በውጭ የሚገኙ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የዕውቀትና የክህሎት አቅም እንዲሁም የአመለካከት ውስንነት በስፋት ይስተዋላል። ከሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደምንረዳው ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት መሰረታዊ ጉዳይ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መጠቀም እና መፍጠር የሚያስችል የሰው ኃይል ማልማት ነው።

ከመሰረታዊ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ በሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የተቃኘ መሰረታዊ የሰው ሀብት ልማት እንዲገነባ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ከዚህ በተጓዳኝ መጻኢውን ጊዜ ማዕከል ያደረገ የሰው ኃይል እንዲገነባ ጎን ለጎን ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ይተገበራል። በተጨማሪም ከሰው ኃይል ልማት አኳያ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን እንቅስቃሴን በብቃት መምራት የሚችል የሰው ኃይል ይገነባል። እንዲሁም ለዜጎች የተለያዩ የሳይንስ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ባህል ግንባታ ሊፈጥሩ የሚችሉ ከመደበኛው የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በተጓዳኝ የማህበረሰብ ልማት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሻሎም ! አሜን።

# ስፖርት





## ታምራት ቶላ የዓመቱ ምርጥ አትሌት ለመባል ተቃርቧል

**ቦጋለ አበበ**

የዓለም አትሌቲክስ ከሳምንት በፊት በተለያዩ ዘርፎች የዓመቱን ምርጥ አትሌቶች የመጀመሪያ ዕጩዎች ይፋ ማድረጉ ይታወቃል። «ከስታድየም ውጪ በተካሄዱ ውድድሮች» በሚል ዘርፍ ሁለት ወንድና ሁለት ሴት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በመጀመሪያው የዕጩነት ዝርዝር ውስጥ መካተታቸው የሚታወስ ሲሆን የመጨረሻ ዕጩዎችም ታውቀዋል።

በወንዶች የኦሊምፒክ ባለድሉ አትሌት ታምራት ቶላና በዚህ ወር አጋማሽ በቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን 57፡30 የሆነ ሰዓት በእጁ ያስገባው አትሌት ዮሚፍ ቀጀልቻ ከአምስቱ የመጀመሪያ ዕጩዎች መካተት ችለዋል። በተመሳሳይ በሴቶች አትሌት ትዕግስት ከተማና አትሌት ሱቱሜ አሰፋ የመጀመሪያ ዕጩዎች መሆን ችለው ነበር።

የዓለም አትሌቲክስ የመጨረሻዎቹን ሁለት ዕጩዎች ይፋ ሲያደርግ ታምራት ቶላ ብቻ ተፎካካሪ ሆኗል። ሽልማቱን ለማሸነፍ ከታምራት ጋር የመጨረሻው ተፎካካሪ ሆኖ የቀረበው የርምጃ ተወዳዳሪው ኢኳዶራዊ ብርያን ዳንኤል ፒንታዶ ነው።

የዓለም አትሌቲክስ የዓመቱን ምርጥ አትሌቶች አሸናፊ የሚለየው በሦስት መንገድ በሚሰበሰበው ድምፅ ነው። አንደኛው የአትሌቲክስ ቤተሰቦች (ባለሙያዎች) የሚሰጡት ድምፅ ሲሆን 25 በመቶ ነጥብ ይይዛል። ሁለተኛው ሕዝብ በማኅበራዊ ትስስር ገፆች (ፌስቡክ፣ ትዊተር ወይም X፣ ኢንስታግራም) ከሚሰጠው ድምፅ የሚሰበሰብ ሲሆን በተመሳሳይ 25 በመቶ ነጥብ አለው። 50 በመቶ ነጥብ የሚይዘው ድምፅ ደግሞ በዓለም አትሌቲክስ ምክር ቤት የሚሰጥ ይሆናል። በዚህም መሠረት ከሕዝብ የሚሰበሰበው ድምፅ ክፍት የተደረገ ሲሆን በመጪው እሁድ ይዘጋል። ማንኛው ሰው ይህን በተጠቀሱት የዓለም አትሌቲክስ ማኅበራዊ ገፆች ገብቶ ለሚፈልገው አትሌት ድምፅ መስጠት




ይችላል።

ከሕዝብና ከአትሌቲክስ ቤተሰቦች የሚሰበሰበው ድምፅ እንዳለ ሆኖ ትልቁን ነጥብ የሚይዘውን ድምፅ የሚሰጠው የዓለም አትሌቲክ ምክር ቤት ለአትሌቶች የተሻለ ነጥብ የሚሰጡት በውድድር ዓመቱ ያስመዘገቡትን ስኬት በማወዳደር ይሆናል። በዚህ ረገድ ታምራት ቶላ የመጨረሻ ዕጩ ሆኖ በቀረበበት ዘርፍ ከተፎካካሪው አኳያ የዓመቱ ምርጥ አትሌት የመሆን የተሻለ ዕድል እንደሚኖረው ይጠበቃል። ለዚህም የሁለቱን ተፎካካሪ አትሌቶች የውድድር ዓመቱን ስኬት በማነፃፀር ማስቀመጥ ይቻላል።

ታምራት ቶላ ከ2024 የውድድር ዓመት ሁለት ወራት ቀደም ብሎ በ2023 የኒውዮርክ ማራቶን የቦታውን ክብረወሰን በ2:04:58 ሰዓት ከአስራ ሁለት ዓመት በኋላ ማሻሻሉ አይዘነጋም። በዚህም በፓሪስ ኦሊምፒክ የኢትዮጵያ የማራቶን ቡድን ውስጥ በተጠባባቂነት መመረጥ ችሏል። በኦሊምፒክ ቡድኑ በተጠባባቂነት ለመመረጡ ሚያዝያ ወር ላይ በለንደን ማራቶን ሦስተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ቀደም ሲል ኒውዮርክ ላይ ካስመዘገበው ሰዓት በአንድ ማይክሮ ሰከንድ በዘገየ በ2:04:59 ሰዓት ማጠናቀቁ ይታወቃል።

ታምራት በፓሪሱ 2024 ኦሊምፒክ በቋሚነት የተመረጠው አትሌት ሲሳይ ለማ መታመሙን ተከትሎ ባገኘው የመወዳደር ዕድል ሳይጠበቅ ባለድል ሆኗል። ወጣቱ አትሌት ከ24 ዓመት በኋላ የኦሊምፒክ ማራቶንን ድል በአስደናቂ ብቃት ወደ ኢትዮጵያ ሲመልስ ያስመዘገበው 2፡06፡26 ሰዓት የኦሊምፒክ ክብረወሰን መሆኑ ድሉ እጥፍ ድርብ ነበር። ይህም እኤአ በ2008 ቤጂንግ ኦሊምፒክ ኬንያዊው አትሌት ሳሙኤል ዋንጂሩ ካስመዘገበው 02:06:32 የኦሊምፒክ ክብረወሰን በስምንት ሰከንድ የፈጠነ ነበር። ታምራት ቶላ ባለፈው ሳምንት ዳግም ወደ ኒውዮርክ ማራቶን ተመልሶ ድል ባይቀናውም ከዓለም ታላላቅ የማራቶን ውድድሮች አንዱ በሆነው ፉክክር በ2:08:12 ሰዓት አራተኛ ሆኖ ማጠናቀቁ ይታወሳል።

የዓመቱ ምርጥ አትሌት ለመሆን ከታምራት ጋር የሚፎካከረው ብሪያን ፒንታዶ በርምጃ ውድድር የውድድር ዓመቱ ስኬታማ አትሌት ነበር። ይህ አትሌት በፓሪሱ ኦሊምፒክ የ20 ኪሎ ሜትር ውድድር 1:18:55 ሰዓት በማጠናቀቅ የወርቅ ሜዳሊያ አጥልቋል። ይህም እኤአ 1996 ላይ በአትላንታ ኦሊምፒክ ጄፈርሰን ፔሬዝ ድል ቀጥሎ በርቀቱ ኦሊምፒክ ላይ ወርቅ ያጠለቀ ኢኳዶራዊ አትሌት አድርጎታል። ያስመዘገበው ሰዓትም እኤአ 2012 ለንደን ኦሊምፒክ ላይ ቼን ዲንግ ካስመዘገበው የርቀቱ የኦሊምፒክ ክብረወሰን በዘጠኝ ሰከንድ የዘገየ ነው። ከዚሁ በፓሪስ ኦሊምፒክ በዱላ ቅብብል የማራቶን ርምጃ ውድድር ከቡድኑ ጋር የብር ሜዳሊያ ማጥለቁ በውድድር ዓመቱ የሚጠቀስለት ስኬት ነው።

ኢኳዶራዊው አትሌት ከታምራት አኳያ ኦሊምፒክ ላይ ሁለት ሜዳሊያ በማጥለቅ የተሻለ ስኬት አለው። ይሁን እንጂ ታምራት ትልቅ ዋጋ የሚሰጠውን የኦሊምፒክ ክብረወሰን ያሻሻለ እንደመሆኑና በውድድር ዓመቱ ታላላቅ በሆኑት ለንደንና ኒውዮርክ ማራቶኖች ጥሩ ውጤት እንደማስመዝገቡ የዓመቱን ምርጥ ከስቴድየም ውጭ አትሌቶች ሽልማት የማሸነፍ ዕድል እንደሚኖረው ይጠበቃል።


## የስብሰባ ጥሪ ማስታወቂያ
## ለአኩፋዳ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ ባለአክሲዮኖች በሙሉ፤
## (3ኛ መደበኛ እና 3ኛ አስቸኳይ የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባዔ)

በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366፣ 367፣ 370፣ 372፣ 392 እና 400 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ የባለአክስዮኖች 3ኛ መደበኛ እና አስቸኳይ ዓመታዊ ጠቅላላ ጉባኤውን ህዳር 22 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2፡00 ሰዓት ጀምሮ በደ/ብርሃን ከተማ በደብረብርሃን ዩኒቨርሲቲ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለሚያካሂድ የተከበራችሁ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻችሁ በተጠቀሰው ቀን፣ ሰዓት እና ቦታ በጉባኤው እንድትገኙ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

### 1. የማህበሩ መረጃዎች

| | |
|---|---|
| የማኅበሩ ስም... | አኩፋዳ ማይክሮ ፋይናንስ ተቋም አ.ማ |
| የአክስዮን ማኅበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ... | ደ/ብርሃን እምዬ ምኒሊክ ክ/ከተማ አጼ ዘርዓያዕቆብ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ |
| የማኅበሩ ዌብ ሳይት | https://www.Akufadamf.com |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የምዝገባ ቁጥር | AM/BD/3/0004970/2014 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ አይነት ... | በማይክሮ ፋይናንስ ሥራ ላይ የተሰማራ አክሲዮን ማህበር |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ | 254,624,000.00 |
| የአክሲዮን ማኅበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ | 131,780,000.00 |

### 2. የ3ኛ ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1. እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2017 ዓ.ም ድረስ የተፈጸሙ ሽያጮችን እና ዝውውሮችን ተቀብሎ ማፅደቅ፣

2.2. እ.ኤ.አ የ2023/24 ሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን ማድመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.3. እ.ኤ.አ የ2023/24 ሒሳብ ዓመት የውጭ ኦዲተር ሪፖርትን ማድመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.4. እ.ኤ.አ የ2024/2025 ሒሳብ ዓመት የውጭ ኦዲተር መሾም እና የሥራ ዋጋ ክፍያ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.5. እ.ኤ.አ የ2023/24 ሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ ክፍፍልና አደላደል ላይ በዳይሬክተሮች ቦርድ ተዘጋጅቶ የቀረበውን መነሻ ሃሳብ ተወያይቶ ማፅደቅ፣

2.6. እ.ኤ.አ የ2023/2024 ሒሳብ ዓመት ለዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ስለሚከፈል ዓመታዊ የትርፍ ድርሻ እና እ.ኤ.አ 2024/2025 ሒሳብ ዓመት ስለሚከፈል ዓመታዊ የሥራ ዋጋ ተወያይቶ መወሰን፤

2.7. ለማኅበሩ ቅርበት ያላቸው ሰዎች ከማኅበሩ የሚወስዷቸው ብድሮች እና ዋስትናዎች ተወያይቶ ማፅደቅ፤

2.8. የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ ማዳመጥ እና ተወያይቶ ማፅደቅ፣

### 3. የ3ኛ ዓመታዊ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

3.1. የማኅበሩ መመስረቻ ጽሑፍ ማሻሻል

3.2. የጉባዔውን ቃለ ጉባኤ ማድመጥ እና ተወያየቶ ማፅደቅ

**ማሳሰቢያ፡-**

* በጉባኤው በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክስዮኖች በደ/ብርሃን ከተማ እምዬ ምኒልክ ክፍለ ከተማ አጼዘርዓያቆብ ሕንፃ 4ኛ ፎቅ የማይክሮ ፋይናንሱ አክሲዮን ሽያጭ እና አስተዳደር ክፍል ወይም በማይክሮ ፋይናንሱ ቅርንጫፎች በመገኘት በንግድ ሕግ አንቀፅ 377 መሰረት ከጉባዔው ሶስት ቀን በፊት በአካል በመቅረብ የውክልና ቅፅ መሙላት የሚችሉ መሆኑን በክብሮት እናሳውቃለን፡፡
* በውልና ማስረጃ ተረጋግጦ በጉባዔው ለመሳተፍ እና ድምፅ ለመስጠት ግልጽ ሥልጣን የሚሰጥ የውክልና ማስረጃ የያዘ ተወካይ በእለቱ የውክልናውን ዋና እና ኮፒ እንዲሁም የባለአክሲዮኑን መታወቂያ ኮፒ ይዞ በመቅረብ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላል፡፡
* በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፎች ቀርባችሁ ውክልና የምትሰጡም ሆነ በጉባዔው በአካል የምትገኙ ባለአክስዮኖች ማንነታችሁን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ መንጃ ፍቃድ ወይም ፓስፖርት ይዛችሁ እንድትቀርቡ እንዲሁም በውክልና በጉባዔው የምትገኙ ተወካዮች ማንነታችሁን የሚገልጽ መታወቂያ ዋናውን እና ኮፒ ይዛችሁ መቅረብ ይኖርባችኋል፡፡

**አኩፋዳ ማይክሮፋይናንስ ተቋም አ.ማ**
**የዳይሬክተሮች ቦርድ**
**WWW.akufadamf.com**